አንደኛ እትም ነሐሴ 2003 ዓ.ም.

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።
© All Rights Resereved

# አበሻው

ደራሲው፡- ጆን ክሪስቶፍ ሩፊን

ተርጓሚ፡- አያሌው ምትኩ ብሩ

1999 ዓ. ም.

# I

# ከሞት የተረፈው ሰው

## ትዕዛዝ

# 1

በሉዊስ አሥራ አራተኛ የዘይት ቀለም ቅብ ሥዕል የግራ ጉንጭ ላይ፣ በአስፈሪ ግርማ ሞገስ ሰፍቶ በተመልካች ዐይን ውስጥ የሚገባ የተሸራረፈ ጥቁር ጠብታ ታይታያል። በምሥራቁ ዓለም ውስጥ የዘይት ቀለም ቅቦችን እንደቁምጥና በሽታ እየሸራረፈ በመብላት መልካቸውን የሚያበላሸው ነገር፣ ቀስ በቀስ በዚህ ሥዕል ውስጥ በየዕለቱ እየተስፋፋ ነው። የነገ ቡኒ ሽበ የመሰለ፣ ጉልህነት የሌለው አስጠሊታ መስመርም ወደ ጆሮ ግንዱ አቅጣጫ እየተሣበ መሆኑ ይታያል። ቀረብ ብሎ ለሚመረምር ሰው፣ በስዕሉ አካል ላይ ጥቁር አክሊል በተጨማሪ ይመለከታል። በእግር ጣቶቹ ላይ ካሉት ነጠብጣቦች ሌላ፣ የቀረው ሁሉ የሚሰቀጥጥ ነው። በአጭሩ የፀሀዩ ንጉሥ ሥዕል ክፉኛ ተበላሽቷል።

ይህ ሥዕል፣ ካይሮ በሚገኘው የፈረንሣይ ቆንሲል መሥሪያ ቤት ላለፉት ሦስት ዓመቶች ተሰቅሎ ቆይቷል። ሥዕሉ ሲሰራ የራሱ የንጉሡ ግላዊ ቁጥጥርና እይታ አልተለየውም ነበር። ሥዕሉን በመጀመሪያ የሣለው ሂያንዝ ሪጋድ ሲሆን ስፍራውም ፓሪስ በሚገኝ የሥዕል ሥራ ቦታ ውስጥ ነበር። ከዚያም በባህር ወደ ካይሮ ይላካል። እንደመጥፎ ሰድል ሆኖ ካይሮ ውስጥም ይሁን በቅርብ ርቀት በሚገኙ የምሥራቅ ሜዲትራኒያን ጣቢያዎች ሊገኝ የሚችል ታዋቂ ሠዓሊ የለም። በዚህ የተነሣ ቆንሲሉ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በማያስደስቱ ሁለት እኩል ምርጫዎች መካከል ውሣኔ ማድረግ ነበረበት። አንደኛው መጥፎ ምርጫ ይህ በንጉሡ ሥዕል ላይ የሚታየው አስቀያሚ ጠባሣ፣ ሕዝብ እያየው እንዲኖር በመሥሪያ ቤቱ ሕንፃ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ተሰቅሎ እንዲቆይ መፍቀድ ነው። ሁለተኛው የማያስደስት አማራጭ ደግሞ፣ ብቁ ሙያ ለሌላቸው እጆች ምስጢሩን ገልጾ መስጠትና ሥዕሉ ፍፁም እንዲበላሽ የማድረግ ዕድል ነው። እንዲህ አጣብቂኝ ውስጥ የከተተውን ምርጫ ቁርጥ ያለ ውሣኔ ሰጥቶ ከመደመደሙ በፊት ዲፕሎማቱ ሙሴ ማይሌ፣ ጉዳዩን እያብሰለሰለ ለሦስት ወራት አቆየው።

ከሦስት ወራት በኋላ የጥገና ሥራውን ለማከናወን ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ካይሮ ውስጥ የሚኖር አንድ መድሃኒት ቀማሚ ግለሰብን መረጠ። ሰውዬው፣ በወቅቱ ካይሮ ውስጥ ከሚኖሩ ፈረንሣዊ ዝርያ ካላቸው መካከል ሲሆን፣ በአየር ጠባይ ምክንያት የተበላሹ የሸራ ላይ ሥዕሎችን የማደስ ችሎታ አለው ተብሎ የሚነገርለት ነው። ግለሰቡ፣ ረዥምና ጉብጥ ያለ ነው። ፊቱ ጥቅጥቅ ባለው በጥቁር ጎብስማ ጢሙ ሣቢያ ወደ ዓይኖቹ ሰርጉዶ ብሎ የገባ ይመስላል። የራስ ፀጉሩ ድብን ብሎ የተጠመዘዘ ጥቅል ይመስላል። ግዙፉን ሰውነቱን በተሸከሙት ረዣዥም ቅልጥሞቹ ሲራመድ፣ ያስጠላል። ይህ ሰው በሥራው ላይ በሚሆንበት ጊዜ ግን የሰውነት እንቅስቃሴው ፍፁም የተስተካከለ ነው። ሌሎች ሰዎች ሜትር ዠረሚ በሚባለው ስም ያውቁታል። ሜትር ዠረሚ ታማኝ ዜጋ የመሆኑ ዝና ይነገርለታል። ቆንሲል ዴ ማይሌ፣ የንጉሡን መልክ ለአንድ አክራሪ ፕሮቴስታንት አደራ በማለት የመስጠቱ ሃሣብ አልተዋጠለትም። ምክንያቱም ሰውዬው፣ በአንድ በሆነ ሰዓት ላይ የተስፋ መቁረጥ ሙከራ ሊፈፅም ይችላል። እንዲህ ያለው ባህርይ ደግሞ ቅጥ አምባሩ በጠፋው የካይሮ የውጭ አገር ማህበረሰብ መካከል ብርቅ አይደለም። ነገር ግን ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ሌላ ምርጫ አልነበረውም።

ትንሽ የልብስ ከረጢት ይዟል። የቆንሲሉ አሽቃባጮች እንደተተነበየው ቆንስላው ጽሕፈት ቤት እንዲገኝ የሚያገዘውን መጥሪያ ይዘው ትናንት ማታ መጥተው ነበር።

በመጨረሻው ሰዓት ላይ ሜትር ዠረሚ የጓደኛውን የጆን ባፕቲስትን ብልሀ ምክር ተቀብሏል። በአንድ አነስተኛ ከረጢት ውስጥ የንፅህና ዕቃዎችን፣ ንፁህ ሸሚዝና የኪስ መፅሃፍ ቅዱስ በመያዝ ከሰዓት በኋላ በግዴለሽነት አሣ ለማጥመድ እንደሚሄድ ሰው፣ እርሱም ወደ እሥሩ ተዘጋጀ።

በቆንስላው መግቢያ ላይ አንድ አገልጋይ መጥቶ በክብር ወሰደው። አስቀድሞ ወደ ሁለተኛው ፎቅ መራው። ከዚያም በላይኛው አዳራሽ ውስጥ ባለ አጭርና ስውር በር አልፈው አንዲት ትንሽ ክፍል ውስጥ ገቡ። ክፍሉ ቅዝቃዜ ያለው ነው። በክፍሉ መሃል ላይ ስፊውን ቦታ ይዞ የሚገኝ የምግብ ገበታ የሚሆን ጠረጴዛ አለ። ዙሪያውን፣ ማይሴ በሚል ጉትያ ጥልፍ ያጌጠ ነጭ የጠረጴዛ ልብስ ለብሷል። የሚያብረቀርቁ የመስተዋት ብርጭቆዎች፣ የፍራፍሬ ጭማቂ የያዘ ብሩህ የመስታወት ጆግ፣ ሁለት የሸክላ ስኒዎችና ትኩስ ዳቦ ተቀምጧል። የታዘዘውን ለመፈፀም ዝግጁ የሆነው አገልጋይ ወንበር ስቦ ሜትር ዠረሚ እንዲቀመጥ ጋበዘው። ነገር ግን መድሃኒት ቀማሚው እምቢ አለ። አንዳች የተፈጠረ ስህተት ስላለ በአስቸኳይ መታወቅ ይኖርበታል። ክፍሉና የሚታየው ዝግጅት ስህተት እንደሆነና እርሱ ወደመታሠሪያው መሄድ እንደሚፈልግ መናገር ሲጀምር አገልጋዩ ልጅ ከአጠገቡ ፈጥኖ ሄደ።

ቆንሲሉ ብዙም ሣይቆይ ደረሰ። ሲያዩት ጤናው ጥሩ አይመስልም። ዓይኖቹ ቀልተዋል። መሆን ከሚገባው በላይ ፊቱ ተኳኩሷል። ስሜቱ በተለየ ደስተኛ መሆኑን መንገዘብ አያዳግትም።

«ሜትር ዠረሚ! ስላገኘሁህ በጣም ደስ ብሎኛል፤ ታዲያ ምነው መቀመጫ አልተሰጠህ? እባክህ ቁጭ በል!»

ደነገጠ። አለማመኑን ሙሉ በሙሉ ሣይተው፣ ባለመድሃኒቱ ረዥም እካሉን በሚያስደስት አኳኋን አጣጥፎ ወንበር ላይ ተቀመጠ። ቆንሲሉ፣ መዓዛው ውብ የሆነ የሚንት



ሻይ አዝዞ፣ እንግዳውን ከመጠን በላይ መንከባከብ ሞከረ። ወተት፣ ስኳርና የማማሰያ ማንኪያ ሰጠው፡ የፍራፍሬ ጭማቂውንም በሁለቱም ብርጭቆዎች ውስጥ በራሱ እጅ ቀዳ። ያችን ቀጭን ሹል ጉራዴውን ባለመያዙ ሜትር ዠረሚ አዘነ። እርሷን ይዞ ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ ቧልት በአንድ ውግ ከፍጻሜ ያደርሰው ነበር።

«እኔ በሌለሁበት የተሰራ ቢሆንም ያከናወንከው ተግባር እጅግ በጣም ድንቅ ነው» አለ ሙሴ ጴ ማይሌ ቅንድቡን ከፍ አድርጎ።

ሜትር ዠረሚ የሚሰጠውን መልስ አላወቀም። ለራሱ እርጋታ እንዲሰጠው በማሰብ የቀረበለትን ብስኩት በአፉ ሙሉ ጉረሰና ጠበቀ። ምን ይከተል ይሆን በሚል ስጋት አፉን ዘጋ።

«ሥራህ ትልቅ ችሎታ የሚጠይቅ ነበር። የተለያዩ ዕፅዋትን አዋህዶ የተለያዩ ማጣበቂያዎች /ሙጫዎች/ እንዲሆኑ ማድረግ፣ መቀባትና መወልወል በእውነቱ ትልቅ ክህሎትን የሚጠይቅ ነው»

ሜትር ዠረሚ ጭንቅላቱን አንዴ ወደ ቀኝ፣ አንዴ ወደ ግራ እያጋደለና ትከሻውን እየነቀነቀ ማላመጡን ቀጠለ።

ምን እንደሆነ እንጃ እንጂ፣ በቆንሲሉ አዕምሮ ውስጥ አንድ ነገር አለ። ዲፕሎማቱ፣ በአንድ ትልቅ ስኒ ውስጥ የተቀዳውን ቡና በአንድ ትንፋሽ ሲጨልጠው፣ መድሃኒት ቀማሚው በበኩሉ የተጠራበት ጉዳይ ከዚህ በኋላ እንደሚቀጥል በልቡ አሰበ።

«እነዚህን ቅይጦች ለብዙ ጉዳዮች እንዲጠቅሙ ማድረግ ይቻላል። በዚህም ላይ ሌላው ቀርቶ መድሃኒት እንደምትቀምምም ስትናገር ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ ብሎ ነበር። ተሣሣትኩ?»

እንግዲህ ጀመርን ማለት ነው፣ ሲል ሜትር ዠረሚ አሰበ።

ከኋላዋ የሚገኝ ቁጥቋጦ ድንገት የተተረማመሰባት መስሏት የበረገገች ድኩላ ይመስል፣ ቁና ቁና መተንፈስ ጀመረ።

ቃስተውል ጀመር፡፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሲነገር ስለነበረው ስለአበሻ አገር ማሰብና ማሰላሰል ጀመረች፡፡ በዙሪያዋ ያለው ዓለምና የአበሻ አገር እጅግ በጣም ቅርቧ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን በቀላሉ አይደረስባቸውም፡፡ ሌሎች ልጆገረዶች ይህን ጊዜ ስለነዚህ አገሮች ያልሙ ይሆናል፡፡ በአንፃሩ በዚህ ቦታ እርስዋ ልትወለድበትም ትችል ነበር፡፡ ቀለሜ ጥቁር ቢሆን ኖሮ ብላ መቃዠትም ጀመረች፡፡ እንደ ወተት አረፋ በሚነጣው ክንዷ ላይ የሚገኘውን እምባሯን ተመለከተችውና ይኸው ብጫና አብረቅራቂ እምባር፣ በጥቁር መደብ ላይ ቢሆን ኖሮ ምን ሊመስል እንደሚችል ብላ አሰባ ተደነቀች፡፡ ክንዶችዋን በመስኮቱ ላይ እንዳሣረፈች በዙሪያዋ የሚገኙትን ቁሣቁሶች ሁሉ ዘንግታ ጤናማ በሆነው የራስዋ ተመስጦ ውስጥ ሰመጠች፡፡ የጊዜው መንኮድ ሣይታወቃት ሃሣቧን ከአንዱ ርዕስ ወደሌላው እያቀያየረች ጭልጥ አለች፡፡

እርስዋ በታች በሚገኘው ፎቅ የፊት ለፊት ደረጃ ላይ በድንገት ድምፅ ሰማች፡፡ ድምፁ በበሩ አጠገብ ሰው የተመለከተው የአባቷ ድምፅ ነበር፡፡ ሰውዬው ከፎቁ ሲወርድ በአይኖችዋ ተከታተለችው፡፡ ከኋላ ስትመለከተው ቀጭን፣ ባርኔጣ ያላደረገ፣ የራስ ቅሉ በሚዘናፈል ፀጉር የተሸፈነ፣ የቆዳ ቦት ጫማ ያጠለቀ ሰው ነው፡፡ በጠባቡ መንገድ ላይ ሲሄድ ቆም አለ፡፡ እርስዋም መከታተልዋን ቀጠለች፡፡ እርሱ ግን ከመንገዱ ፈንጠር ብሎ በመውጣት በመስኩ ላይ ተራመደ፡፡ እርስዋ ራሷ አስተውላው በነበረውና ከሌሎች ተራ እፅዋት ጋር ከማይመሣሰለው ትንሽ ዛፍ አጠገብ ሲደርስ ተንበረከከ፡፡

የጐብኚውን ሰው ቅርፅ መለየት ቻለች፡፡ ሰውዬው፣ ከትናንት በስቲያ በክሣሊጅ ድልድይ ላይ ያየችውና እስዋን በተለየ ሁኔታ ሲመለከታት የነበረው ነው፡፡ ተክለ ሰውነቱ ቀጭጭን ብሎ፣ማራኪ ቁመና ያለውን ነው፡፡ እንዴት ተዝናንቶ በርከክ እንዳለና እንዴትስ አድርጐ ቢላዋውን ከኪሱ ውስጥ እንዳወጣው፣ ቅርንጫፉንም እንዴት በቀላሉ እንደጨበጠው አስተዋለች፡፡ በቆንስላው ውስጥ ያጋጠሟት ጥቂት ሰዎች ሁለት ፍፁም ተፃራሪ የሚመስሉ ዓይነቶች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ የአጋጣሚ ዓይነት ምሁራን፣ ትሁቶች፣ ለራሣቸው ሙሉ ክብር የሚሰጡ፣ ግትሮች፣ በጣም የሚከበሩ፣ በተለይም በሚተገበር ጉዳይ ላይ ተፈጥሯዊ እንቅቃሴን ማከናወን የማይችሉ አስመሣዮች ናቸው፡፡ ሌላኞዎቹ ዓይነቶች ሕዝባውያን፣ ሁሉንም ተግባር የሚያከናውኑ ነገር ግን ከምንም የማይቆጠሩ ናቸው፡፡ ምግብ አዘጋጆች ይሁኑ፣ ጋሪ ነጂዎች ይሁኑ፣ ዘበኞች ይሁኑ እንደ ጠበብት ክችች ያሉ ናቸው፡፡ በዚህ ሣቢያ፣ ማንም ቢሆን ፀጥ፣ረጭ ብለው ተደብቀው ቢቆዩለት ይመርጣል፡፡ ከፊት ለፊትዋ የሚታየው ወጣት ግን



የሁለቱንም የህብረተሰብ ክፍሎች በጋራ አጣምሮ የያዘ ቅይጥ ይመስላል፡፡ ተክለ ሰውነቱ የጌታ ነው፡፡ ትዕግስቱ የአጃቢ ነው፡፡

እንዲህ እየተከታተለችው እያለች ምናልባት በድንገት እታይ ይሆን? የሚል ስጋት አልተሰማትም፡፡ በርስዋ ፍልስፍና በእንቅልፍ ላይ ያለ ሰው ከቶም እንደማይጋለጥ ሁሉ፣እሲስ አሁንም በህልም ዓለም ውስጥ ነች፡፡ ሆኖም ግን ይህ ወጣት ሰው ዓይኖቹን ወደርስዋ ወረወራቸው፡፡ በማህበረሰቡ መካከል፣ በማይታወቅ ሰው እየተመረመሩ ለሚኖሩ ሁሉ በጣም ጤነኛ የሆነው ይህ ልዩ ስሜት ከተሰማት ምን ያህል ጊዜ ይሆን ይሆን? በርግጥ ከህፃንነት ካለፈች በኋላ ምናልባት አንዳንድ ጊዜ አባቷ ራት ከሚጋብዛቸው ሽማግሌ ቀሣውስት በስተቀር እንዲህ ያለ ስሜት አንድም ጊዜ ተሰምቷት አያውቅም፡፡ ነገር ግን ራሱን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ሰመፈተሽ ያቀረበ፣ ተፈጥሯዊ አቋሙን የጠበቀና ግልፅ መደነቁን የሚገልፅ ሰው አይታ አታውቅም፡፡ እንዲህ ባለ ግራ መጋባት ውስጥ ሆና፣ ለርሱ ፈገግታ፣ የፈገግታ መልስ ሰጠች፡፡ ከመፍራቷ የተነሣ ከመስኮቱ ሦስት እርምጃ ወደኋላ ተራመደችና ወዲያውኑ ተፀፀተች፡፡ እጆችዋን ጀርባዋ ላይ አጣምራ፣ የመኝታ ክፍሏን የእንጨት በር እየዳበሰች፣ በሃይል እየተነፈሰች፣ ስሜቷ ታውኮባት ለረዥም ጊዜ ፀጥ ብላ ቆመች፡፡ በነዚያ ዐይኖች ውስጥ የነበረው የጋለ ስሜት ግን አመለጣት፡፡ ስሜታዊ መልስዋ ግን፣ አንድ ህፃን በጣም የሚያስደስት ገጠመኝን ተመልክቶ እንደመቦረቅ ፈንታ አደጋ ይኖራል ብሎ ሲያስብ እንደሚሮጥ ዓይነት ነው የሆነችው፡፡

ለምንስ ወደኋላ ተራመድኩ? ስትል ራስዋን ጠየቀች፡፡ ያ ወጣት የሚያስፈራ አይደለም፡፡ እኔም አልፈራሁም፡፡ አልፈራሁም፡፡ ከዚህም በላይ ፍፁም ታማኝና ትሁት ይመስላል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ አባቴ በፍፁም ወደዚህ አይጋብዘውም ነበር፡፡ በመስኮቱ ወደ ውጭ ማየቴ ምን ጥፋት ነው? አንድ ጐብኚ ከቆንስላው ግቢ ሲወጣ መመልከትስ ምን የሚያስነውር ነገር አለበት?

ለረዥም ጊዜ ከራሷ ጋር ተከራከረች፡፡ በመጨረሻም አንደኛው ሃሣብ አመዝኖ የክርክሩ ትግል ሲቋረጥ ተመልሣ ወደ መስኮቱ ሮጠች፡፡ እንግዳው ሰው ግን የለም፡፡

ጠበቀችው፡፡ ሰውዬው ግን አልተመለሰም፡፡ በመጨረሻም ፊቷን ወደ ክፍሉ መለሰች፡፡ በቤቱ ውስጥ ያለው ሙቀት ማቃጠል ጀምሯል፡፡ ከውጭ፣ ረጋ ባለው ነፋስ የሚወዛወዙት

በቅድሚያ ቢነገር ሌላ ነገር የማያስብ ሰው የለም። ለልጃችንም፣ ትንሽ ትንሽ ወጣ ማለት ይጠቅማታል። በዚያውም አካላዊ እንቅስቃሴ ታደርጋለች»

«ይህ እርኩሱ፣ እንዲያውስ በመጀመሪያ ደረጃ እንዴት ሊያስተውላት ቻለ?» አለ ድንገት ከተኛበት ደንብሮ በመቀመጥ። «በዚህ ቤት ውስጥ ምስጢራዊ ግንኙነት ፈፅመው ሊሆን ይችላል?»

«እንግዲህ ይህን ስታመነኝርክ አትዋል። ምን ጣጣ ነው? ልጃችን ጠንካራ ተፈጥሮአዊ ትህትና እንዳላት እኔ እናቷ እመሰክርላታለሁ። ሰወዬው ያነጋገራት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚያውም እኔ በቦታው ነበርኩ።»

በትንሿ የአትክልት ሥፍራ የነበረውን ሁኔታ በአጭሩ አስታወሰችው።

«እናም» ስትል ማዳም ዱ ማይሌ ቀጠለች። «ስለዕፅዋት አበቃቀል ያላትን ዝንባሌ ያወቀው ያን ጊዜ ነው። ሰውዬው ትክክል መሆኑን ላረጋግጥልህ እችላለሁ። በአትክልት ማብቀያ ውስጥ ከማበቅላቸው ትንንሽ ዕፅዋት መካከል በሙቀት ወይም በድርቁ ምክንያት ሸምድምድ የሚል ካለ ሁሌም ለአሊስ እሰጣታለሁ። ወደ ክፍሏ ትወስደውና ከጥቂት ቀናት በኋላ አረንጓዴና ጤነኛ ሆኖ መልሳ ትሰጠኛለች።»

ማዳም ዱ ማይሌ፣ በጥሩ ሁኔታ ተከራክራ ባሏን አሳመነችው። ፖንሴ፣ ከጉዞው የመመለስ እድል አይኖረውም ሲል ለራሱ አሰበ። የሰውዬው ሃሣብ ክብር የጉደለውና ሕገወጥ ዕቅድ ቢሆንም፣ ይህን ለማስፈፀም ግን ለምንጊዜውም ዕድሉ አይኖረውም። ይህን የመጨረሻ እንቅፋት በድል በመወጣቱ ሰላምና እርካታ አገኘ። ምንም እንኳ ለዚህ ሁሉ የርሱ ድርሻ ቢኖርበትም፣ ቆንሲሉ፣ ንቢያዊ አሽከሩን በጣም ተራ ማስታወሻ አስይዞ ላከው። «ልጄ፣ ከአባ ጋቦሬ ጋር ሆና ሁልጊዜ ማለዳ በቤትህ ተገኝታ እፅዋትህን ታጠናለች። አሁን ሂድ»



# 2

# ጉዞ ወደ አበሻ ሃገር

በቅድሚያ ቢነገር ሌላ ነገር የሚያስብ ሰው የለም። ለልጃችንም፣ ትንሽ ትንሽ ወጣ ማለት ይጠቅማታል። በዚያውም አካላዊ እንቅስቃሴ ታደርጋለች»

«ይህ እርኩሱ፣ እንዲያውስ በመጀመሪያ ደረጃ እንዴት ሊያስተውላት ቻለ?» አለ ድንገት ከተኛበት ደንብሮ በመቀመጥ። «በዚህ ቤት ውስጥ ምስጢራዊ ግንኙነት ፈፅመው ሊሆን ይችላል?»

«እንግዲህ ይህን ስታመነኝርክ አትዋል። ምን ጣጣ ነው? ልጃችን ጠንካራ ተፈጥሮአዊ ትህትና እንዳላት እኔ እናቷ እመሰክርላታለሁ። ሰወዬው ያነጋገራት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚያውም እኔ በቦታው ነበርኩ።»

በትንሿ የአትክልት ሥፍራ የነበረውን ሁኔታ በአጭሩ አስታወሰችው።

«አዎን» ስትል ማዳም ዱ ማይሌ ቀጠለች። «ስለዕፅዋት አበቃቀል ያላትን ዝንባሌ ያወቀው ያን ጊዜ ነው። ሰውዬው ትክክል መሆኑን ላረጋግጥልህ እችላለሁ። በአትክልት ማብቀያ ውስጥ ከማበቅላቸው ትንንሽ ዕፅዋት መካከል በሙቀት ወይም በድርቀ ምክንያት ሽምድምድ የሚል ካለ ሁሌም ለአሊስ እሰጣታለሁ። ወደ ክፍሏ ትወስደውና ከጥቂት ቀናት በኋላ አረንጓዴና ጤነኛ ሆኖ መልሳ ትሰጠኛለች።»

ማዳም ዱ ማይሌ፣ በጥሩ ሁኔታ ተከራክራ ባሏን አሳመነችው። ፖንሴ፣ ከንቱው የመመለስ እድል አይኖረውም ሲል ለራሱ አሰበ። የሰውዬው ሦሣብ ክብር የጐደለውና ሕገወጥ ዕቅድ ቢሆንም፣ ይህን ለማስፈፀም ግን ለምንጊዜውም ዕድሉ አይኖረውም። ይህን የመጨረሻ እንቅፋት በድል በመወጣቱ ሰላምና እርካታ አገኘ። ምንም እንኳ ለዚህ ሁሉ የርሱ ድርሻ ቢኖርበትም፣ ቆንሲሉ፣ ኑቢያዊ አሽከሩን በጣም ተራ ማስታወሻ አስይዞ ላከው። «ልጁ፣ ከአባ ጋቦሬ ጋር ሆና ሁልጊዜ ማለዳ በቤትህ ተገኝታ እፅዋትህን ታጠናለች። አሁን ሂድ»



# 2

# ጉዞ ወደ አበሻ ሃገር

ትዕይንቱን ክርቀት ሲመለከቱ የነበሩት አባ ብሬሼደንት፣ ጆን ባፕቲስት እጠገብ ለመቀመጥ መጡ። ካህኑ ከጥቂት ቀናት በፊት ካጋጠማቸው ሥቃይ ቢያገግሙም፣ ሁኔታቸው ግን አሁንም የሚያጠራጥርና አስፈሪ ነው።

«ይህን ያህል ጊዜ ለምን ቆየ? ከመነሣታችን በፊት ሁኔታውን ሊያሣየን ይችል ነበር» ሲሉ የግመሎችን ጌታ በመጠራጠር እየተመለከቱ አጉረመረሙ።

«መሆን አልነበረበትም። ካይሮን ከመልቀቃችን በፊት የኔ ህክምና ውጤት አልባ ቢሆን ኖሮ፣ ምን ሊሆን እንደሚችል እስቲ ያስቡ። ንጉሡንም ማዳን አይችልም፣ ተብዬ በድፍረት ተነግሮብኝ ጉዞውም ይሰረዝ ነበር። አሁን ባለንበት ደረጃ ላይ ግን ፣ ሃጂ አሊ፣ ከፍለነው ራሣችንንም በርሱ ሥር አድርገናል። እዚህ ቢተወን፣ ጥቅሙ በአመዛኙ የርሱ ነው?»

ሁለቱም ዝም አሉ። የካህኑ አዕምሮ ከመቼውም በበለጠ በጨለምተኛ አስተሣሰቦች እንደተወጠረ፣ ጆን ባፕቲስት ገመተ።

እንደ እውነቱ ከሆነ አባ ዴ ብሬቬደንትም ቢሆኑ፣ በጆን ባፕቲስት የሕክምና ችሎታ ላይ እምነት የላቸውም። ዕፅዋትን ለማየት በተጓዙባቸው ጊዜያት የመድሃኒት አዋቂው ችሎታ ምን ያህል ትንሽ እንደሆነ እንዲያዩ አስችሏቸዋል። ጆን ባፕቲስት ግን፣ በምንም ዓይነት የሚወናበድ ሰው አይደለም። «የሥነ-ዕፅዋት ዕውቀት ከመድሃኒት ጋር አንድ ዓይነት ነገር አይደለም። በሕክምና ጥናት የሚፈለገው ትጋት፣ የተፈጥሮ አስተዋይነት፣ ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል ያለውን የስሜት ቅርርብ መገንዘብ ነው። በሕክምና ጥናት የሚፈለገው፣ በሕመምተኛው ሰውና እርሱን ሊፈውስ በሚችለው ዕፅ መካከል ያለውን አስፈላጊ ስምምነት ማግኘት የመቻል ጉዳይ ነው»

እኒህን ጆላጆል ብሬቬደንትን በተመለከተ ከሆነ፣ እንደ አስማት አንድ ዘርፍ አድርገው ያስባሉ። እነዚህ በሃሣብ ያሉ ግን እውነት ያልሆኑ ጉዳዮች ዛሬ በሃጂ አሊ ላይ፣ እና ነገ ደግሞ በንጉሡ ላይ ምን ያህል ከባድ ጉዳት እንደሚኖራቸው አያውቁም። ይህን በተመለከተ ወደ ኋላ መመለስ በጣም የዘገየ ጉዳይ ነው። የጄስዊቱ ካህንም ዕጣ ፈንታቸው፣ ለልማት ወይም ለጥፋት ቢሆን ከዚህ እንግዳ ከሆነ የዕፅ ሃኪም ጋር አስተሳስረውታል።



የውይይቱን ርዕስ ለመለወጥና ድባቡም ቀለል እንዲል ለማድረግ በማሰብ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ጭውውቱን አል-ዋህ በተባለው በዚህ የበረሃ ገነት የሆነ መንደር ስም ላይ እንዲያተኩር አደረገ።

«ሥሙ የመጣው አል-ሃዌህ ማለት አየር ከሚለው ይመስለኛል። ስሙ በአካባቢው ካለው ቅዝቃዜና የተምር ቅጠሎች ያለዕረፍት እየተንሻሹ ከሚፈጥሩት ትንፋሽ ሊሆን ይችላል»

ብሬቬደንት፣ በሌላ በኩል፣ ሃላዋ ማለት ጣፋጭ ማለት ነው ወደሚለው ትርጓሜ ይበልጥ አደሉ። በቋንቋው ዕድገትና ታሪክ ላይ ያላቸውን ልዩነት አንድ ተወላጅ ሰው እንዲዳኛቸው ወሰኑ።በመጀመሪያ ያገኙዋቸው አንድ ሽማግሌ ሰው ሁለት አህዮችን ይነዱ ነበር። ቅርጫቶቻቸው በተምር የተሞሉ ሲሆን፣ ከከብቶቹ ጉን እየተራመዱ በትንሽ ዘንግ እንስሳቱን ወጋ ወጋ ያደርጓቸዋል።

አረቦች ቋንቋቸውን ይወድዳሉ። ቋንቋን በሚመለከት፣ በቃላት ላይ የሚነሱ አለመግባባቶችን ሁልጊዜም ያስተናግዳሉ። ሽማግሌው፣ ሁለቱን ተጓዦች እንዳገኟቸው ጭርምትምት ያለው ፊታቸው በታላቅ ፈገግታ ተዘረጋጋ። ሁለቱ ፈረንሣዊያን፣ የየራሣቸውን አስተያየት በአጭሩ ገለፁላቸው። ሽማግሌው፣ በያዙት ዘንግ የሻምላ ስንዘራን እንደማክሸፍ ዓይነት የብሬቬዳንትን ደረት ወጋ አደረጉና

«አይደለም!»

ቀጥሎም ወደ ፖንሴ ዞሩና እርሱም ላይ እንደዚያው ካደረጉ በኋላ «አል-ዋህ» አሉ። ቃሉን በተወላጆች ቅላጼ ተናገሩና እንዲከተሏቸው በዓይናቸው ጠቀሷቸው።

ሽማግሌው እየመሯቸው፣ ጆን ባፕቲስትና ብሬቬደንት እየተከተሏቸው፣ ሁለቱ አህዮች ከኋላ እየተጎተቱ መስኩ በተመነጠረበት ቦታ አቋረጠው አይን ምድር እንዲደርቅ የሚያደርገው ለብል ያለበትን ማሣ አልፈው በመታረስ ላይ ያለውን ቦታ አቋርጠው ጥቅጥቅ ያለ ጥቁር አረንጓዴ ቅጠል ያለባቸው የቁጥቋጦዎች ጥሻ ውስጥ ገቡ። ወደ ትንንሾቹ ዛፎች በበትራቸው እያመለከቱ ሦስት ጊዜ ተናገሩ።

«አል-ዋህ!»

ድምፅ እንዳታሰማ አስጠንቀቀቻት። አሊስ፣ ራሷን አረጋጋችና ሁለቱም ሴቶች በዝምታ ርስ በርሳቸው ተያዩ። በመስኮት የታየችው ሴት፣ በዕድሜ በሰል ያለች ነበረች። ሴትዮዋ፣ በርቀት ከሚገኝ የሕይወት ጫፍ የወረደችና በርስዋ ዕድሜ ማንም ሊደርስባት የማይችል መስለቻት። ከአርባ ዓመት በላይ ይሆናታል። ጠንካራና ውብ የገበሬ ሴት ቁመና ያላትና ፊትዋ ሙልት ያለ ነች። ዐይኖችዋ፣ ፈገግታ የተሞሉና ጉላ ጉላ ያሉ ናቸው። ወዲያውኑ፣ በአንድነት መንፈስ ስሜት እንዳየቻት፣ በድሃ ኩራት የአይኖችዋን ብርሃን ለቀቀችባቸው። ተራ የሆነ ጥቁር ቡኒ የአገልጋይ ልብስ ስለለበሰች፣ ድቡልቡሎቹ ክንዶችዋ፣ ጠንካራዎቹ ትከሻዎችዋና ፍርጥም ያሉት ጡቶችዋ ከቅርጫት ውስጥ ሞልቶ የሚፈስስ ፍሬ ይመስሳሉ።

«አይዞሽ ጓደኛሽ ነኝ፣ ጓደኛሽ ነኝ» እያለች በአንድ እጅዋ ምልክት በመስጠት ስታንሾካሹክላት ሌላው እጅዋ ከንፈሮችዋ ላይ እንደተቀመጠ ነበር።

አሊስ፣ አቅሏ መመለሱን ስትመለከት፣ አሁንም ዝቅ ባለ ድምፅ «ሂጂና ቂሱ ተኝተው እንደሆን ተመልከቺቸው» አለቻት።

ወጣቷ ልጃገረድም የተነገራትን ፈፀመች።

ወደ ታችኛው ፎቅ ስትወርድ ስለቄሱ እንዴት ማወቅ ቻለች? ስትል በመገረም ራሷን አወዛወዘች።

አባ ጋቦሬ በሰላም ያንኮራፋሉ።

«እኔው ወደታች፣ እመጣለሁ» ስትል ሴትዮዋ ተናገረች።

በዚህ ላይ ወጣቷ ልጃገረድ ልትጨቃጨቅ አልፈለገችም። ይልቁንስ፣ ይህች ጠንካራ ሴት በመስኮቱ ላይ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና ወጥታ፣ ዱካዋ እንደማይሰማ ድመት አርከኑ ላይ ስትዘልል ተመለከተቻት። ተከረዝ የለሽ ሰንደል ጫማ ብታደርግም፣ አሊስ ትረዝማለች። የተጨማደደውን ቀሚሰዋን በእጇ መዳፍ አንድ ሁለት ጊዜ ሳብ፣ ሳብ አድርጋ ካስተካከለች በኋላ፣ ወጣቷ ልጃገረድ አጠገብ ደረሰች። የአሊስን ሁለት እጆች በወዳጃዊ ስሜት በመያዝና ወደ ራስዋ ሳብ በማድረግ፣ በአድናቆት ከላይ እስከታች ቃኘቻት።

«እንደተባለውም በርግጥም ቆንጆ ነሽ» አለቻት



አሊስ በንግግሩ አፈረች። እንዲያውም ቀይ ወፍራም አበባ የሆነች መሰላት።

«እርሱ ከተናገረውም የበለጠ ቆንጆ ነሽ» ስትል አከለች።

በሴትዮዋ ፊት ላይ አንዳች የርህራሄና የማፅናናት ሁኔታ ይነበባል። ፈገግታዋ፣ በዓይኖችዋና በከንፈሮችዋ ዙሪያ የሚታዩት የፊት መሸብሸቦች፣ እንባና የመከራ ዘመናት አብረዋት እንደዘለቁ ያመለክታሉ። እንዲህ ንፁህ በሆነው ደስታዋ ላይ እነዚህ ነገሮች ጥልቅ የፍቅር ስበት ኃይልን ይጨምራሉ።

«ማነው እሱ?» ስትል ጠየቀች

«ዠረሚ ነዋ! ሌላ ማን ይሆናል» አለች ሴትዮዋ እየሣቀች

ማዳሞዜል ዴ ማይሌ፣ በፊትዋ ላይ የሚነበበውን ቅሬታ መደበቅ አልቻለችም።

«ስለዚህ ጉዳይ የነገረኝም እርሱ ነው» ስትል ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ አክላ ተናገረች።

የአሊስን እጅ ይዛ ወደ አንድ ወንበር ወስዳት እንድትቀመጥ አደረገቻት። እርስዋ ግን ወደ ፎቅ መውጫው ላይ ባለው የደረጃ መደገፊያ ላይ ተደገፈች።

«ባለፉት ሁለት ሣምንታት ስከታተልሽ ነበር። ስለአንቺ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ። ስሞሽን አውቃለሁ። ከማን ጋር ፍቅር እንደያዘሽም አውቃለሁ። በርግጥ ይህ ንግግሬ ተገቢ አይደለም። ስለራሴ ጥቂት ነገሮችን ልንገርሽ። ስሜ፣ ፍራንቾይዝ ይባላል። የምኖረው እዚህ ቤት ውስጥ ነው። ሁለቱ ጌቶች፣ እዚህ ቤት በነበሩ ጊዜ በየዕለቱ እየመጣሁ ምግባቸውን አዘጋጅላቸው ነበር። ይህ ማረጋገጫ ሊሆንሽ ይችላል?»

«እሥን . . . የለም . . . እኔ እንጃ አላውቅም» አለች አሊስ ግራ ገብቷት።

«በርግጥ ከቀናት በፊት ሳነጋግርሽ ይገባኝ ነበር። ታዲያ ፋይዳ ያለው ሥራ ሳላከናውን፣ እዚሁ ከአስር ጫማ በላይ በማይርቅ ቦታ ሆኜ፣ አንቺን ማየት የሚያስደስተኝ መሰለሽ?»

ለማየትና ለማድነቅ ቻሉ። በዚህ አካባቢ የወንዙ ዳርቻ መሬት ከውሃው ወለል በላይ ከሁለትና ከሶስት ጫማ የበለጠ አይረዝምም። መሬቱም በግብፅ እንደሚሆነው በየዓመቱ በጐርፍ አይጥለቀለቅም። ሰዎች በሰሩት የማያቋርጥ መዘውር በግድቦቻቸውና በቦዮቻቸው ተጠቅመው ሰብሎቻቸው በመስኖ ይለማሉ። ወደ ቤተመንግስት እንደተመለሱ አገረ ገዥው በግብርና ላይ ስላለው እቅድና አውራጃውን በትክክል በማስተዳደሩ መደነቁን በማክል ፖንሴ ገለፀ።

«ከተማዋን ልትንከባከባት ከፈለግህ ያንተው ናት። እዚህ ሃኪም ሆነህ መኖር ትችላለህ። ነገውኑ ሸለቆው ውስጥ ሃያ ኤከር መሬትና በዚያ ላይ የሚሠሩ ሰላሣ ቤተሰቦችን እሰጥሃለሁ። ከተማው ውስጥም ቤት፣ በግመሎችና በአረብ ፈረሶች የተሞላ ጋጣም ይኖርሃል። እመነኝ ደስተኛ ትሆናለህ።»

ሃጂ አሊ፣ ጠቃሚ ሰው መሆኑን በድጋሚ አስመሰከረ። በትህትና፣ ለአገረ ገዥው፣ ይህ ፈረንሣዊ የአበሻውን ንጉስ ሲጐበኝ እንደሚጓዝ ገልፆ ለተደረገላቸው ታላቅ መስተንግዶና ስጦታ ሲመለሱ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ገለፀ። የአባይ ሰዎች አበሻዎችን የውሃ ጌቶች አድርገው ያስቧቸዋል። የውሃውን መነሻ ስለሚቆጣጠሩት የፍሰት አቅጣጫውን ሊለውጡት ወይም እስከናካቴው ሊያደርቁት ይችላሉ ብለው ይገምታሉ። «የውሃዎችን አባት» ማስቆጣት የሚታሰብ ነገር አይደለም። ስለዚህም አገረ-ገዥው ዝቅ ብሎ እጅ ነሣ።

በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ፣ ከፖንሴ ታካሚዎች የሚሰማው ዜና እጅግ በጣም ጥሩ ነበር። በያንዳንዱ ቀን የማይታመን ማገገምና መዳን ይሰማል። አባ ብሬቬደንት እያጉረመረሙም ቢሆን፣ ምንም ምንም ይሁን ምን፣ ይህ ወጣት የማዳን አቅም እንዳለው አምነው ተቀበሉ። የሌሎችን ሰዎች ስቃይ በጥንቃቄ ለመመርመርና ለመፈተሽ፣ ብሎም ለመፈወስ ችሎታው አለው። ከሰዎች ጋር ያለው መግባባትና መቀራረብም ፍፁም ንፁህ መልክ ያለው ነው። ህፃን ልጅን ሲመለከት፣ በልጁ ውስጥ ፈገግታ ይጫራል። እንስሳት ሳይቀሩ፣ የርሱ በዙሪያቸው መገኘት ርጋታን የሚሰጣቸው ይመስላል። በመንገድ ላይ የሚወጡና ሰዎችን በሩቅ የሚሸሹ አስቀያሚና አስፈሪ እከካም ውሾች፣ መግቢቸውም ባያውቅ በደመነፍስ ከተማው ውስጥ ይከተሉታል። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ሁሉ ጋር ያለው ግብነትና ስምምነት ከጥብቁና ከክባዱ ብሎ ካለው ቅዱስ አግናጢዮስ ይልቅ ከሞኛሞኞች የቅዱስ ፍራንሲስካ ተከታዮቹ አስተሳሰብ ጋር እጅግ ይመሣሰላል። ጀስዊቶች፣ እንዲህ ያለውን የልጅ ቂላቂልነት በርግጥ



አያደንቁም። በሌላ በኩል የፖንሴ ስጦታዎች እንደ አካባቢው ቋንቋዎችና እምነቶች እንዳችም ዓላማን እንደማያገለግል የእውነተኛውን እምነት ምክንያቶች ግን በምስጢር ለማሣካት የሚጠቅም ዓይነት ነው። ፖንሴ፣ ወደ አቢሲኒያ የሚያስገባውን እጅግ ድንቅ ፖስፖርት አስገኝቷል። ብሬቬደንት ደግሞ ከዚህ የሚገኘውን ጥቅም በሚገባ መጠቀም ይኖርባቸል።

በመጨረሻ የሚለቅቁበትና የሚሄዱበት ሁኔታ ተስተካክሎ ተዘጋጀ። ለመጨረሻው ስንብት በአንድ ቦታ ላይ ለምሽት ግብዣ ተጠሩ። ቅፍለቱ እስሚቀጥለው ማለዳ አይንቀሳቀስም። ምክንያቱም በአጐራባች አገሮች ሊገጥማቸው የሚችለውን አደጋ በመፍራት፣ ጉዟቸው በቀን እንዲሆን ወስነዋል።

በበሩ ላይ የመሷጠጥ አይነት ድምፅ በሚሰማበት ጊዜ ፖንሴ በክፍሉ ውስጥ ዕረፍት ላይ ነበር። ምናልባት ከተማ ውስጥ አንድ የታመመን ሰው እንዲመለከት ሊሰምነው መልዕክተኛ መጥቶ ይሆናል። ማን እንደሆነ ለመለየት ብቅ ሲል ፀጉሩን የተላጨ በአፍንጫው ላይ ንፍጡ የሚወርድበት፣ ግማሽ ሰውነቱ እርቃኑን የሆነ አንድ ደካማ፣ ትንሽ ጥቁር ልጅ የማስታወሻ ወረቀት አውጥቶ ሰጠው። ደብዳቤውን ፖንሴ ከፈተው። የተፃፈው በፈረንሳይኛ ነበር።

«መጥተህ እንድንገናኝ። ይህ ህፃን ያሳይሃል»

የእጅ ፅሁፉ አጣጣል እንዳይለይ ቃላቱ የተፃፉት በትልልቅ ፊደላት ነው። በዚያም ላይ መልዕክቱ አልተፈረመበትም።

ፖንሴ በምድር ቤቱ ውስጥ የተኙትን አባ ብሬቬደንትን ቀስቅሶ፣ አብረውት እንዲሄዱ ሊጠይቃቸው ወሰነ። ቀጥሎም የተዘጋጀውና ይዞት የሚሄደውን ሻንጣውን ተመለከተ። ከዚያ ውስጥ አንድ ጕራዴ መዝዞ ታጠቀ። ሌላ አንድ ትልቅ ፖቤ አውጥቶ፣ በፍርሃት ለሚንቀጠቀጡት ጀስዊት ሰጣቸው። ጭለማው እየበረታ፣ ለአይን ያዝ ማድረግ በጀመረበት ሰዓት ትንሹ ልጅ እየመራቸው ወሰዳቸው። የከተማው መሃል በሰዎች የተሞላ ነው። ቀኑን ሙሉ ከቤታቸው ውስጥ የሚቆዩት የከተማው ነዋሪዎች፣ ከመስኮት የለሹ ቤታቸው ቀስ እያሉ በመውጣት ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው እያወሩ ይመላለሳሉ።

እንዲያከምለት ፖንሴን ለመነውና የቁስል መጥረጊያውን እንደ ሀማዕት ተቋቋመው:: ከአራቱ ተጓዦች መካከል ከዚህ አጭርና የድል አድራጊነት ተጋድሎ በኋላ ቆስሎ የተገኘው እርሱ ብቻ ነው::

የንጉሱ ብቀላ ሊደርስባቸው ከሚችለው እጅግ እርቀው መገኘታቸውን በመገመት፣ በየመንደሩ ጥጋጥግ እያንዣበቡ መንዝ የአካባቢውን ተወላጆች ጥርጣሬ ከሚያስፈልገው በላይ ስለሚቀሰቅስ፣ እንደ ሰላማዊ ተጓዦች በግልፅ መሄድ እንደሚሻል ጆን ባፕቲስት ገለፀ:: ከዚህ በኋላ ሕይወታቸውም ይበልጥ የተመቻቸ ሆነ:: የሚያገኟቸው ጉሳዎች፣ ጥቃት የሌለበት መስተንግዶ ያደርጉላቸዋል:: ከርቀት ቦታዎችም፣ ነጮን ቆዳቸውን ለማየት ይመጡ ጀመር:: አንዳንዶችም እየፈሩ ይነኳቸዋል:: የአካባቢው ተወላጆች ሞቅ ያለ አቀባበል ያደርጉላቸው ጀመር:: የተጣሏቸው ጉሣዎች የተጋጪቸው፣ ንብረታቸው በድብቅ በመወሰዱ ተቆጥተው ነው:: በወዳጃዊ ስሜት ከተጠየቁ ያላቸውን ለመስጠት ወደ ኋላ የማያሉ ናቸው:: ለተጓዦቹ የማሽላ ቂጣዎችና አፍሪካውያን ከፍተኛ ጥራት ያለው የሚሉትን ትኩስ የላም ደም ተደባልቆበት የተመታ ትልቅ ወጪት ወተት ይሰጧቸዋል:: እንደ ቀላል የመልካም አቀባበል ማረጋገጫ ከዘመዶቻቸው ውብ የሆኑ ኮረዳዎችንም ያቀርቡላቸዋል:: ፖንሴና ሜትር ዣረሚ ለረዥም ሰዓታት በኮርቻ ላይ ስለሚውሉ አልጋ ላይ ከወደቁ በኋላ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ከመተኛት ሌላ የሚያስቡት የለም:: የተመረጡላቸው ሴቶች ከጎናቸው እንዲተኙ ቢጋበዙም፣ ጥቂትም ሣያቆዩ ማንኮራፋት ይጀምራሉ:: ከማንቀላፋታቸው በፊት ግን ተጓዳኞቻቸው ሙሉ አካላዊ ክፍላቸውን ያሳዩዋቸዋል:: በኋላ እንደገለፁላቸው ከሆነ እነዚህ አብረዋቸው እንዲያድሩ የሚደረጉት ወጣት ሴቶች አብይ ተግባራቸው፣ በሚቀጥለው ቀን ለማህበረሰቡ በሞላ የነዚህ የተጓዦች ፍፁም የግላቸው የሆነው የአካል ክፍላቸው ምን አይነት ቀለም እንዳለው ሪፖርት ማቅረብ ነው:: ለእነዚህ ተወላጆች ይህ እንግዳ የሆነው ነጭ የቆዳ ቀለም ከባዕዳኑ ሰውነት ላይ፣ ከላይ እስከታች ድረስ መዝለቁን የአይን ምስክር ሆኖ የሚያረጋግጥላቸው ስለሌለ ለማሣመን አስቸጋሪ ነበር::

አባ ብሬቬደንት የሚደረግላቸውን ክብር በምንም መልክ እምቢ እንዳይሉና እነርሱ የሚያርጉትን እንዲከተሉ ጓደኞቻቸው መክረዋቸው ነበር:: እርሳቸውም፣ ለዘንዶ እንዳይጣሉ በመፍራት ሌሊቱን ሙሉ የፀፀት ፀሎት ሲፀልዩ ያድራሉ:: በእግራቸው ላይ ካለው እብጠት በዘላል ቢድኑም፣ ባጋጠማቸው መከራ ቢደክሙም፣ የቀራቸውን የጤንነት ጉዳይ ይበልጥ



አባባሉት:: ሜትር ዣረሚ እያሾፈ ክብረ ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ እንዳልሆነ የቅዱስ አግናጢዮስን ትዕዛዝ በመውሰድ፣ እንደፈሣ መሆን ነውና ጥቅም የለውም ይላል::

ሃጅ አሊ፣ እንዲህ ባሉ ትክክለኛውን ነገር በመፈፀም ጉዳይ ራሱን አያስጨንቅም:: እርሱ አሁን እየተጨነቀ ያለው በወጉት እሾሆች ሲሆን ለአመል ሲነኩት ይጮሃል:: የሚያደርገው ቢኖር የነዚህን ያልሰለጠኑ ሰዎች ባህል ማንኳሰስና እስልምና እስካሁን እነርሱን ባለማሰልጠኑ በማዘን የሚሰጠው አስተያየት ነው::

በዚህ አይነት ሁኔታ ከአንዱ መንደር ወደ ሌላው ለአምስት ቀናት ከተጓዙ በኋላ፣ ገሬፅም ከተባለ ትልቅ ከተማ ደረሱ:: ገሬፅም፣ በዘንባባ ዛፎች የተከበበች፣ በጉዋባ፣ በሮማን፣ በአቦካዶና በብርቱካን አበባዎችና ፍሬዎች የተዋበች ነች:: በቀቀኖችና ሌሎች ብሩህ ቀለማት ያሏቸው አዕዋፋት በየዛፎቹ ውስጥ አርፈው ሲታዩ ለብዙ ቀናት የተጓዦቹ ብቸኛ አጃቢዎች ሆነው በሰማይ ላይ ይታዩ ከነበሩት ጥንብ አንሣዎች ይልቅ ተስማሚ ለውጦች ናቸው::

እሁንም ረዥሙንና ለሙን የሰሜን ሸለቆ እስኪደርሱ ወደ ሰርኬ የሚወስዳቸው ገና የሁለት ቀናት አጫጭር የምድረበዳ ጉዞ ይቀራቸዋል:: የጥጥ ተክል በሰበሱ ነጫጭ ኮረብታዎች ዙሪያዋን የተከበበችው ከተማ፣ ትልቅ የንግድ ቦታ ነች:: በከተማዋ መካከል እረፍት የለሽ ገበያ አለ:: ከአካባቢው በሚጉርፈው የስራ ውጤት የሚያማምሩት ደማቅ የጥጥ ልብሶች፣ በከተማው ውስጥ ተሸምነው በጥሬ ማቅለሚያዎች፣ በከርሚን፣ በጥቁር ሰማያዊ፣ በብርቱካንማ ቀለማት ተሰርተው ይታያሉ:: የቅመም መዓዛ በገበያው አየር ውስጥ ይንሣፈፋል:: በየመደብሩ፣ ውብ ሽታ ያላቸው የኢትዮጵያ ሽቀጦች ይታያሉ:: ከተማዋ፣ የመሸገሪያ ድልድይ ባላት በአንዲት ቀጭን ምንጭ አጠገብ የተመሠረተች ናት:: በርቀት ያለችው አገር አቢሲኒያ ነች:: የረዣዥምም ተራራዎች ምድሮች ቅርፅ በአቧራማው አይታ ውስጥ ሲጠፋ ይታያል::

***

ድልድዩን እኩለ ለሊት በስድስት ሰዓት ላይ አቋረጡት:: በዙሪያቸው ከነበረው አንዳችም የተለወጠ ነገር ባይኖርም ከወንዙ ማዶ እግራቸው መሬቱን ሲረግጥ መንፈሣቸው ተነሳስቶ

ተሠርቶ፣ በጭቃ፣ በጥድና በከብት እበት ድብልቅ የተመረገ ነው። ወለሉ በቆሻሻ የተሞላ ነበር። በአጠቃላይ አንድን በሽተኛ ሰው ለማስታመም የሚሆን አመች ቦታ አልነበረም። ጊዜያዊ በሆነችው ጠባብ አልጋቸው ላይ የተኙት ምስኪኑ ዮሴፍ፣ ዕለት በዕለት ይበልጥ ወደ መቃብራቸው ይጠጉ ጀመር። ሰጡዬው ብርታታቸውን ከሚገባው በላይ ገምተው ነበር። ለተልዕኳቸው የነበራቸው ፍፁም ታዛዥነት፣ እንደርሣቸው ያለ ፅጥ ያለ የቤተመፃሕፍት ምቾትን የለመደ ምሁር፣ በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ጉዞ ላይ የሚገጥማቸውን ፈተና በሰንሰለት ተቆራኝተው እንደተፈረደባቸው ሰዎች በፅናት እንደሚወጡት እንዲያምኑ አድርጓቸዋል። ነገር ግን እያደር የሚጨምረው ድቀታቸው ሰውነታቸውን ለበሽታ ስላጋለጣቸው፣ የጥድ እንጨት እሣት ቀኑን ሙሉ እንዲነድና እንዲሞቃቸው ግድ ሆነ። ጆሰዊቱ በርግጥ በሚያሣዝን ሁኔታ ላይ ነበሩ። ረኻቶሙና ግዙፉ ሰውነታቸው እንደሃረግ ጥምልምል አለ። የሚተነፍሱት በአፋቸው ስለሆን ከራሳቸው ሰውነት የሚመጨነው የትኩሣት ሙቀት ከንፈሮቻቸውን አደረቀባቸው። ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዠረሚ በካህኑ አልጋ አጠገብ ተራ በተራ መቀመጥ ጀመሩ። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ፕሮቴስታንቱ ሲያደርግላቸው የነበረው ርህራሄ እየተዘነጋቸው፣ ይህ መናፍቅ አጠገባቸው መሆኑን ህሊናቸው መለስ ሲል ሲያውቁ፣ ፍፁም የጥላቻ ርግማናቸውን ይገልፃሉ። ጤናቸው እንደሚመለስና እንደሚድኑም ስለሚያምኑ ተልዕኳቸውን እንደሚፈፅሙ ያምናሉ። አንዳንድ ጊዜ በሚያስደስት ቅላፄ ከውስጥ፣ ከአንጀታቸው መንጭቶ አቢሲኒያን እንደምን የሃይማኖታቸው መስመር ተከታይ እንደሚያደርጓት ታላቁን እቅዳቸውን ለረዥም ሰዓት ያብራራሉ።

«አስቀድሞ የምንፈልገው የአቢሲኒያን ህዝቦች ባህል፣ ጠባይና ቋንቋ መገንዘብ ነው። አዎን፣ ቋንቋቸውን ማወቅ ነው። እዚያ እንደደረስን እኔ ቋንቋውን ማጥናት እጀምራለሁ። ስለቋንቋው ፈረንሣይ ውስጥ መጠነኛ ነገር ተምሬአለሁ። በርግጥ የሚናገረው ሰው የለም። ሰዎችን ለማግባባት የሚያስችለው ጉዳና ቋንቋ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ እምነታቸው . . . አስቀድመህ ግን በትክክል ልታውቃቸው ይገባሃል። ትልቁ ምስጢርም ይኸው ነው። አውሮፓ ውስጥ እምነት ያልነበራቸውን አረማውያን ባህላዊ ክብረ በዓላት፣ ቀናቱ፣ ቦታዎቹና አስተሣሰቦቹ ተመሣሣይ ሆነው የቤተክርስቲያን ስርዓቶች ተክተዋቸዋል።»

አንዳንድ ጊዜ በአልጋቸው አጠገብ ያለው ማንም ይሁን ማን ጨበጥ ያደርጋሉ። በመጨረሻም ፖንሴ እየመሠላቸው በስህተት ከሜትር ዠረሚ ጋር ሣይቀር ያወሩ ነበር።



«በአያት ቅድመ አያቶቻችን የተፈፀሙትን ስህተቶች እንደግማቸውም። ልክ አይደለም እንዴ? አስቀድመን ሕዝቡንና ካህናቱን ሳንለውጥ በፊት ንጉሡ ሃይማኖቱን እንዲለውጥ መደረግ የለበትም. . . »

ጆስዊቱ በጣዕረሞት ተይዘው ሣሉ እንኳ፣ ውርደትን በትህትና ለመቀበል የነበራቸው ፈቃደኝነት፣ ይህም የታላቅ ክብራቸው መገለጫ መሆኑን ያሣዩ ነበር። የሃይማኖት ማህበራቸውን ደንብ በፍፁም ታዛዥነት ሲቀበሉ ሁሉንም አይነት ግላዊ ምኞቶች ይክዱናሉ። ይህን የሚያደርጉት ሥልጣንን በሙሉ ሃይል ለመጠቀም ከዘመናት በፊት የታቀደውን የተጠራቀመ ጉጉት ለማገልገል ሲሉ ነበር። አንድን ንጉስና ግዛቱን ለመግዛት አስቀድሞ በውሃ ቀጅነት ማገልገልን የሚመርጡ ሰው ነበሩ። ጆን ባፕቲስት፣ ለካህኑ አኳኋን፣ ጥንካሬና ብስለት አትኩረት ቢሠጥም፣ የጆስዊቱ ህመም እየጠናባቸው መጣ። ቄሱም በቅርብ እንደሚሞቱ አወቀ። የመሞታቸውን ሁኔታ ሲረዱ የታዛዥነት ፍቅራቸው አዲስ መስመር አበጀ። ለቅዱስ ተልዕኳቸው ፍላጐት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ቢያስገዙም፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም የሚለውን ሃሣብ ተቀበሉ። ራሣቸውን ሙሉ በሙሉ በህመማቸው ስር በመጣል፣ የተወሰነው ዕጣ ፈንታቸው ለዚህ እንደላካቸው መሣለፅ ጀመሩ። ከዚህ በኋላ ቀጣይ ህክምና መስጠት ጥቅም አልነበረውም። ሃጅ አሊ እያምባረቀባቸው ትዕዛዝ ይሠጣቸው እንደነበረው ሁሉ ለሞት ጥሪም ታዛዥ ሆነው ከሁለት ቀን በኋላ አረፉ።

ፖንሴና ዠረሚ በግቢው ውስጥ ያለው የግራር ዛፍ ባጠላበት ቦታ ቄሱን ለመቅበር ፈለጉ። ይሁን እንጂ ያረፉበት ቤት ባለቤት፣ ቤቱን የሠራው ቅድመ አያቱ እጅግ ክፉኛ ታመው ሲሞቱ የተቀበሩበት ቦታ በመሆኑ አይሆንም አላቸው። ይህንን መጥፎ የጉዞ ጓደኛ አስከሬን በዚያ ውስጥ በመጨመር፣ መቃብሩን ለዘላለም ማርከስ ከጥያቄ ውጭ ነው ሲል ባለቤቱ ተቃወመ።

በዚያን እለት ማታ ወደ ባቂላ ማሣ በሚወስደው ጠባብ መንገድ፣ ጠፍ በሆነ መሬት ዳርቻ ላይ ጠለቅ ያለ ጉድባ ቆፍረው የጆስዊቱን አስከሬን ቀበሩ። የተከፈኑት በለበሱትና ሃጅ አሊ ሁጊዜም እየተቆጩ በሚያጠራበት የአረብ ሸሚዛቸው ነው። መፅሃፍ ቅዱስን በመጥቀስ ሜትር ዠረሚ አጠር ያለ ፍትሃት ሲያደርግ፣ በዚያ ቦታ የነበረው ብቸኛው ካቶሊክ ፖንሴ፣ እንዲህ ላለው ሥነ-ስርዓት ልምድ የሌለው በመሆኑና ምን ማድረግ እንዳለበትም ስለማያውቅ

«አሁን በጣም ትክክል እንደሆነ አምናለሁ» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ በመመፃደቅ ዓይነት «እርማቶቹን ካስገባህ በኋላ እንደገና አንድ ጊዜ እናነበውና ከዚያ በኋላ ይላካል።»

ሙሴ ማቼ ብድግ አለና እንደ ፅሕፈት ቤት ወደምታገለግለውና ወደምታፍነው የእቃ ማስቀመጫ ክፍሉ አመራ።

ቆንሲሉ፣ ከወፍራሙ የመስኮት መጋረጃ በስተኋላ ትንሽ ፈቅ ብሎ ልጁ በመኖሪያ ቤቱ ያሉትን እፅዋት ልትንከባከባቸው ስትሄድ በስስት ተመለከታት። የደስደስ ያለውን ቁመናዋን፣ ረጋ ያለ አረማመዷንና ከሕፃንነት ወጥታ ኮስተር የማለቷን ሁኔታ አደነቀ።

ጋብቻ እንድትፈፅም መወሰን ያለብኝ ጊዜ ነው።

## ፲፮

«ይህች አውሬ የምትችለውን ሁሉ በማድረግ ልትጥለኝ ትፈልጋለች»

ሜትር ዠረሚ ትንሿን ፈረስ ለመቆጣጠር ክብደቱን ሁሉ ተጠቀመ። ፈረሷ ግን በፍርሃት ዓይኖቿ ዘለለች። ሃጅ አሊ አንዱን አገልጋይ ሲያመለክተው ወዲያውኑ ለኮንውን ያዘ።

«አሁን የመዝናናትና ግጹለሽ የሚሆንበት ጊዜ አይደለም።» አለ ጆን ባፕቲስት ልጓሙን በሁለት እጆቹ ጨብጦና ፈረሱ እንድትራመድ ጥረት በማድረግ ሲሳካለት።

ከአረቦች መኖሪያ ወጥተው፣መንደሩን ከዋናው ከተማ የሚለየውን አነስተኛ ምንጭ ተሻገሩ። ከዚህ በኋላ በሙስሊም ጥምጣም መሸፈናቸው ቀርቶ፣ ለሁሉም ሰው አውሮፖውያን መሆናቸውን በግልፅ ማሣየት ጀመሩ። በጠቦቹ የከተማው መንገዶች ውስጥ የሚጉርፈው ህዝብ እነርሱን በተመለከተ አንዳችም ጉጉት ሣያሣይ ረጋ ያለ ነበር። ለዚህ ደግሞ ብዙ ምክንያቶችም ነበሩ። በመጀመሪያ ደረጃ ለምድረ በዳው የፀሐይ ቃጠሎ ለረዥም ጊዜ ተጋልጦ የነበረው የሁለቱ ፈረንሣውያን ቆዳ ጠቆር ስላለ፣ ይህ ቀለም ከአቢሲኒያ ክርስቲያኖች ጋር ይቀራረባል። ሁለተኛ፣ ጐንደር ውስጥ በቁጥር ብዙ የውጭ ዜጐች ስለሚኖሩ ሕዝቡ የመልኩን ቀለምና ቅርፅ ለምዶታል። ብዙዎቹ ግሪካውያንና አርመናውያን ሲሆኑ ጥቂት



ደቡባዊ እስላሞች አሉባቸው። እነዚህ ሠዎች የአቶማንን የአገዛዝ ቀንበር ሲሸሹ፣ በአበሻው ንጉስ ጥገኝነት የተሠጣቸውና ጥበቃም የሚደረግላቸው ናቸው። በመጨረሻም እንግዶቹ ቀስ በቀስ የሚያውቁት አንድ ነገር አለ። አቢሲኒያውያን ስሜታቸውን ወይም አስተሣሠባቸውን በግልፅ ማሣወቅ አይወድዱም። በዚያም አለ በዚህ፣ ሁለቱ ጓደኛሞች ስለነዚህ ጉዳዮች ምንም ሳያስተውሉ ለረዥም ጊዜ ሲያልሟት የነበረችውን የዚህችን የተረት ተረት ያህል የምትታወቅ አገር አካል መሆናቸውን በደስታ እያሰላሰሉ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ጥቅጥቅ ያለውና ግራጫ መሆን ዳጀመረው የሜትር ዠረሚ ጺም፣ የብልህና የአዋቂ ሞገስ ሲሰጠው፣ የጆን ባፕቲስት በጣም ጥቁርና የተጥመለመለው ፀጉሩ፣ ትኩስ ቁመናው፣ ግርማ ሞገስ ያለው ዛላውና፣የመጓጓትና በደስታ የመሞላት ስሜቱ ጉን ለጉን ሲጓዙ ወጣት ሃብታም አስመስሎታል።

ወደ ቤተመንግስቱ በዝግታ እየወጡ ሳሉ፣ የተሠበሠበው ሕዝብ በመሃል እንዲያልፉ መንገድ ይለቅቁላቸው ነበር። ወንዶችም ሴቶችም አንድ አይነት ተራ ካባ፣ አንድ ወጥ በሚመስለው ቀጭን ትከሻቸው ላይ ለብሰዋል። ምጥጥ ያለው፣ የታወቀ ቅርፅና መጠን ያላቸው ትልልቅ አይኖቻቸውና ቀጥ ያለው ቁመናቸው፣ ጆንን ባላባቶች ያስመስላቸዋል። ድል ከተመቱ አገሮች የመጡ ባሮች ፊታቸው ሻክሮና ጉብጦ እርስ በእርሳቸው እየተለፋለፉ ሲጓዙ መለየት በጣም ቀላል ነው።

ከተማው አሁንም ቢሆን ጦራቸውን፣ የቆዳ ጋሻቸውንና በቅርቡ በተደረገው ዘመቻ የተያዙ እስረኞችን ይዘው በመንገዶች መሃል በሚንቀሣቀሱ የታጠቁ ወታደሮች እንደተሞላ ነው። አንድ ገለጥ ያለ፣ ከዚያም ሣር የሸፈነው አካባቢ ምናልባትም የስልፍ ወይም የስብሰባ ቦታ ሣይሆን የማይቀር ሲያልፉ ሜትር ዠረሚ ወደ ጆን ባፕቲስት ዞር አለ።

«ከትናንት ወዲያ ስለሠማነው ጉዳይ መግለጫው ይኸውና»

በቅርቡ ንጉሡ ድል ያደረጋቸው አንድ ሃያ ምርኮኛ ተዋጊዎች፣ አደባባዩ ውስጥ ያቃስቱ ነበር። ጥቂቶች ስብርባሪ ድንጋዮች ላይ ተቀምጠዋል። ሌሎች ደግሞ ክንዶቻቸውን ዘርግተው ቆመዋል። አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ደግሞ ጭንቅላቶታቸውን በእጆቻቸው ሸፍነው መሬት ላይ ተጋድመዋል። ሁሉም በነዚያ ጥቋቁር ፊቶቻቸው መሃል ሁለት የደም ምልክቶች በአይኖቻቸው ላይ ነበሩባቸው።

ራስ ዮሐንስ በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ እንዲሰፍን አዘዙ። ሰዎችም ፀጥ አሉ። ከዚያም አንድ አጭር ሰው ከባለስልጣናቱ መካከል ወጥተው ወደፊት ተራመዱ። ቢጫ ብርቱካንማ የመነኩሴ ልብስ ለብሠዋል። ያበጡት አይኖቻቸው አጥርተው አያዩላቸውምና በዙሪያቸው የሚገኘውን በጭጋግ ውስጥ የሚያዩ ይመስላቸዋል።

«ክርስቶስ ስንት ባህርያት አሉት?» ሲሉ እንደቃጭል በቀጠነ ድምፅ ጠየቁ።

የጥያቄዎቹ ሁሉ እምብርት ይህ ነው። ጄስዊቶች ለረዥም ጊዜ የተፋረጉበት ጥያቄ ነው። ነጥቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የሮማ ቤተክርስቲያን ከአስራ ሁለት ክፍለ ዘመናት በፊት እንዲለያዩና በየራሣቸው መንገድ እንዲጓዙ ያደረጋቸውና ሊገለፅ ያልቻለ ውስብስብ የመንፈሣዊ ትምህርት ጉዳይ ነው። ሁለቱ መንገደኞች ቀደም ሲል ባደረጉት መሠናዶ ውስጥ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ይነሣሉ ብለው ዝግጅት አላደረጉም ነበር። በጣም በግልፅ እንደሚታወቀው እንዲህ ያለ ከባድ ሃሣብ ይነሣል ብሎ የተጨነቀም ሰው አልነበረም። ሜትር ዠረሚ ወደ ጆን ባፕቲስት ሲመለከት ጥልቅ የመደነቅ ስሜት በፊቱ ላይ አስተዋለበት።



# 10

«ክርስቶስ ስንት ባህርያት አሉት?» ሲሉ መነኩሴው ለሁለተኛ ጊዜ ጠየቁ።

ከባድ ዝምታ በክፍሉ ሁሉ ላይ ሰፈነ። ሁሉም ዓይኖች ምንም ወደማይናገረው ወደ ጆን ባፕቲስት ዞሩ። ከዚያም በድንገት አንዳች መንፈስ አነሣሣውና ተበረታታ።

«ክርስቶስ ስንት፣ ስንት ባህርያት አሉት የሚለውንማ ጥያቄ አባቶቼ እኔ እናንተን የምጠይቀው ነው።»

ሃጂ አሊ ቃላቱን እንዲተርጉም ጊዜ ሠጠውና ቀጠለ።

«እያንዳንዳችን መናገር የሚገባን በራሣችን የሙያ እውቀት ዙሪያ ያለውን ነው። በበኩሌ እኔ ሐኪም ነኝ። ጓደኛዬም መድሃኒት በመቀመምና በማዘጋጀት ባለሙያ ነው። ከዚህ ውጭ የምናውቀው በሆናችን ታጥቀናቸው ያሉትና አያያዛቸውንም የምናውቅባቸውን ኮራጆዎቻችንን ነው። እፅዋትንና መሣሪያዎቻችንን በተመለከተ፣ አባቶቻችን፣ ደስ ያላችሁን ጠይቁንና በተቻለን መጠን የሚያረኩ መልሶች እንሰጣችኋለን። ነገር ግን አሁን የጠየቃችሁን ጥያቄ በርግጥ እናንተን የመሰለ የመንፈሣዊ ትምህርት ሊቃውንትን የሚመለከት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ለመማር ደግሞ ዝግጁ ነን።»

ጆን ባፕቲስት በክብር ዝቅ በማለት መልሱን አጠናቀቀ። ነጭ ካባውን እንደለበሰ አንድ እጁን በልቡ ላይ አሣርፎ ወደ ራስና እዚያ ወደ ተሰባሰቡት ጓደኞቻቸው ትጥቅ በማስፈታት ታማኝነት መልክ ተመለከታቸው።

በአንድ ገደል ጥግ፣ በሁለቱም ጐኑ ስስ መድረሻ ባለው ጠባብ መንገድ ላይ የሚራመድ መስሎት ውስጡ ተሰቃየ። ልቡ ዘለለች። ቀዝቃዛ ላብ በጀርባው ቁልቁል ወረደ። ይሁንና ይህን ሁሉ ላለማሣየት ራሱን አበረታ።

ረዘም ያለ ፀጥታ ተከተለ። የሚሰማ ድምፅ ቢኖር በግቢው ውስጥ የተነሣው የሴቶችና የወንዶች የተደባለቀ የቅሬታ ድምፅ ብቻ ነበር።

ንጉሱ፣ ምንም ዓይነት ምስጋና ሳያቀርቡላቸው አሰናበቷቸው:: የተናገሩት ቢኖር በሚቀጥለው ዕለት የህክምና ትዕዛዛቸውን እንደሚጠብቁ ብቻ ነበር:: በዙፋኑ አጠገብ ቦታቸውን የያዙት ራስ ዮሐንስ፣ ዛቻ ያለበት በሚመስል አነጋገር፣ መድሃኒቱ መጀመሪያ በሰስት ባሪያዎች ላይ፣ ቀጥሎ በሁለት ባለስልጣኖች ላይ ተሞክሮ እንደሚፈተንና ንጉሰ ነገስቱ ከዚያ በኋላ እንደሚሰጣቸው አክለው ተናገሩ:: በዚህ ሂደት ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ላይ አደጋ ቢከሰት በሁለቱ ባዕዳን ላይ ውጤቱ የከፋ ይሆናል:: በመጨረሻም በከተማውና በገጠሩ እንደልባቸው ለመዘዋወር ነፃ መሆናቸውን ነገሯቸው:: ከሚፈልጉት ማንኛውም ሰው ጋር መነጋገር ይችላሉ:: ነገር ግን የካቶሊክን እምነት የሚሰብክ የሚመስል አንድ ቃል ቢተነፍሱ ፈጣንና ተገቢው ቅጣት ይፈፀምባቸዋል::

እንግዶች ለሁለተኛ ጊዜ ብዙ በመቆማቸው ከደከሙ በኋላ፣ ሲደበደቡ የቆዩ ይመስል ክፉኛ እየተንቀጠቀጡ የስብሰባውን አዳራሽ ለቅቀው ወጡ::

ወደ ሃጅ አሊ የሙስሊም ጓደኛ ቤታቸው በመመለስ ላይ ሳሉ አንድ እንደነገሩ የለበሰ እግረኛ መልዕክተኛ ሲሮጥ ደረሰባቸው:: ሁለቱ ባዕዳን ሣጥኖቻቸውን ቀርቅበው በፈረሶቻቸው ላይ እንዲጭኑና እንዲከተሉት ነገራቸው:: ሃጅ አሊ ብዙውን ነገር ስለዘረፋቸው የመጫን ስራው የሚወስድባቸው ጥቂት ጊዜ ነው:: ከቀሯቸው ጥቂት ቁሣቁሶች ውስጥ ያረጁ የአውሮፓውያን ልብሶቻቸውን፣ አረቡ ሊያነብባቸው የማይችላቸውን መፃሀፍቶቻቸውን፣ የመድሃኒት ሻንጣቸውንና በጨርቅ ውስጥ ሆነው በኮርቻ ስር ያሉትን የሚወዷቸውን ጉራዴዎቻቸውን በጆንያ ውስጥ ከተቱ:: መልዕክተኛው ቀደም ሲል ከነጩበት ጉን በተቃራኒው ባለ ከቤተመንግስቱ ግድግዳ ቀጥሎ በሚገኝ የድንጋይ ቤት አስገባቸው:: ለዘበኛ ተብሎ የተሠራ ቤት ይመስላል:: መግቢያው ወደ አንድ ረዥም የመወጣጫ ደረጃ የሚያመራ ጠባብ የመተላለፊያ ቦታ ነው:: በከባድ ቁልፍ ተቸንክሮ የነበረውን ከባድ መዝጊያ በትግል ከከፈተው በኋላ ይህንኑ መልዕክተኛ ተከትለው ደረጃዎቹን ወጡ:: መጠነኛ ስፋት ያለው ክፍል አሳያቸው:: ወደ ማለዳው ፀሐይ አቅጣጫ በሚከፈት መስኮት ብርሃን ይገባል:: በክፍሉ ውስጥ ሁለት የጠፍር አልጋዎች፣ ሁለት የእንጨት በርጩማዎች፣ አንድ ጠረጴዛና ለጋራ የሚያገለግል መስታወት አለ::

በፖንሴና በጓደኛው አዕምሮ ውስጥ የሚመላለሰው ጥያቄ ግዙፉ ቁልፍ ምን እንደሚሆን ነበር:: ለነርሱው ተሰጥቷቸው ይህ ከእንግዲህ ቤታችን ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸው



ይሆን? መልዕክተኛው ግን ቁልፉን በበሩ ላይ ተወው:: ይህ ሰው አረብኛ አያውቅም ነበርና ከርሱ አንዳችም ነገር ማወቅ አልቻሉም::

ሁለቱ ጓደኞች ብቻቸውን ከቀሩ በኋላ ለረዥም ሰዓታት በየአልጋቸው ላይ በፀጥታ ተጋድመው ቆዩ::

«እንደ ዮናስ በአሳነባሪ ሆድ ውስጥ የሆንክና በህይወት የምትወጣበት ምንም ዕድል እንደሌለህ ታስባለህ?» ሲል ዠረሚ በመጨረሻው ጠየቀው::

«በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ላይ እናተኩር» አለ ጆን ባፕቲስት እየተንጠራራ:: «እስከአሁን ድረስ ጥቂት መሰናክሎችን አልፈናል:: ከእንግዲህ ቀጣዮቹን ማየት ይገባል:: ዛሬ ማታ ለንጉሡ ባሪያ መድሃኒት እናዘጋጅለታለን:: ሃጅ አሊ እንዳረጋገጠልን፣ ንጉሱ ያለባቸው ሕመም ልክ እርሱ ላይ እንዳለው ደዌ ነው:: ከዚያ በኋላ የሚሆነውን እናያለን::»

ይህን ተናግሮ ጆን ባፕቲስት እንቅልፍ ወሰደው:: ሜትር ዠረሚ በደስታ የጓደኛውን ፈለግ ተከተለ::

በሩ ላይ በተፈጠረ አነስተኛ መንኳኳት ነቁ:: በውጭ ያለው የፀሐይ ብርሃን ቀነስ ያለ ሲሆን፣ ሰማያዊ ጥላ ከወደ መንገዱ በኩል እየዘለቀ ነው:: ጊዜው ከቀትር በኋላ ዘግይቶ ነው:: ወደ ክፍላቸው የዘለቀው ወጣት ሰው ሃያ አመት የሚሆነው አጭርና በጣም ቀጭን ነው:: ፊቱ በፈንጣጣ የተላላጠ ስለሆነ ሕመሙ ቀዳውን አደድሮታል:: ፊቱ ሸካራ ሲሆን አፍንጫው በተለይ አጭርና እንደኳስ ክብ ነው:: ጥቋቁር አይኖቹ ብልህነትና ለዛ የተሞሉ ናቸው:: በከንፈሮቹ ላይ ፈገግታ ሲያንዣብብባቸው አጠቃላይ እንቅስቃሴው ለዛ ያለው ነው:: እነዚህ ምልክቶች ከጥቁርና ከርዳዳው ፀጉሩ ጋር ሲታይ፣ ለጆን ባፕቲስት እንዳልታደለ ወንድሙ ያህል ነው::

«ስሜ ዲሚጥሮስ ነው» አለ በአረብኛ

አረብኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ መናገሩ በግልፅ ያስታውቃል:: አፍ የፈታበትን ግሪክኛንም እንደሚናገር ነገራቸው:: እነርሱ ግን ይህን ቋንቋ አያውቁትም:: ጣሊያንኛን ግን

ይህ ሲነገር፣ ጆን ባፕቲስትና ጓደኛው ይህ በነፋስ የሚውለበለብ አስደንጋጭና በሞራልም ረገድ መጥፎ የሆነውን ቆዳ ሲመለከቱ አጥወለወላቸው። ከሰልፉ በስተመጨረሻ ያሉት ፊገግ የሚሉ ሴቶችና ሕፃናት ሲሆኑ በፀጥታ ያጨበጭባሉ።

ሦስቱ ሰዎች ጉዟቸውን ቀጠሉ። ሁለቱ ባዕዳን ባዩት ነገር ክፉኛ እንደሚጉዱ ዲሚጥሮስ ይሰማዋል።

«አትበሳጉ» አላቸው። «የደረሳችሁት ድል አድራጊ ወታደራዊ ሠራዊት ከዘመቻው በተመለሠበት መጨረሻ ላይ ነው። እስረኞቹ እየተቀጡ፣ ከሃዲዎች እየተጋለጡ፣ ጀግኖች እየተሸለሙ ነው። ሕይወት ሁል ጊዜም አስደሳች አይደለም»

«በመስማታችን ደስ ይለናል።» አለ ሜትር ዠረሚ «የኛም ቆዳ በጉዳናዎች መሃል በሰልፍ የሚያልፍበት ጊዜ እስኪመጣ ለህዝቡ የምንሠጠው አዝናኝ ነገር እምብዛም አይኖረንም። ይህን በማወቃችን እንፅናናለን።»

«የናንተ ቆዳ በጉዳናዎች መሃል መቼም በሰልፍ አያልፍም» አለ ዲሚጥሮስ በሳቅ እየተንከተከተ። «ይህ ሙሉ በሙሉ ሊሆን የማይችል ነገር ነው።»

«መድሃኒታችን ውጤት ባይሰጥስ ምን ይሆናል?» ሲል ፖንስ ጠየቀ

«ያን የመሰለ ቅጣት በናንተ ላይ አይፈፀምም። እናንተ የንጉሡ ነገሥቱ እንግዶች ናችሁ»

«ጂስዊቶችስ? የንጉሡ ነገስቱ እንግዶች አልነበሩም እንዴ?» አለ ሜትር ዠረሚ

«ኦ! ቆይ እስኪ» አለ ዲሚጥሮስ አመልካች ጣቱን አውጥቶ «እኔ እስከማውቀው ድረስ ጂስዊቶች ከነ ህይወታቸው ቆዳቸው አልተገፈፈም። እነርሱን በተመለከተ ሕጉ በጥብቅ ነው የተፈፀመው»

«ማለት?»



«ማለትማ በድንጋይ ተወግረው ተገደሉ። ወደታች ተመልሰን ስንሄድ፣ በአደባባዩ መካከል ላይ ሁለት የድንጋይ ክምሮችን ታያላችሁ። የመጨረሻዎቹ በሞት የተቀጡት ጂስዊቶች የተቀበሩበት እዚሁ ነው። እነዚህን የድንጋይ ቁልሎች ደግሞ ማንም እንዲነካቸው አይፈቀድለትም»

«ስለዚህ እኛም የመገፈፍ አደጋ ውስጥ ነን ማለት ነው?» አለ ፖንሴ፣ ከዚህ ቀን፣ በግልፅና በትህትና ከሚናገር ልጅ ጋር መጫዋወቱ ደስታን እየፈጠረለት።

«ኑ፣ ኑ፣ እናንተ ምንም አይነት አደጋ ውስጥ አይደላችሁም» አለ ዲሚጥሮስ። ሁለቱንም ክንዶቻቸውን ይዞ፣ ከርሱ ጉን እንዲራመዱ እያደረጋቸው። «ንጉሡ ነገስቱ ይጠብቋችኋል። እኔ ደግሞ አሽከራቸው ነኝ። ከዚህ በኋላ አዲስ ርዕስ ላይ እንነጋገራለን። ይህች አገር ሌሎች ብዙ ደስታዎችን እንደምትሰጣችሁ ታያላችሁ»

ፖንሴና ጓደኛው፣ ጐንደር በኖሩበት ጊዜ የንጉሡን ምስጢራዊ ጠባቂ፣ የርሱንም ጥላ ከለላ መለየት ቻሉ። ከዲሚጥሮስ በተጨማሪ በጣም ጠንቃቃና ማንነታቸው ተለይቶ የማይታወቁ ምስክሮች፣በሚጓዙባቸው ጉዳናዎች፣ ምግብ በሚበሉባቸው ቤቶች ፣ እፅዋት በሚሰበስቡባቸው የባላገር አካባቢዎች ሁሉ ከጐናቸው ይኖራሉ። የማያስቀይመውን የገበሬዎች፣ የወሮበሎችን ወይም የነጋዴዎችን ሁኔታ በማየት ንጉሡ በፈረንሣውያን ላይ ያላቸውን ሃያልነት ይቀበላሉ።

እነዚህ ተጓዦች በዋናው ከተማ ውስጥ የሰነበቱባቸው ሣምንታት፣ የየዕለቱን ሕይወት ትዕይንት የአይን ምስክር ሆነው እንዲያረጋግጡ ዕድሉን ሰጥቷቸዋል። የአገሬውን እንግዳ ባህል ተመልክተዋል። ምንም እንኳ በዚህኛው መስመር ቁጥብ መሆናቸው መጥፎ ስም ቢያስጣቸውም፣ ጥቂት የሲጋ ፈቃድ ግንኙነትንም አድርገዋል። ከዚህም ባሻገር ብዙ ቤተክርስቲያናትን ጐብኝተዋል። አገራዊውን ባህላዊ የስዕል ቅብ ተመልክተዋል፤ በመጀመሪያ ላይ አልጥማቸው ያላቸውን የአገሪቱን ሙዚቃ አድንቀዋል። በተለይም ሙዚቃው በውዝዋዜ ታጅቦ ትዕይንትና ድጋፍ ሲኖረው ውበቱን በተሻለ መረዳት ችለዋል።

ብዙ ነገሮች ከምን እንደተሠሩ፣ ከእንጨት ይሁን ከመዳብ ወይም ከቀርከሃ ፈጥነው ለማወቅ ቻሉ። የእጅ ስራዎቻቸው ዓይነት፣ መለያየትና መብዛት፣ በንጉሠ ነገስቱ ግዛት ውስጥ ብዙ የተለያዩ ባህሎች አብረው መኖራቸውን ያንፀባርቁላቸዋል። ፖንሴ፣የማስታወሻ ደብተሩን በሙንጭርጭር ፅሁፍ ሞላው። ለዘዴኛው ዲሚጥሮስ ምስጋና ይግባውና ሌላም ገዛ። አቢሲኒያውያን ወረቀት ስለማያውቁ የሚፅፉት በብራና ላይ ነው።

ጥርጣሬ ላለመቀስቀስ፣ እንደመጀመሪያው ቶሎ ቶሎ ባይሆንም ንጉሡን ማየታቸውን ቀጠሉ። የሕመማቸውን ሣይሆን የምልክቱን ቀስ በቀስ መክሰምና መሰወጥ መዘገብ ቻሉ። ንጉሡ ስለህመማቸው መብርታት ወይም መሻል ፈፅሞ ደግመው አልጠየቋቸውም። በሌላ በኩል ለቁጥር የሚያታክቱ ስለ ባህል፣ ስለሳይንስና ስለምዕራባውያን አገሮች ፖለቲካ ይጠይቋቸው ነበር።

ንጉሡ እንደገና ለወታደራዊ ዘመቻ እንደሚንቀሣቀሱ ዲሚጥሮስ የሚያረዳቸው ዕለት ደረሰ። የሲናር ንጉስ፣ በድንበር አካባቢ የተፈጠረውን አነስተኛ ግጭት ሰበብ በማድረግ



በአቢሲኒያ ላይ ጦርነት አውጇል። ጐንደር ከመሰንበት ይልቅ ንጉሡን ተከትሎ መሄዱ አደጋው አነስተኛ እንደሚሆን ወጣቱ ግሪካዊ ነገራቸው። የንጉሡን ድጋፍ ለማግኘት በአደገኛ ሁኔታና በብልጣብልጥ አካሄድ የመድረሳቸው ጭምጭምታ በሚናፈስባቸው በሁለቱ ባዕዳን ላይ፣ የቤተመንግስቱ ባለስልጣናት በሚያገኙት ተነፃፃሪ ነፃነት ሌላ ሴራ ለመጠንሰስና ለመፈልፈል ዕድል ይኖራቸው ይሆናል። የፈረንሣውያን ሐኪሞችን ባለስልጣናቱ በይፋ ያስተላለፉላቸውን መመሪያ በመጣስ በአደገኛ ሁኔታ ወደ ንጉሡ ቀርበዋል። ያዘጋጁላቸውንም መድሀኒት የወሰዱና የዳኑ በማስመሰል በመግለፅ፣ ሕመማቸው እንደተሻላቸውና በመጨረሻም ንጉሡ መዳናቸውን ሁሉም እንዲያውቁት በማድረግ አስፀኑ። ንጉሡም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ብዙ ስጦታዎች ለሁለቱ ባዕዳን ሸለሟቸው። ከዚህም ባሻገር፣ በከተማዋ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ሕሙማንም ገንዘብ ያገኙ ነበር። በጊዜ ብዛት ጆን ባፕቲስትና ሸሪኩ ጓደኛው ከሁሉም ዓይነት ደረጃ ከሚመጡ ሰዎች ጋር እንዲገናኙ ጥሪ ይጐርፍላቸው ጀመር። ይልቁንም ንግስቲቱ የሚማረሩበትን ህመማቸውን እንዲያክሙ በይፋ በመጠራታቸውና በተሣካ ሁኔታ በመፈፀማቸው ካህናቱ በርግጥ ተቆጥተዋል።

ንጉሡን በወታደራዊ ዘመቻቸው ላይ የማጀቡ ጥያቄ ሲመጣ፣ እውነቱ መገለፅ ያለበት ጊዜ መድረሱን ጆን ባፕቲስት ወሰነ። አቢሲኒያ ውስጥ መቆየቱ ምንም ያህል ደስታ ይሰጠው እንጂ፣ የጉዞው እውነተኛ ምክንያትና እርሱም በይሁንታ ለመቀበል የተገደደበትን አይዘነጋውም። አንድ የአቢሲኒያን ኤምባሲ ይዞ መመለስ ይኖርበታል።

ኤምባሲ ይዞ የመመለስ እድሉ ደግሞ የተረጋገጠ አይደለም። ንጉሡ፣ ጀስዊቶችንና ምዕራባውያን ሃይሎችን ያላመኑበትን ምክንያት ፈረንሣውያኑ ተገንዝበዋል። ንጉሠ ነገስቱም አገራቸው በሯን የምትከፍትበት ጊዜ ገና መሆኑን ነግረዋቸዋል።

የኤምባሲ ሃሣብ ጉዳይ የፖለቲካ መሰናክል ቢሆንም፣ ሌላ የግል የሆነ ችግርም አለ። እስከ አሁን ድረስ ፈረንሣውያኑ፣ ንጉሠ ነገስቱ ዘንድ ለመድረስ የነበራቸውን የረዥምም ጊዜ ዕቅድ ጥቅም ብቻ ነው ያገኙትና አሁን ግን የዚህን ዕቅድ ጉዳትም ማሸተት ጀምረዋል። የንጉሡን አመኔታና ወዳጅነት ለማግኘት ያደረጉት ጥረት፣ እነርሱ ከመጀመሪያውኑ ተስፋ ካደረጉት ይልቅ በጣም ተሳክቶላቸዋል። ከሁሉም የበላይ የሆኑት ንጉሠ ነገስት ወድደዋቸዋል። ከነርሱ ጋር በመተማመንና በፍቅር ተሣስረዋል። ለዚህ ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የማያጨቃጭቅ ማረጋገጫ ሰጥተዋል። እነርሱ ያከናወኑት ጨዋታ ግን አደጋ

ከመቸውም ጊዜ በበለጠ አሁን በጣም ጠቃሚ ነው። ስለዚህ ለግብፅ ፓሻ በገባሁለት ቃል መሠረት እንድትሄዱ ልፈቅድላችሁ እችላለሁ።»

« ለግርማዊነትዎ እጅግ ትልቅ ውለታ አለብን።»

«እኔም አንድ ተመሣሣይ ጥያቄ እንዳቀርብላችሁ ፍቀዱልኝ» አሉ ንጉሡ

ፖንሴ ጭንቀላቱን ዝቅ አደረገ። የበላይ ገዥው ፍላጐታቸውን በሃይል ለመጫን ባይፈልጉም አግባብተው ሊያቆዩዋቸው የመሞከር ጥረታቸውን ግን አልተዉትም።

«ምንም አይነት ፍቅር ሊነፍጋችሁ ከማይችለው ከአንድ ክርስቲያናዊ ልዑል ይልቅ ይህን አንዳችም ምስጋና ምን ጊዜም አሣይቷችሁ ለማያውቀው ለዚህ ቱርካዊ ለማገልገል ለምን መረጣችሁ?»

«ግርማዊ ሆይ የምንመለሰው ለካይሮው ፓሻ ስንል አይደለም» አለ ፖንሴ።

«ታዲያ ለምንድነው?»

ወጣቱ ሃኪም ወዲያውኑ አሰበ። እንግዲህ ተቃርበናል። ቡናውን ፉት አለና ቀጠለ።

«እንደሚያውቁት ሜትር ዠረሚና እኔ ሸሪኮች ነን። እሱ እኔን ይከተለኛል። እርግጡን ግን ወደቤት መሄድ የምፈልገው እኔ ነኝ።

«እንግዲያው ደህና፣ እኔም ጥያቄውን ያቀረብኩት ላንተ ለጆን ባፕቲስት ነው» አሉ ንጉሡ

«ይኸውልዎ ግርማዊ ሆይ፣ ከአንዲት ወጣት ሴት ጋር ፍቅር ይዞኛል» አለ ፖንሴ።

ንጉሡ ሣቁ። እንዲህ ሲስቁ ሲያዩ የመጀመሪያቸው ነበር። ድምፅ አውጥተው በጣም ሲስቁ፣ ጭንቅላታቸውን ወደ ኋላ ጣል አድርገው ነው። ጭውውቱ እንደገና እንዲቀጥል ዲሚጥሮስ በአክብሮት ጠበቀ።

«ደህና» አሉ ከሁሉም የበላይ የሆኑት ንጉስ። «በኔ ቤተመንግስት ውስጥ ሙሉ በሙሉ በወርቅ በተሸፈነ መኖሪያ ቤት ለመኖር እጅግ እንደምትደሰት አስባለሁ። እንደሠማሁት ካይሮ



በጣም ይሞቃል። ሴቶች ደግሞ የኛን ያየር ጠባይ ይመርጣሉ። ሚስትህ ጐንደር መጥታ አብራህ እንድትኖር አድርግ»

«ሚስቴ አይደለችም።» አለ ጆን ባፕቲስት

«እዚሁ ልታገባት ትችላለህ»

«እውነቱን ለመናገር፣ ግርማዊ ሆይ . . . እዚህ ደረጃም ላይ ገና አልደረስንም።»

ንጉሡ፣ ያን አስደናቂ አሣሣቃቸውን እንደገና ሣቁ።

«ታዲያ ምን ደረጃ ላይ ነው የደረስከው?»

«ግርማዊ ሆይ፣ ይህች ወጣት የማህበረሰብ ደረጃዋ ከኔ እጅግ ከፍ ያለ ነው። አባቷ፣ በመንግስታችን ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ አላቸው፣ እኔና እርስዋ እንፋቀራለን»

ይህን እንደተናገረ ምናልባት ዕድሉን ሊሞክር እንዳሰበ መሰሎት ጆን ባፕቲስት ለአጭር ጊዜ መጥፎ ስሜት ተሠማው። በአፍቃሪ ላይ በሚነገር አጉል እምነት የተነሣ፣ በዚህ በተለየ ነጥብ ላይ ስለ ዕጣ ፈንታ ከሌላው ሁሉ ነገር በበለጠ ፈራ።

«አሁንም ቢሆን ቤተሰቦችዋን ማሳመን መቻል ይኖርብኛል። ይህ ደግሞ ቀላል የሚሆን አይደለም።»

«እንግዲያው በአንድ ታላቅ ንጉስ አጠገብ እንደምትኖርና አንተም ከከፍተኛ መኮንኖቹ አንዱ እንደምትሆን ንገራቸው።»

«አቤት! ግርማዊ ሆይ፣ እርስዎ ሰዎችን በተሻለ ያውቋቸዋል። ሰዎች አርቀው አያዩም። ምንም ነገር ይሁን በቀጥታ በአይናቸው ስር ካልሆነ የለም የሚሉ ናቸው። ለግርማዊነትዎ የማገልገል ሹመት፣ የብዙ ማዕረጐች ክብረት እንዳለውና የታላላቅ ቤተሰቦቻችንን ልጆች በኩራት እንደሚሞላቸው በሚገባና ሙሉ በሙሉ አውቃለሁ። ነገር ግን ያፈቀርኳትን ልጅ አባት ለማሣመን ይህ በቂ አይሆንም»

ዲሚጥሮስ ተርጐሞ እስኪጨርስ ለጥቂት ጊዜ አቋረጠ። ከዚያም ድምፁን ከፍ አድርጐና እያንዳንዱ ሃሣብ በአምሮው ውስጥ እንዳመጣለት አስቦ እንዲነግረው ጭንቅላቱን ግራና ቀኝ በማወዛወዝ ቀጠለ።

«ግርማዊነትዎ እኔን ለመርዳት የሚቻለውን ሁሉ እያደረገልኝ መሆኑ ይታየኛል። ለዚህም ባለውለታ ነኝ። አንደ እውነቱ ሌላም ነገር አለ . . .»

«ምንድን ነው? ተናገረው»

«ብናገረው ድፍረት ይሆንብኛል። ምክንያቱም አስተሣሰቦቼ እርስዎ አጥብቀው ከሚይዙት የፀና እምነትዎ ጋር በተቃራኒው የሚሄድ ነው»

«ቀጥል! ተናገር። የምከለክልህ ከሆነ፣ ቢያንስ ከሁለት አንዳችን፣ መሞከር ሲገባን ያላደረግነው አለን ብለን እንፀፀታለን።»

«እንግዲያው እንዲህ ነው» አለ ጆን ባፐቲስት በመጨረሻ። ልክ አንድ ሠው ጭንቱን ከትከሻው ላይ አንቃንቆ እንደሚጥለው አይነት ቃላቱ በጥድፊያ ይወጡ ጀመር። «የፍቅረኛዬ አባት ዲፐሎማት ናቸው። ስርሣቸው ደረጃ ተመሣሣይ በሆነ ማህበረሰባዊ ቦታ ለመድረስ ብችል በደስታ ይቀበሉኛል። እኩል መሆኔንም ያረጋግጣሉ። ወይም የተመሣሣይ አለም አባል መሆኔን ይቀበላሉ። ይህ ሊሆን የሚችለው ግርማዊነትዎ እኔ በአቢሲኒያ የፈረንሣይ ንጉስ፣ የግርማዊ ሉዊስ አስራ አራተኛ፣ ቋሚ አምባሣደር፣ እንድሆን እርስዎ ሃሣብ ቢያቀርቡ ነው። ከዚያ በኋላ ወደዚህ ልመለስና የደረጃዬን አንፀባራቂነት ለማፈቅራት ሴት አረጋግጣላታለሁ። ግርማዊነትዎ በዙፋንዎ አጠገብ የሚሰጡኝን ደረጃ የፍቅረኛዬ አባት ሊረዱት የሚችሉት ካልሆነ ዝቅ አድርገው ይገምቱታል ብዬ እፈራለሁ»

«ኤምባሲ ነው?» አሉ ንጉሡ

በዚያን ቅፅበት፣ በንጉሣዊ ድንኳን ስር የገባው ድንገተኛ ነፋስ፣ የአሸዋ አውሎ ነፋስ ከወለል ላይ በማስነሣቱ ውይይቱ ቆም አለ።

«አየህ፣ ይህ የኛ ባህል አይደለም» አሉ የሁሉም የበላይ «ለጐረቤቶቻችን መንገር የሚገባን ጉዳይ ካለ በተቻለ መጠን በነጋዴዎች፣ ቅዱሣን ቦታዎችን ለመሣለም በሚጓዙ



ሰዎችና አንዳንዴም በለማኞች ሣይቀር በቀጥታ መልዕክቶቻችንን እንልካለን። የየመንግስታቸው ይፋ ባለስልጣኖች ተደርገው ሰዎች ሲላኩልን፣ ለምሣሌ በቀድሞ ጊዜ ከፖርቱጋል እንደተላኩት አይነት እብሪታቸው ደማችንን ያፈላውና አገራችንን ለቅቀው ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ እንፈቅድላቸውም ነበር»

«አውቃለሁ» አለ ፖንሴ

ንጉሡ በጠረጴዛቸው ዙሪያ እጃቸውን በሸካራው የድንኳን ጨርቅ ላይ ምንም እንደማያስብ ወይም እንደማያዳምጥ ሰው አሣርፈው ወዲያና ወዲህ አሉ።

«ከዚህም በተጨማሪ፣ እናንተ ጀስዊቶች የምትሏቸው ካህናትና ሌሎችም እንዲሁ አሉ። የአረቦችን ልብስ እየለበሱ በድንበሮቻችን አካባቢ በማንገዋበብ፣ ወደ አገራችን ለመግባት አመቺ የሚሆናቸውን አነስተኛ ሰበብ ሁሉ አፈፍ ያደርጋሉ። ሕፃን እያለሁ፣ ልክ እኔ፣ አንተ እንድትመጣልኝ እንደላክሁት፣ አባቴም፣ ከካይሮ ሃኪም እንዲመጣለት ላከ። ሁለት መነኮሣት መጡ። ጥቂት ቢጠራጠርም፣ በወዳጃዊ ሁኔታ ተቀብሎ አስተናገዳቸውና ሐኪሙ ማንኛቸው እንደሆነ ጠየቃቸው። ዶክተሩ ከነሱ ጋር ጉዞ ሊጀምር እንዳልቻለና እነርሱ ግን ቀድመው መምጣታቸውን በጥሞና ተናገሩ።

«እና ምን ሆኑ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀ

«የፈረንሣይ ካህናት ተመልሰው መምጣታቸውን ህዝቡ ሲሰማ፣ መሠብሠብ ጀመረ። የኛ ካህናትና መሣፍንት ደግሞ፣ ከዚህ በፊት እንዳጋጠመን መጥፎ ዕድል፣ ንጉሡ ሃይማኖቱን ይለውጥ ይሆናል በሚል ፍርሃት፣ በተገለለ ቦታ አስቀመጡት። በማንኛውም ሰዓት የርስበርስ ጦርነት ሊፈነዳ የሚያሰጋ ነገር ነበር። ንጉሡ አባቴ! ፈፅሞ አላመነታም። ሁለቱንም እንግዶች በቁጣ ለወጣው ሕዝብ አሣልፎ ሰጣቸውና በቤተመንግስቱ ፊት ለፊት በድንጋይ ተወግረው ሞቱ። ይህን ያነሣሁልህ፣ እኛ ባንፈልጋቸውም እንኳ እዚህች አገር ለመግባት ምንም ነገር እንዲያቆማቸው የማይፈልጉ እክራሪዎችን ኤምባሲው ከመነሻው ይዞ ቢመጣ የሚል ስጋት መኖሩን ልገልፅልህ ነው።»

«ትክክል ነው» አለ ጆን ባፕቲስት፣ እንደተከዘ ቆይቶ። ወዲያውኑ የመጣለትን ሃሣብ ለመናገር እንደከጀለ ሆኖ ቀጠለ። «ግርማዊነትዎ በሚገባ የሚያውቁትን፣ ለካህናቱ ያለዎትን ጥላቻ የሚያውቅና እነርሱን ወደዚህች አገር ፈፅሞ ላለማምጣት ቃል የሚገባልዎትን አምባሣደር ይሹሙ። ይህ አሠራር ጉዳዩን ሁሉ ፍፁም በአዲስና ጠንካራ መሠረት ላይ ይጀምረዋል። እኔ እንደማስበው፣ ግርማዊነትዎ በእውነት የሚያስፈራዎ እምብዛም ነው። በተቃራኒው ግን፣ በአገርዎ ያለውን ሁኔታ ከሚያውቁት የፈረንሣይ ንጉስ መልዕክተኛ መቀበል፣ ጉን ለጉንም የጀስዊቶችን የብልጣብልጥ እንቅስቃሴ ማወቅዎና ቀሣውስቱ የሚፈፅሙትን የመጀመሪያ አዲስ የዘመቻ እንቅስቃሴ ምልክት ለሁሉም የበላይ ንጉሳችን ሪፖርት እንዲያደርጉ ይረዳዎታል። ንጉሰ ነገስት ሉዊስ አስራ አራተኛ፣ ከጳጳሱ ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ስላላቸው የሃይማኖታቸው ማህበር ያለውን ከፍተኛ ጉጉት እንዲገታው ሊጠይቋቸው ይችላሉ። ብዙ ነገሮች የሚሆኑት እርስዎና አገርዎ በኛ አገር በሚገባ አለመታወቃችሁ ነው። ፕሮፖጋንዳ በማይምነት ውስጥ ስር ይሰድዳል። ግልፅ በመሆኔ ይቅር ይበሉኝ። ስናገረው ያሳፍረኛል እንጅ፣ ጀስዊቶች፣ ይህች አገር በማይምነትና በጭካኔ የተሞላች የአረማውያን ምሣሌ ነች እያሉ መናገር ችለዋል። ይህ ደግሞ፣ የእምነትን ብርሃን እንዲያስገቡ ለማስቻል ለነርሱ ክብርና ዝና ይሠጣቸውና ባለውለታ ያደርጋቸዋል። እኔ ያለውን እውነተኛ ሁኔታ ለንጉሣችን በትክክል ማስረዳት ብችል እርሣቸው ይረዱኛል። በሁለቱም አቅጣጫ ልረዳዎት እችላለሁ። በጋራ መከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ባላቸው፣ አንዱ በምዕራብ ሌላው በምስራቅ በሚገኙ ሁለት የክርስቲያን ንጉሦች መካከል እንዲኖር ልረዳዎት እችላለሁ። ይህ አካሄድ የንጉሠ ነገስት ግዛትዎን ሰላም በማናጋት ስልጣንና ዘለዓለማዊውን ነፍስ ለመንጠቅ የሚጥሩትን የሰርጎገቦችን ምንጭ ከመነሻው ይገድበዋል።»

ቀስ በቀስ እያደገና እየጋለ፣ ሌሎችን ሲያሄስ የቆየበት ረዥምና ቁጣ የተሞላበት ንግግሩ ሲያበቃ፣ ድንገተኛ የሆነ መደነቅና የመውደድ ስሜት ስላሳደረበት፣ ጆን ባፕቲስት ዓይኖቹን በንጉሡ ላይ ተከለ። ንጉሡ መንቀሣቀስ የማይችሉ መስለው ለረዥም ጊዜ ቆዩ። ከዚያም ዘበኛውን ጠሩት። በአንድ እጁ አለንጋ፣ በቀበቶው ላይ ጉራዴ የታጠቀ ረዥምና በጣም ቀጭን ወጣት መጣ።

«ፈጥነህ ሰው ወደ ከተማ ላክ። ሙራድ እዚህ እንዲመጣ አድርግ» አሉት።



# 14

ሰው ምንም ያህል ዋሾ ቢሆን፣ ሌባም ቢሆን፣ ቃሉን የማይጠብቅና ከሃዲም ቢሆን እንኳ፣ እድሜውን በሰላም ለመጨረስና ለተባረከ ረዥም ዘመን የሚበቃው ጠንካራ እምነት ሲኖረው ብቻ ነው። ቅንጣት ታህል እምነት ያለው፣ የዕምነት ፅናቱ ፍፁም የሆነ፣ በሆነ ባልሆነው ጉዳይ ዕምነቱ የማይዛባበት ሰው፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠበቃል። ሙራድ እንዲያ ያለ ሰው ነው። ይህ አርመናዊ፣ በካውካሰስ ሕዝቦች ላይ ብቻ የሚታየውን ዓይነት የማይገመት ዕድሜ ኖሯል። የካውካስስ ሕዝቦች በሂሳብ ጉብዞች ቢሆኑም፣ የዕድሜ ጉዳይ ሲነሣ ስለሚጃጁ ይምታታባቸውና ፣ የታላላቆቻቸውን ዘመን እንኳ መናገር ያቅታቸዋል። የሙራድ ረዥም እድሜ በሁለት ክፍሎች ብቻ ሊከፈል ይችላል። የመጀመሪያው የልጅነት ጊዜው ነው። በሻን ሐይቅ አጠገብ በምትገኝ መንደር ውስጥ የሕፃንነት ዘመኑን ያሣለፈው ሙራድ፣ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከነጋዴ አባቱ ጋር ነው። ከአስራ አምስት አመቱ ጀምሮ፣ ባልተቋረጠና ባልተናጋ አራት የአቢሲኒያ ነገስታት ዘመን አገልግሏል። የኢትዮጵያን የቅርብ ጊዜ ታሪክ በሙሉ በዓይኑ ያየ ሰው ነው። የጀስዊቶችን ተልዕኮ፣ ከአገር መባረራቸውን፣ ከዚያም የተከተለውን የስርዓት አልበኝነት ጊዜ፣ የፋሲለደስ ወደስልጣን ዳግም መመለስና መንግስት መቆጣጠር፣ የልጅ ልጁ እያሉ ያከናወናቸውን ሁሉ አይቷል። ቋንቋዎችን በማወቁ፣ በዲፕሎማሲ ጥበቡ፣ ሰዎችን ፈጥኖ በመፈረጅ ችሎታው፣ በተለይም ወደህንድና ባሲ ወደሚገኘው የደች ተጠሪ፣ የነገስታቱ ተመራጭ የመንግስት መልዕክተኛ እንዲሆን አድርጎታል። ለረዥም ጊዜ በቆየው ዝናው ሳቢያ፣ አሁን በቅርቡ ከተመለሰበት ተልዕኮ ባታቢያውያን ስለአድናቆታቸው የሰጡትን ብዙ የነሐስ ደወል ይዞ መጥቷል።

ጆን ባፕቲስት፣ ጐንደር ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ሙራድን ብዙ ጊዜ አግኝቶታል። በመጀመሪያ እንደተገናኙ ሙራድን ዕድሜው መከላከያ ያልሆነለትን ሕመም አክሞለታል። ነገር ግን በዕድሜው ምክንያት እንኳ ሊደክም ባልቻለው የፍትወት ብርታቱ ይህ ሕመም እርሱ እንዳለው «ለሃያ አራትኛ ጊዜ» ይዞታል። የፖንሴ ሕክምና ውጤታማ ነበር። ሽማግሌው፣ ሃያ አምስተኛውን የመለከፍ ዕጣ ለመቀበል፣ ከዕለታት አንድ ምሽት ላይ አንዲት ያለተዳረች ውብ ድንግል ወጣት ሴት አስከትሎ ሲንቀሳቀስ ድንገተኛ በሆነ የአንጐል ውስጥ ደም መፍሰስ ግማሽ ሰውነቱን በድን አደረገበት። ጆን ባፕቲስት ሳደረገለት እንክብካቤና ጥንቃቄ ምስጋና ይግባውና የተጐዳው ጐኑ ቀስ በቀስ ወደ ሕይወት ተመለሰለት። ሆኖም ግን፣ አንዱ እጁ አሁንም

ሲሰንፍበት ከንፈሮቹም የወደቁ ናቸው፡፡ አዕምሮው ግን ጉዳት አላገኘውም፡፡ ንጉሡ የራሣቸውን አስተያየት ሁልጊዜም ያለአድልዎ በማድነቅ በሚመለከተው ሰው ሃሣብ ላይ መጨመራቸው ወጣቱን ሃኪም ፖንሴን እፎይ አሰኘው፡፡

ሽማግሌው ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ደረሠ፡፡ ሲያዩት እንቅልፉን ሳይጨርስ አስቀድሞ እንደተነሣ ሰው ቅር መሠኘትና የመበሳጨት መልክ ይታይበታል፡፡ ሙራድ ትንሽ እንደሚተኛና ለዚያውም ጥሩ እንቅልፍ እንደማይወስደው፣ አለመደሰቱን የሚያሣየው መቃጣትም ለማስመሰል እንደሆነ ጆን ባፕቲስት አውቋል፡፡ ይህ ገፅታው፣ ገና ምክክር በሚደረግበት ጉዳይ ላይ የሽማግሌውን ዕርካታ የሚደብቅለት ዘዴ ነው፡፡ ሽማግሌው፣ እታላይ ነጋዴ ስለሆነ፣ ይህ የቅሬታና የብስጭት መልክ ለድካሙ፣ ለጥረቱና ለሚከፍለው መስዋዕትነት የሚጠይቀውን ዋጋና የሚጠብቀውን ማካካሻ ከፍ ያደርግለታል፡፡

ሙራድ እንደመጣ፣ ንጉሡ፣ የጆን ባፕቲስትን የኤምባሲ ስራ ሙሉ በሙሉና በቀላሉ እንዲገነዘበው አደረጉ፡፡ በርግጥ የፍቅርን ጉዳይ አላነሱም፡፡ ይህን አስቸኳይ ጉዳይ ለመቀበልና ለመፈፀም ያለውን ዝግጁነትም ጠየቁት፡፡

ሽማግሌው፣ በክፈል የንጉሡ ነገስቱ የአደን እቃ በሆነውና አንፀባራቂ ሱል ከተለበጠ ወንበር ላይ ተቀምጦ አዳመጠ፡፡ አቀማመጡ በጉን ሆኖ፣ ክርኑ ላይ ተደግፎ፣ አይኖቹን በከፊል ጨፍኖ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ከታችኛው ቅንድቡ በስተጀርባ ባሉት የነጡ አይኖቹ አጮልቆ ሲመለከት፣ በራሱና በንጉሡ መካከል ልዩ ንቃት ኖሯቸው፣ ወደ ኋላና ወደፊት እንዲንከባለሉ እያደረገ መሆኑን ጆን ባፕቲስት ተሰማው፡፡ ወጣቱ ሰው ግን፣ ንጉሡ እየገለፁት ያሉት ጉዳይ አንዳችም ማስመሠል የሌለበት እጅግ ከፍተኛና ጠቃሚ ጉዳያቸው መሆኑን ለመግለፅ ተቁነጠነጠ፡፡ የንጉሡ ንግግር ቀዝቀዝ እያለ ሲመጣ፣ ሙራድ በተቆራረጠ የሕመም ስሜት ድምፅ ተናገረ፡፡

«ግርማዊ ሆይ! ይህ ድንቅ ሃሣብ ነው፡፡ ነገር ግን ሄሮደቱስ እንደተናገረው የማሰንቆ መምቻ እንደተጠቃሚው ነው፡፡ ሲያስፈልግ የሙዚቃ መሣሪያ ይሆናል፡፡ አለበለዚያ የጦር መሣሪያ ይሆናል፡፡ በተመሣሣይ መልክ ይህ እጅግ ታላቅ የሆነ አዲስና አስቸጋሪ እቅድዎ በአተገባበሩ ላይ ተመስርቶ በጭራሽ የተለየ ውጤት ያስገኝ ይሆናል፡፡»

ይህ የሙራድ የተለመደ የአነጋገር ስልት ነው፡፡ አንድ ጦረኛ ሊመታው የሚፈልገውን ሰው፣ ከጋሻው በስተጀርባ ራሱን ደብቆ እንደሚቀርብ ሁሉ፣ ሙራድም እውነት ይሁን የፈጠራ



የግሪክ ፈላስፎችን ምሣሌ እንደሸፋን ሳይጠቅስ የራሱን አስተያየት ጨርሶ ሰጥቶ አያውቅም፡፡ ንጉሱ ቀሪውን ለመስማት ጠበቁ፡፡

«በመጀመሪያ» አለ ሙራድ፣ ፍፁም በደከመ አኳኋን፣ «ግርማዊነትዎ በፅሁፍ አንዳችም ነገር ማስፈር የለብዎትም፡፡ በምዕራባውያን ዋና ከተማና በዚህ መካከል ያለው መንገድ ረዥም ነው፡፡ ደብዳቤዎ ባልሆነ ሰው እጅ ወድቆ ያለአግባብ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ዕድልም በጣም ሰፊ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ እዚሁ አገር ውስጥ፣ እርስዎ ከፈረንሣይ ንጉስ ጋር ኤምባሲ መጠየቅዎን ቀሣውስቱ ቢያውቁ፣ ሊፈጥሩ የሚችሉት ትልቅ ችግር ይኖራል፡፡ ወይም ደግሞ በጉዞው ላይ ደብዳቤው ቢጠፋና በማይገባው ሰው እጅ ቢወድቅ፣ ቱርኮች በርስዎ ሃሣብ ላይ መጠንቀቅ ይጀምራሉ፡፡ ሰር ፖንሴም፣ ርስዎ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑበት ፍጡርዎ ተደርጐ ይገለፃል፡፡ በመጨረሻም መታሰብ ያለበት የፈረንሣይ ቤተመንግስት አለ፡፡ ጀስዊቶችን፣ ብልጣብልጥ ክርክራቸውን፣ አንድን ሰው እውነት ያልሆነውን ነገር እውነት ነው ብሎ እንዲቀበል የማድረግ ችሎታቸውን፣ ቅንነት የጐደለውንና ሸፍጥ የተሞላውን አስተሣሰባቸውንም እርስዎም ያውቃሉ፡፡ በርስዎ ግምት ፍፁም ጉዳት የላትም የምትባል አንዲት ቃል፣ በነርሱ ተጠምዝዛ የነርሱን መገኘት የምትጠይቅ ሊያደርጓት ይችላሉ፡፡ ወይም ደግሞ ለርም የታማኝነት መግለጫ ያደርጓታል፡፡ ወይም ማንኛውንም እነርሱ የሚፈልጉትን ያደርጉታል፡፡ በአጭሩ አንዳችም ነገር በፅሁፍ አያስቀምጡ»

«እንግዲያው እንዴት መቀጠል እችላለሁ?» ሲሉ ይህን ሁሉ ቆመው ሲሰሙ የነበሩት ንጉሱ እጃቸውን ወገባቸው ላይ ወደኋላ አሣርፈው ጠየቁ፡፡

«አባትዎና አያትዎ እንዳደረጉት፣ እርስዎ ራስዎም ብዙ ጊዜ ሲያደርጉ እንደነበረው»

«ሰር ፖንሴን እጅብ የሚሄድልኝ መልዕክተኛ» አሉ የሁሉም የበላይ «አንተ ያልከውን ዘዴ ለመከተል ፈልጌአለሁ፡፡ ግን ማን ይሁን? አንተው ሙራድ?»

«ግርማዊነትዎ ይህን የሚጠይቁኝ ለደንቡ ቢሆንም፣ ይህ ለእኔ ታላቅ ክብር ስለሆነ አመሰግንዎታለሁ፡፡ ግን እንደሚያውቁት ሞት በከፊል መትቶኛል፡፡ ትዕግስት ስለነበረኝ ሞትን አጉንብሼ አሣለፍኩትና አመለጥኩት፡፡ ሆኖም ግን በድጋሚ የሚመታኝ ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አስባለሁ፡፡ ይህም ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡»

«እንግዲያው ማን ይሁን?» ሲሉ ንጉሡ ጠየቁ፡፡ «ሃጅ አሊ ንቃቱንና ጠንቃቃነቱ በመሃመዳውያን መካከል ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ተልዕኮ መወጣት አይችልም»

«እንካችሁ» እሉ ለእያንዳንዳቸው የእጅ መዳፍ የሚያክልና የይሁዳ አንበሣ ምስል መሀሉ ላይ የታተመበት የወርቅ ሜዳሊያ እየሰጧቸው:: «እንደማታምኑበት አውቃለሁ:: ነገር ግን በነዚህ ውስጥ ከቁሣዊ ሃብትነታቸው ይበልጥ ጥቂት ነገሮች አሉባቸው»

ንጉሡ የወርቁን ሰንሰለት ቢጀን ባፕቲስት አንገት ላይ በራሣቸው እጅ ካጠለቁለት በኋላ አቀፉት:: በተመሣሣይ መልክ ለሜትር ዠረሚም አደረጉና ወዲያውኑ ተለዩዋቸው::

የዚያኑ ዕለት በርቀት በሀዝባዊ ስብሰባ ላይ እንደገና ንጉሡን አዩዋቸው:: እንደቀሣውስቱና መሣፍንቱን ከሆነ፣ ተጓዦቹ ንጉሡን በግል ማየት አይፈቀድላቸውም:: ይሁን እንጅ ውስጠ ምስጢርነቱን ሁሉም ያውቃሉ::

ሁለቱም ፈረንሣውያን ዙፋኑ ወደተዘጋጀበት የቤተመንግስት ግቢ ተወሰዱ:: ከንጉሰ ነገስቱ ጥቂት እርምጃዎች ፈቀቅ ብለው አራት አንበሶች በጉጆአቸው ውስጥ ሆነው ያቃስታሉ:: እንደሁልጊዜውም፣ ንጉሡ ነገስቱ ንቅንቅ ሳይሉ በአፈ ንጉሣቸው በኩል ይናገራሉ:: ፖንሴና ሜትር ዠረሚ በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፍተው ሰገዱ:: ግንባራቸውን የገጨው በመንገዱ ላይ የተነጠፈው ጉርበጥባጣ ድንጋይ መጀመሪያ ሲመጡ በጣም ቀዝቃዛ ከነበረው ቢለይም ተመሣሣይ ስሜት ነበረው:: ልዩነቱ እምብዛም በማይታወቅበት ምድር፣ ከሠማይ በታች ተቀራርቦ የተነጠፈው ጥቁር ድንጋይ፣አፈሩ ወይም ድንጋዩ ከእንግዲህ በኋላ በከፊልም ቢሆን የነርሱ ነው:: ከንጉሠ ነገስቱ ዘንድ የቀረቡበት ጊዜ ትንሽ ረዘም ሲል፣ ቀሣውስቱም፣ ተጓገሮቹ ረዘም ላለ ጊዜ እንደሰገዱ ቢቆዩ ጥሩ እንደሚሆን አሰቡ:: ሲነሱ ግን ሁለቱም ሰዎች እያንዳንዳቸው መሬቱን በስሱም ቢሆን እንዳወረዙት ይህም በእንባቸው እንደሆን አስተዋሉ::

ሠላሣ ፈረሰኛ ወታደሮች ከከተማው ጀምሮ የአምስት ቀን ጉዞ እስከወሰደባቸው አክሱም ድረስ አጀበዋቸው ተጓዙ:: እንደደረሱም፣ ከወጣቱ ሙራድና ከቀሪው ቅፍለት እንዲሁም ዝሆኖች ጋር ተቀላቀሉ:: እስከ ንጉሠ ነገስቱ ግዛት ወሰን ድረስ በቁጥር ሰባት ወንዶች ያሉበት ቀላል አጃቢ ኃይል ይዟቸው ሄደ:: ከዚያም አክሱምን ለቅቀው ወደ ቀይ ባህር ጠረፍ ተጓዙ::



# 3

# የሹመት ደብዳቤው

# 1

ዲፕሎማሲ ጥበብ ነው። ጥበብ ሲባልም ርጋታን የሚጠይቅ ጥበብ ነው። ሁልጊዜም ያልተቋረጠ ክብር የሚጠይቅ ጥበብ ነው። ለአረማመድ እንኳ ግርማ ሞገስ የሚሻ ጥበብ ነው። ስለዚህ ከጥረት ጋር፣ ከድካም ጋር፣ ከጥድፊያ ጋር የሚጣጣም አይደለም። በአጭሩ ወይም በሌላ አባባል ከስራ ጋር የሚስማማ አይደለም።

ሙሴ ዱ ማይሌ፣ አንዳችም የሚሠራው ነገር ባልነበረውና ራሱን ሙሉ በሙሉ ለስራ ማዋል ይችል በነበረበት እንደነዚያ ጊዜያት ሳይሆን፣ እንደአሁኑ አስተዋይ ዲፕሎማት ሆኖ ሥራውን አከናውኖ አያውቅም። ማንም ሰው፣ ወኔ ኖሮት ስለዚያ ጊዜው ሀይወቱ ሊጠይቀው ቢችል በምስጢር ተሸፍኖ፣ በማጣት ሽትቶ ይኖር ከነበረበት ደረጃ ተነስቶ፣ ራሱን የመንግስት ባለሟል ማድረግ የቻለ ሰው መሆኑን ይረዳል። የመልዕክተኞቹ ቡድን ወደ አቢሲኒያ ከሄደና ከካህናቱ መጥፎ ሴራ በኋላ፣ ቆንሲሉ የተለመደውን የመንግስት አገልግሎቱን ቀጠለ። ጥቂት ዘግይተው በደረሱት ጋዜጦች ላይ፣ ከሥራ አቻዎቹ አንዳንዶቹ አዲስ የስልጣን ደረጃ እንዳገኙ ያነበበውን ወደጉን በመተው የራሱንም ህጋዊ የጉጉት አቅጣጫ ማመላከት የሚችልበትን ዘዴ መፈለግ ጀመረ። በመጨረሻም፣ ከርሱ በፊት ተወስኖ በነበረ ትዕዛዝ መሠረት ብዙ የቱርክና የአረብ ሰዎችን ጉበኘ። ለነዚህ ሰዎች የሚነግራቸው አልነበረውም፣ ከነርሱም ምላሽ ለመስማት ደንታ አልነበረውም። ውይይቱ፣ ልክ የምስራቃውያን የቀረፃ ጥራት የብዙ ሺህ ተጓገኞችን አይኖች እየማረኩ ግን አንዲትም ቅርፃቅርፅ ወይም መልክ ወይም ምልክት እንደማይችሩ፣ እንዲሁ ያለ አንዳች ፋይዳ ይቋጫሉ።

ይህም በስምምነት የዘለቀ ቆይታ፣ ፖንሴና ሃጅ አሊ ጉዞ ከጀመሩ በኋላ፣ በ1700 ግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ ከፋኛ መሰናክል ገጥሞት ነበር። ይህ ሁሉ የሆነው በሁለት ሣምንት ለድጫ ውስጥ ነው። በመጀመሪያ የክቡር ዱ ፖንቻርትሬይን ደብዳቤ የያዘ ፖስታ ከእሌክሣንደርያ ይመጣል። ቆንሲሉ ሳይረበሽ ለማንበብ ቢሮውን ቆልፎ ተቀመጠ። ደብዳቤው፣ በመደበኛው የሰላምታ አቀራረብ ጀምሮ ወደ ሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮች ይሸጋገራል። ከዚህ በኋላ ሚኒስትሩ ርዕሱን ኢትዮጵያን ወደ ሚመለከት ጉዳይ ይቀለብሱታል። ሙሴ ዱ ማይሌ፣ ከደብዳቤው ውስጥ የሚከተሉትን አስደንጋጭ ዐረፍተ ነገሮች ያገኛል።

*ወደ ኢትዮጵያ የጀመርከውን የመንግስት መልዕክተኞች ሥራ በተመለከተ የንጉሡን ሃሣብ የዘገቡልህ መልካሞቹ ጀስዊቶች፣ ምንም እንኳ ተመሣሣዮች ባይሆኑም ከራሣቸው ሃሣቦች ጋር ያምታቱት ይመስለኛል።*

*አቢሲኒያ፣ የቅዱስ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ በተመሰጋኞቹ የየሱስ ማህበረሰቦች ጥረት መግባቷን ሲያውቁ፣ ግርማዊነታቸው ደስታቸውን መግለፃቸውን በጆሮዬ የሰማሁት ሐቅ ነው። ነገር ግን፣ ቬርሣይለስ ውስጥ የአቢሲኒያን ንጉስ መቀበል አልፈቀዱም ነበር። ከግርማዊነታቸው ጋር ዛሬ በድጋሚ ተመካከርን። እንዲህ ያለውን ኤምባሲ ለመቀበል ደስተኛ እንዳልሆኑ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ። ምክንያቱም፣ ይህ አይነት ተግባር አሁን ያለውን የአውሮፖ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከመቸውም በበለጠ ጥሩ ግንኙቱን ጠብቆ ማቆየት ሲገባ፣ የአቶማን ሡልጣንን የሚያስቆጣ ሊሆን አይችልም ማለት አይቻልም። ከደብዳቤህ እንደተረዳሁት መልዕክተኞችህ በሰላም ስለመመለሳቸው ልበ ሙሉ አይደለሁም። ነገር ግን፣ እነዚህ መልዕክተኞችህ ወደ ካይሮ የሚመለሱ ከሆነና ከኢትዮጵያው ንጉስ መልዕክተኞች ጋር ታጅበው የመምጣት ዕድል ካላቸው፣ እነዚህን ባለሙሉ ሥልጣን አምባሣደር የሆኑ ሰዎችን ወደ ቬርሣይለስ እንዳይጓዙ እዚያው እንድታቆያቸው የራሴን አስተያየት እለግስሃለሁ። ለጥቂት ጊዜ አጠገብህ አቆያቸውና የሚያቀርቡትንም ምስጋና ተቀበል። ከዚያ በኋላ ከብዙ የምስጋና ጭነት ጋር ወደ ጌታቸው መልሰህ ላካቸው። ከዚህ ሌላ አይደረግም።*

እነዚህ አዳዲስ መመሪያዎች አንዳች ክፉ ነገር እንደሚመጣ የሚጠቁሙ ናቸው። ሙሴ ዱ ማይሌ፣ በገበታ ላይ እንኳ ትካዜና ሃሣብ ገብቶት ሲውል በተከታታይ ቀኖች በጉዳዩ ላይ ከሙሴ ማቼ ጋር ሲመካከር ሰነበተ። የዕቃ ማስቀመጫ በሆነችው ትንሽ ክፍል ውስጥ የሚሠራው ፀሐፊ፣ አሁንም፣ አሁንም በመጠራቱ ደስታ እየተሰማው ነው። በሚቀጥለው ሣምንት ደግሞ ሌላ አስደናቂ ሁኔታ ተከሠተ። አንድ አረባዊ ፈረሰኛ በፈጣን ግልቢያ እስከፈረንሣውያን ማሕበረሰብ መኖሪያ ድረስ ሽምጥ እየጋለበ ይመጣል። ያደረገው ቀይ ባርኔጣ በነፋስ ውስጥ እየተውለበለበ፣ ቆንስላው ግቢ ፊት ለፊት ሲደርስ ከፈረሱ ላይ ዱብ ብሎ ወርዶ፣ ለፈረንሣይ ተወካይ ደብዳቤ መያዙን ያስታውቃል። ቆንሲሉ በፖስታው ላይ አጥብቆ በተጠየቀው መሠረት፣ ደብዳቤውን ከመልዕክተኛ እጅ ላይ ራሱ ተቀበለ። ጥቂት ጥያቄዎች ካቀረበለት በኋላ፣ ደብዳቤውን ያመጣው መልዕክተኛ ሦስት ደረጃዎችን አልፎ በአረቢያን የባህር



ወሽመጥ በኩል ከጅዳ የመጣ መሆኑን አወቀ። መልዕክተኛው እንደደረሰ ሊከፈለው ይገባ ነበርና፣ በዋጋው ላይ እንዲከራከር ሙሴ ዱ ማይሌ ሃላፊነቱን ለፀሐፊው ሰጠው።

አዲሱ ደብዳቤ ዲፕሎማቱን ከመጀመሪያው የበለጠ መንፈሱን ረበሸው። በቤቱ ውስጥ ያለው አጠቃላይ እንቅስቃሴም ግራ ተጋባ። ስንፍናን ዱቄት ለማድረግ በሚገባ ተሟሽቶ የሰለጠነው የቆንሲሉ ጭንቅላት፣ ዛሬ እፍኝ በማትሞላ የመታወክ ፍሬ መንሣጠጥና ማቃሰት ጀመረ። ማዳም ዱ ማይሌ፣ ባሏ እንደገና ጤናውን አደጋ ላይ እየጣለ መስሏት ተጨነቀች።

ከሁሉም ይልቅ የተጨነቀችውና ዜናውን የተራበችው በርግጥም አሊስ ነበረች። በነዚህ ሁሉ ረኸርም ወራት ሁሉንም የስሜት ደረጃዎች በማቋረጥ፣ ከተስፋ ወደ መጨነቅ፣ ከዚያም መጥፎ ነገር ይደርሣል በሚል መሰቃየትና በመጨረሻም ገና ያልተከሰተ አስፈሪ ሁኔታ ይኖራል በሚል ተሰቃየች። በአሁኑ ጊዜ እጅግ አደገኛና ወደ ሞት ሊያደርስ ወደሚችል ደረጃ ራሷን እያደረሰችው ነው።

የሁለቱ መልዕክተኞች መድረስ፣ የአሊስ ትዕግስት የማጣት እና የጉጉቷን መጠን እንደአሣት የሚያቃጥል ትኩሣት ለቀቀባት። ሙሴ ዱ ማይሌ ግን አዕምሮውን የያዘውን ምስጢር ጉዳይ ለቤተሰቡ ላለማጋለፅ ወሰኗል። የመልዕክተኛው ቡድን ወደ አቢሲኒያ ሲንቀሣቀስ እድሮበት በነበረው ከመጠን ያለፈ በራስ መተማመን ሳቢያ፣ በቤቱ ውስጥ ተፈጥሮበት የነበረውን ምስቅልቅል ሁኔታ በሚገባ ያስታውሰዋል። በዙሪያው ያሉት ሰዎች ያቀረቡለትን የመጀመሪያ ጥያቄ ተከትሎ ምስቅልቅል ነገሮች ስላሉ፣ እንደ አይሰተር አሣ ዝም፣ ዝግት ብሎ ያጉረመርማል።

በር ስር ተለጥፈው ለማዳመጥ ከፍተኛ ጥረት ከማድረጋቸው በስተቀር፣ አሊስና ፍራንቾይዝ የተሻለ ነገር ማወቅ አልቻሉም። በዚህም ሣቢያ መላምቶችን መደርደር ጀመሩ። አሊስ፣ መንጓትና ፍቅር ስላለባት፣ የታሰባትና በርግጥም ያለማጋነን ያጋጠማት፣ በጆን ባፕቲስትና በተልዕኮው ላይ አንዳች አሰቃቂ ነገር ደርሷል የሚል ነው። ፍራንቾይዝ በመጨረሻ ላይ አንድ ሃሣብ እስኪታመጣ ድረስ ተስፋ በመቁረጥ ምንም አይነት ዜና ላለመስማት ወስና ነበር።

«ቆንሲሉ ይህን በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚያከናውኑት ስላልሆነ፣ ያለው ብቸኛ ነገር ምንነቱን መፈተሽ ነው» አለች

የዝሆኑን ጆሮዎች አስቀርጦ ያስቀመጠበት ምክንያት ፍፁም የተለየ ነበር። ከዚህ በፊት እንደሰማው የዝሆን ጆሮ በሚገባ ተጠብቆ እንዲደርቅ ቢደረግ ተወዳዳሪ የሌለው ልስላሴ ይወጣዋል።

የባሮችም ሁኔታ የተለየ አልነበረም። ለቱርካዊው ሱልጣን ምስጋና ይግባውና እርሱ በላከለት ጠመንጃ ተኳሽ፣ በትንንሽ ደሴቶች ላይ የነገሠው የምፅዋ መስፍን፣ መንገደኞቹ ሣይረበሹ እንዲያልፉ የሚጠይቀውን የንጉሡን መልዕክት ለማክበር ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነበር። ናኢቡ፣ ሃያላኑ ጎረቤቶቹ በርሱ በኩል መልዕክተኞቻቸው እንዲያቋርጡ ሲጠይቁት አጅግ ያመሰግናል። ይሁን እንጂ በንጉሥ ነገስቱ መልዕክት ውስጥ የባሮች ነገር ስላልተጠቀሠ፣ ናኢቡ አራቱን ሴቶች ለራሱ ጥቅም ሲል አስቀራቸው። ከሙራድ ሰዎች አንዱ በዝሆኑ ሣጥን ውስጥ አብሮ ሞተ። አራቱ ግን ጅዳ ደረሱ። የእንስሳቱ ጭነት ቀለል ይልላቸዋል በሚል ለመካው ሸሪፍ ታስቦ የነበረውን ስጦታ፣ አርመናዊው፣ ምፅዋ ላይ ሸጧቸዋል። በምትኩ ግን የቀረበለት የጥርኝ ዝባድና ሁለት ክረጢት የወርቅ አፈር፣ ለሸሪፉ አነስተኛ ካሣ ሆነለት። ከቀሩት አቢሲኒያውያን ባሮች ይበልጥ ፈርጣማ ጡንቻ ባላቸው በሁለቱ ላይ አይኑን የጣለው ሸሪፍ፣ እነዚህ የርሱ ንብረቶች መሆናቸውን አሳወቀ። በዚህ ላይ ፖንሴ ተቃውሞ ሲያነሣ፣ ሸሪፉ አንዱን ብቻ ለመውሰድ ተስማማ። ከዚህ በኋላ የተረፉት ሦስት ብቻ ሆኑ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ እግረ ቀልማማ ሲሆን፣ ሁለቱ የአስራ አንድና የአስራ አራት ዓመት ሕፃናት ናቸው። እነዚህ ልጆች በዚያን ዕለት ምሽት በስዊዝ ኮረብታዎች ላይ እራታቸውን በሉ።

ሁለቱ ፈረንሣውያን እስካሁን ያለውን ታሪካዊ ሂደት ሊያሻሽሉት አልቻሉም። ፖንሴ፣ በአረቢያ ውስጥና በቀይ ባህር ጉዞ ላይ ክፉኛ ከመታመሙ በስተቀር ፈረሶቻቸውና ብዙው ጓዛቸው አሁንም ድረስ መኖራቸው ርግጥ ነው። ቀደም ሲል ምፅዋ ውስጥ ሜትር ዠረሚ ታምሞ ነበር። ከአንድ ዓመት ጉዞ በኋላ ሰውነታቸው መንምኖ፣ በትኩሣትም ደክሞ፣ በጀልባ ላይ ከወጡም በኋላ እግሮቻቸው ቆስለው፣ የሚታጠቡበት የጨው ውሃ አሳብጦባቸው፣ አሽዋውም አበቃ ሲባል ይባስ እያበሳጫቸው ነው። ክብራቸውንና ማዕረጋቸውን ሊመልስላቸው የሚችለው ጅዳ ውስጥ ተስፋ አድርገው የገዟቸው አዳዲስ ቦላሌዎች፣ ባለማሰሪያ ኮሌታ ያላቸው ከጥጥ የተሰሩ ሸሚዞችና ቀያይ ለደሪያዎች ናቸው። የገዙትም እንዲህ ነው። ጥቂት የባህር ላይ ወንበዴዎች እነዚህን ልብሶች ከአውሮፖውያን የሸልማት መርከብ ላይ በምርኮ የወሰዷቸው ናቸው። ወንበዴዎቹም ልብሶቹን በመጠነኛ የወርቅ መጠን ሊለውጧቸው



ይስማሙዋቸዋል። ልብሶቹን ከገዙ በኋላ በጥንቃቄ አጣጥፈው በቆዳ ሻንጣዎቻቸው ውስጥ ይደብቋቸዋል። ከዚህ በኋላ የተነሣው ጥያቄ እነዚህን ልብሶች እንዴት ሊጠቀሟቸው እንደሚችሉ ነው። ከዚህም በተረፈ ዘማቹ ጓድ፣ ካይሮ መግባቱ አይቀርምና እንዴት ሊገሰፅ ነው የሚለው ሌላው ጥያቄ ነበር።

«ከካይሮ የሶስት ቀናት ጉዞ ርቀት ላይ ነን» አለ ጆን ባፕቲስት «ከዚህ በኋላ ከነዚህ ከሁለቱ ጋር አብረን እንጓዛለን። በመጨረሻው ሠፈራችን ላይ፣ ዠረሚ ፈረስህን ለኛ ትተህ በቅሎ በመያዝ ወደ ሰሜን ትሄዳለህ። ከሁለት ቀናት በኋላ በአባይ ዳር ካለችው ቤንና መንደር ትደርስና ከአንድ ቀን በኋላ ከአሌክሳንደሪያ ካይሮ ትገባለህ። ምክንያቱም ሄዷል የተባልከው አሌክሳንደሪያ ስለሆነ ነው።»

ምንም እንኳ ይህ ሰው የጉዞውን መከራ ሁሉ አብሮ የተጋራ ቢሆንም፣ በመልሱ ላይ አንዳችም ክብር ሳያገኝ ነው። ይሁን እንጅ ይህን ትሁት ድርሻ፣ ይህ ልምድ ያለው የጥንት ወታደር በዝምታ መቀበሉን ፖንሴ ያውቃል።

«ሁለታችንስ፣ አብረን እንቆያለን?» ሲል ሙራድ በመጓጓት ጆን ባፕቲስትን ጠየቀው።

«አዎን፣ ግን ለሁለት ቀናት ብቻ። ከዚያም ዠረሚ የሚለየን ቦታ ላይ ትቆያላችሁ። እኔ ቀድሜ እሄዳለሁ።»

«ምን?» አለ ሙራድ «ብቻዬን በምድረ በዳ መካከል ልቆይ ነው?»

«ብቻህንማ አትሆንም። ባሮቹ አሉልህ» ሲል ሜትር ዠረሚ አጉረመረመ

«ቅር የሚልህ ነገር አለ? ለመሆኑ አይተሃቸዋል?»

«ደህንነቱ በሚያስተማምን የሲራራ ነጋዴ ሰፈር እናርፋለን። እዚያም ለሚጠብቃችሁ ሰው እኔ እከፍላለሁ።» አለ ፖንሴ ኮስተር ብሎ

«እናም አንተ ቀድመህ ትሄዳለህ?» አለ ሙራድ ጠንካራ እምነት ሳይኖረው።

«የናንተን መድረስ አስቀድሜ ወሬው እንዲነዛ አደርጋለሁ። በሚቀጥለው ቀን እኩለ ቀን ላይ፣ በተቻላችሁ መጠን በጨዋነትና በኩራት ትመጣላችሁ። ከባሮቹ አንዱ፣ በዕድሜ ጠና

ያለው፣ የእግሩን ሽባነት ለመደበቅ ቁርጥራጭ ጨርቆችን እንጠመጥምበትና በሌላው በቅሉ ላይ ሆኖ ይከተልሃል። ሁለቱ ህፃናት በእህዮች ላይ ሆነው ከኋላ ይከተላሉ።»

ሙራድ ጭንቅላቱን አነቃነቀ።

«ለመሆኑ ሣጥንህ ውስጥ ስንት ልብሶች አሉህ?» አለ ፖንሴ

«አንድ»

«በመጠባበቂያነት ያዘው። በይፋ የምትታይበት ቦታ ስትደርስ ቀይረው። ወደ ከተማዋ መግቢያ ላይ ስትደርስ ሰላምታ ሊያቀርቡልህ የሚመጡትን ሰዎች እጅግ ረዥም፣ አስቸጋሪና አደገኛ ጉዞ አድርጐ የሚመጣውን ሰው እባካችሁ ተዉት በላቸው።»

ከዚህ በኋላ በጥቂት ተጨማሪ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ከተስማሙ በኋላ፣ ጊዜው ስለመሸ በእሣቱ ዳር በየጆንያዎቻቸው ላይ ተጠቅልለው ተኙ ። ጆን ባፕቲስት፣ ታላቅ ፍንደቃ ተሰማው። መላ አካሉ፣ አንድ ሺህ አንድ የድካምና የሕመም ስሜት ለቀቀበት። ላለፉው አንድ አመት ከስራቸው ሆኖ ያደረባቸውንና በቅርቡ የሚለያቸውን የከዋክብት እይታም አሰበ። በቅርብ ያለችውን ካይሮና የአሊስ ልዩ ስሜት አዕምሮውን ሞላው። ሁሉም ነገር ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢሆንም እንኳ አንድ ተንኾ በጉዞ ጆማሮው ላይ ትዕግስት አያጣም። ስለሆነም በጉዞው መሃል ላይ የነበረው ትዝ አለው። ታዲያ አሁን በመመለሻው ሰዓት ላይ መዘግየቱ ለምንድን ነው?። ደቂቃዎች እንዲህ እየተንቀራፉፉ የሚያዘግሙት ለምንድን ነው? በተለይም ሰላም በሚያገኝበትና ሁሉንም በመጨረሻው ላይ በሚያውቅበት ሰዓት ለምንድን ነው ጥቂቶች እንቅፋት የሚሆኑት? ሲል ይጠይቃል።

የመመለሱን ሃሣብ ጆን ባፕቲስት ለረዥም ወራት በውስጡ ሲያሣድገው ቆይቷል። አሊስን፣ ፍቅሯንና እስከ ዘለዓለም የሚጣመሩበትንም ሁኔታ አስቧል። ነገር ግን የሚወድዳትን ሴት፣ በዓይኖቹ ሥር የሚያኖርበትን፣ ራሱንም ለታላቅ ደረጃ ለማብቃት፣ ድንጋይ በድንጋይ ላይ በመገንባት መላውን ሕንፃ እንዴት እንደሚሰራው በቅዕበት አሰበ። በመካከላቸው ያለው ርቀትና ልዩነት ምንም ያህል የሰፋ ቢሆንም፣ ከተለያዩና ግራ ከሚያጋቡ ደካማ ተስፋዎች የተሠራ የሃሣብ ሕንፃ ቢሆንም፣ ትዝታውን ይጠግንለታል። ጥቂት ረዘም ካሉ ያለፉ ቀናት የተሰበሰቡ ያልተሟሉ የዕይታና የድምፅ መረጃዎችን ይዞ፣ በመሠረቱ አይታው የማታውቀው



ሴት ታፈቅረኛለች ብሎ ማሰቡን፣ በሚገባ የማታውቀው ሴት ትጠብቀኛለች ብሎ በጭፍን የሚወራረድ መሆኑን፣ ይህ ሁሉ ሃሣብ እንዴት በሚከዳ በአሸዋ ላይ የተገነባ ሕንፃ እንደሆነ ተገንዘበ። ይህን እያሰላሰለ ረዥምም ቦታን ለረዥም ጊዜ ተጓዘ። ይህ ታዲያ ከራሱ ፍላጐት ሌላ ሊሆን ይችል ይሆን? ያንን ሌሊት በነዚያ ስለታም የምድረ በዳ ድንጋዮች ላይ ሳይመቸው አረፍ ብሎ፣ ጆን ባፕቲስት፣ አሊስ ታፈቅረው እንደሆነ ብቻ ሳይሆን፣ ከቶውንም እርሷ በዚህ ዓለም ላይ በርግጥ ኖራ ይሆን ሲል ራሱን ጠየቀ።

በመጨረሻም ይህን የመጨረሻ ሠፈር እኩለ ለሊት ላይ ለመልቀቅ ወሰነ። ባለፉው ቀን ሁሉም ነገር እንደታቀደው ተከናውኗል። ሜትር ዣረሚ፣ እንደልማዱ እያጉረመረመ በአሌክሣንደሪያ አቅጣጫ ሄዷል። በጣም እንቅስቃሴ በሚበዛበት የሲራራ ነጋዴዎች ማረፊያ ስለሠፈሩ፣ ሙራድ ተፅናንቷል። በዚህም ላይ ሁለት ሚሊሺያ ወታደሮች ለሊቱን እዚያ ለማሣለፍ ወስነዋል። ሁሉም ሰው ስለደከመው በጊዜ ተኛ። ሙራድም ወዲያውኑ በከፍተኛ ድምፅ ማንኮራፋት ጀመረ። ጆን ባፕትስት በበኩሉ እንቅልፍ እንደማይወስደው አውቋል። በፀጥታ ፈረሱን ጫነው። እህያውንና ሌላውን መሣሪያውን ሁሉ በሚቀጥለው ቀን ወደ ከተማ እንደሚደርሱ ስላወቀ ከቀረው ጓዝ ጋር ተወው። ሲነሳ ግን፣ ንፁህ ሸሚዙን፣ ባሌውንና ኮቱን ለብሶ ብቻውን ወጣ። በምዕራብ በኩል ትልቅ ነጭ ጨረቃ መንገዱን እንደ ክረምት ፀሐይ ወገግ አድርጋ፣ በማብራቷ ታሣያለች። ቀኑ የሚያንገበግብ ሙቀት በመሆኑ ከአንዳንድ ኪስ ቦታዎች ላይ ባሉ መንገዶች ሞቃት አየር ይጋረፋል። ብቸኛው ሰው እንደ ብዙ የሣር ኩቶች መውለብለብ ብቅ ጥልቅ እያለ ይጋልባል። በምድረ በዳው መሬት ላይ የፈረሱ የኮቴ ምት እንደ ብዙ የልብ ትርታዎች የገደል ማሚቶ ፈጥሮ ይሰማል።

ጆን ባፕቲስት፣ በፕቶሎሚ ቤተመቅደስ ፍርስራሽ ስር ሲያልፍ፣ ዓለም ገና በጨለማው ውስጥ እንደጠለቀች ነች። የጊዜውን ማጠር ማሰላሰል አልፈለገም። ይልቁንም፣ እርሱ በተቃራኒው፣ የእያንዳንዷን ሴኮንድ ዘለዓለማዊነትና ከቤቱ ተለይቶ የቆየበትን ማብቂያ የሌለውን የጊዜ አዝጋሚነት ያስባል። ሰማይና መሬት ሲላቀቁ ካይሮ ደረሰ። ዘበኞቹ ሁሉ ተኝተዋል። በሮችም ዝግ ነበሩ። ውብ ልብስ የለበሰና ምንም መሣሪያ ያልታጠቀውን ፈረንሣዊ ከተመለከቱ በኋላ ምንም ጥያቄ ሳያቀርቡለት እንዲገባ ፈቀዱለት። እንደግራጫ ጥላ ከወዲያና ከወዲህ በመዋከብ ላይ ከሚገኙት ለማኞች በስተቀር፣ ከተማዋ አሁንም በእንቅልፍ

«እምላኬ ! በጣም ክስተሃል። ያ ጉንጭህን ይሞላው የነበረው ፂምህም ደብልጥ ጉድጉዷል! ፀጉርህ በጣም አድጓል!»

አይኖችዋ እንባ እንዳዘሉ ታየው ጀመር። እርሱ በበኩሉ ስሜቱ በጣም ስለተነካ ቃል መተንፈስ አልቻለም።

«እንዴት ያሉ ውብ ልብሶች ናቸው?» አለች፣ ልዩ ልዩ ጥልፍ የተሰራበትን ወፍራም የቀይ ኮት ጨርቁን እየነካች።

በባህር ላይ ዘራፊዎች ተይዛ የነበረችው መርከብ ከፍተኛ ዋጋ ነበራት ማለት ነው። ጆዳ ውስጥ ስለጉዳዩ እምብዛም አትኩሮት ያልተሰማው ጆን ባፕቲስት፣ እንደጨዋ ሰው መልበሱን አሁን ተገነዘበ።

«ርበሃል?» ስትል ፍራንቾይዝ ጠየቀችው። ራሷን ስትገዛ «ጠምቶሃል?» ቀይ ከቤት የሆነ ነገር አገኛለሁ።

«የለም» አለ ጆን ባፕቲስት «አትቸገሪ፣ ይደርሳል፣ በኋላ፣ በኋላ፣ ብቻ የት እንዳለች ንገሪኝ»

«አ! ሙሴ ጆን ባፕቲስት፣ ስትጠይቃት መስማቴ ለኔ ደስታ ነው። ይህ ማለት ደግሞ አልረሣሃትም ማለት ነው። በጣም ሩቅ አገር በመሄድህ ምክንያት ፍርሃት ነበረብኝ። ለርሷ ግን ሁልጊዜም በተስፋ እንድትጠብቅህ እነግራት ነበር። በህይወት መንገድ ውስጥ ብዙ ነገሮች ሊያጋጥሙና የልብ ስሜትም ሊለወጥ ይችላል»

ጆን ባፕቲስት ተነስቶ፣ እግሮቹን ከአልጋው ልብሶች ውስጥ አውጥቶ ቀጥ ብሎ ተቀመጠ።

«ሊለወጥ ይችላል? የኔ ግን በምንም ምክንያት አይለወጥም። የሆነው ሆኖ እባክሽ የት እንዳለች ንገሪኝ? ለመሆኑ ሃሣቧስ እንዴት ነው?»

«ሃሣቧ ሁሉ አንተኑ የማፍቀር ነገር ነው። ከዚህ ከሄድክበት ዕለት ጀምሮ ካንተ በስተቀር ሌላ አስባ አታውቅም።»



«አ! ፍራንቾይዝ» አለ ጆን ባፕቲስት በክንዶቹ እያቀፋት ወይም እናቱ የሆነች መስሎት በርሷ ክንዶች ውስጥ እየገባ።

ከዚህ በኋላ የፍራንቾይዝን ትልልቅ እጆች በእጆቹ ውስጥ ይዞ ወደ ኋላ ራመድ አለ።

«ወደዚህ ትመጣለች?»

«በየዕለቱ»

«መቼ?»

«እ . . . » አለች ፍራንቾይዝ እየወጣች ያለችውን ፀሐይ በመስኮት በኩል እያየች «በዚሁ ሰዓት አካባቢ»

በጉጉት ስሜት፣ ጆን ባፕቲስት ዘሎ ተነሣ

«መምጣት የለባትም . . . » አለ። «ሂጅና እንዳትመጣ አድርጊያት። መመለሴን ንገሪያት። ነገር ግን በዚህ መልክ ሆኜ ልታየኝ አይገባትም። ለመሆኑ ማኑኤል እስካሁን እዚሁ ነው?»

ማኑኤል በዚህ ግቢ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የኖረ ሽማግሌ አገልጋይ ነው። የቀድሞው ጌታው ወደ ፈረንሣይ ከመመለሱ በፊት፣ ጥቂት የጡረታ ገንዘብ ትቶለታል። ምንም እንኳ ዲዳ ቢሆንም፣ እስካሁን ድረስ ጠንካራ ሰው ስለሆነ፣ ፖንሴና ሽሪኩ በየጊዜው ሥራ ይሰጡት ነበር።

«እቤት ነው ያለው» አለች ፍራንቾይዝ

«ጥሪው። በገንዳው ውስጥ ውሃ እንዲሞላልኝና ሣሙናም እንዲያመጣልኝ ንገሪው። በተጨማሪም ፀጉሬንና ጢሜን እንዲያስተካክልልኝ እፈልጋለሁ። አንቺም ፍራንቾይዝ፣ ልትንከባከቢኝ ይገባል።»

«ቆስለሃል እንዴ?»

አለምን በሚያተራምሷት ዲፕሎማቶች እጅ ስለሚገባ አንድ ተራ፣ አግረኛና የልምድ መድሃኒት አዋቂ፣ ሣይሣለቁበት እድገት ሊመኝ እንደማይችል ሊረዳው ይገባዋል። ለኢትዮጵያ ኤምባሲ ተገቢውን አቀባበል ለማድረግ፣ ሙሴ ዱ ማይሌ አግባብነት ያላቸው ጥያቄዎችን ጠየቀ። የመልዕክተኛውን ስም፣ የክብር ተከታዮቹን ብዛት፣ የተጓዘበትን አቅጣጫና እዚህ ሊደርስ የሚችልበትን ሰዓት ግምት ጠየቀ። ወጣቱን ሰው፣ በጉዞው ላይ ስለነበረው ጀብዱ ላለማሞገስ፣ ቆንሲሉ ጥሩ ጥንቃቄ አድርጎ አለፈው። ተጓዡም በዚህ ነጥብ ዙሪያ ፍንጭ ሲያሣየው፣ እንዲህ ያሉትን ዝርዝር ጉዳዮች በርሱ ደረጃ ያለ ሃላፊ ሊሰማው እንደማይገባ ግልፅ አደረገ። ስለነዚህ የጉዞ አጋጣሚዎች ሁሉ፣ ቆንሲሉ ጆሮውን ቢሰጥ ሲበዛ ጅልነት ይሆናል። ሰውዬውም፣ እነዚህ ጀብዱዎች ለክብሩ ብቸኛዎቹ መሠረቶች ስለሆኑ ለራሱ ጠቀሜታ ሊያስተካክላቸው እንደሚጥር እርግጠኛ ነበር።

ጆን ባፕቲስት ፍፁም ደክሞታል። ወደ ቆንስላው ግቢ ሲገባም ሞልቶት የነበረው ጥልቅ ስሜትና አሲስን በድንገት የማግኘት ተስፋው ሁሉ፣ ስርዓተ ቢስነቱን በመመገብ ሊጠቅመው የሚችለውን የወኔ ሃይሉን፣ ተስፋ አስቆራጭ ወደሆነ መልክ ለውጦታል። ያጋጠመው የእንኳን ደህና መጣህ አቀባበል፣ ከቆንሲሉ የሚጠብቀው አይነት እንደሆነ አውቋል። ይሁን እንጅ፣ ከምሩ፣ ምናልባትም ይህንኑ ተስፋ አድርጎ ነበር። ሆኖም እጅግ ጥልቅ የቅሬታ ስሜት አደረበት።

«መስናበት እንድችል የቆንሲሉን ፈቃድ ባገኝ?» ሲል ወደ በሩ እየተራመደ ጆን ባፕቲስት ጠየቀ።

«አመሰግናለሁ» አለ። ለመልካም ተግባር የሚገባውን ሽልማት በሚገባ የሚያውቀው ሙሴ ዱ ማይሌ።

«ደህና ሁን ሙሴ ፖንሴ»

ወጣቱ ሰው ወጥቶ ሄደ። በውይይቱ ወቅት በአንድ ጨለማ ጥግ ቆይቶ የነበረው ማቼ፣ ወደ ቆንሲሉ ጠረጴዛ በመቅረብ ወደፊት ጉንበስ በማለት በተጣደፈና ዝቅ ባለ ድምፅ ተናገረ።

«ክቡር ሆይ፣ ኤምባሲውን ለመገናኘት የሚሄደውን የመልዕክተኞች ቡድን ይህ ሰው እንዲያጅብ ቢደረግ ተገቢነት የለውም ማለት አይቻልም»



«እሱንʔ እና በምን ሚናʔ» ሲል ሙሴ ዱ ማይሌ ጠየቀ።

«እንደሚመስለኝ . . . የንጉሡ መልዕክተኞችና ይህ መድሃኒት ቀማሚ ርስ በርስ ይተዋወቃሉ። ቢያንስ ቢያንስ፣ ከርሱ ጋር የሚኖረን የመጀመሪያ ግንኙነት ቀላል ይሆናል። አምባሣደሩም፣ የጉዞ ጓደኞቹ የት እንዳሉ ይጠይቅ ይሆናል . . .»

«ልክ ነህ። አሁንም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ወጣ ብለህ በመንገድ ላይ እንዳለ ተመልከተውና፣ መገኘት እንደሚገባው ንገረው» አለው ቆንሲሉ።

ልብስ አጣቢዋ፣ ጥሩ መዓዛ ያለውን ትኩስ ሽቶ በተፈጥሮ በሚያመነጨው ጠረኑ ፋንታ ልብሱ ላይ ስለረጨችበት፣ ሙሴ ማቼ ወደ በሩ ሲንደረደር ሽታው በክፍሉ ውስጥ ቀረ።

አዳራሹን አቋርጦ ደረጃው ላይ ፈጥኖ ደረሰ። በዚያም ሳይታሰብ በመንገዱ ላይ ራቅ ብሎ አገኘዋለሁ ብሎ ከሚያስበው ፖንሴ ጋር ተላተመ። የቀርከሃ ቅርጫት በክንዷ ስር ይዛ የነበረችው ፍራንቾይዝ፣ ከመድሃኒት ቀማሚው ጋር በመወያየት ላይ እንደነበረች አመነ። እርስዋ ግን ፀሐፊውን እንዳየችው አንዳችም ነገር ሳያቋርጣት፣ ከአትክልቱ ሥፍራ በቀጥታ እንደመጣች አስመስላ ወደ ቤት ገባች። ምንም ነገር የማይዘነጋው ሙሴ ማቼ፣ በተለይም አብራርቶ ሊገልፀው የማይችለውን ነገር የማይዘነጋው ሙሴ ማቼ፣ በርቀት ከዝግ በሚያቀይበት፣ ነገር ግን በሚገባ ለይቶ ሊያውቀው በሚችልበት የአዕምሮው ክፍል ውስጥ፣ «ጥርጥር» የሚለውን ግምታዊ ሃሣቡን መዘገበ። ምንም እንዳላስተዋለ ሆኖ፣ ጆን ባፕቲስትን አናገረው።

«ነገ ጠዋት፣ ለአምባሳደሩ ሰላምታ ለማቅረብ ከሚንቀሣቀሰው የመልዕክተኞች ቡድን ጋር ተቀላቅለህ ለመሄድ ራስህን አዘጋጅ። በሰዓቱ ላይ እስከ አሁን ያልወሰንን ቢሆንም፣ ጊዜው ሲደርስ በተረኛው ወታደር በኩል መልዕክት እንልክብሃለን።»

ሙሴ ማቼ እንደማቅማማት ብሎ፣ ሙሉ በሙሉ የግሉን ምክር እንደሚለግስ ሰው፣ ዝቅ ባለ ድምፅ «እናም ተስማሚ ልብስ ልበስ። እዚህ የምንነጋገረው ወደ ንጉሡ ከሚሄደው ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ጋር ነው።»

«እንዲህ መሰዬ መታየት አልፈልግም»

«ጆን ባፕቲስት በማንኛውም ሰዓት እዚህ ሊደርስ ይችላል። እንደሚመስለኝ ለአፍታ እየት የማድረግ ጉዳይ ነው። የሚመጣውም ሳንቺ ሲል ነው። የሚፈልገው ደግሞ አንቺ እስካሁን እዚሁ መኖርሽንና የምትጠብቂው መሆንሽን ለማየት ነው። መዘጋጀት ያለብሽ ራቅ ያለ ቦታ መሄድ ስለሚያስፈልግሽ ጉዳይ አይደለም። ብቻ ይይሽ። አንችም ታይዋለሽ። ሁለታችሁም፣ እንደስሜቶታችሁ ትፅናናላችሁ። ወደፊት ደግሞ ረዘም ያለ ጊዜ አብራችሁ ማሳለፍ ትችላላችሁ።»

«ፍራንቾይዝ፣ አይሆንም! ይህ ቡጉር በጣም አስጠሊታ ነው። እንዲህ ሆኜ እንዲያየኝ አልፈልግም።»

---

ሰፊ ልምድና ተሞክሮ ያላት ሴት በመሆኑዋ ከዚህ የበለጠ መጉትጉት ጥቅም እንደሌለው ፍራንቾይዝ ተገነዘበች። አሊስ፣ የቡጉሩ ጉዳይ በእውነት ያስጨነቃት ግብዝ አይደለችም። ይህ ሁሉ፣ የፍቅር ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ላይ የሚታይና የፈስጉትን እንዳያደርጉ ነፃነታቸውን የሚገድብባቸውና ባህርያቸውን አፍኖ የሚይዝባቸው ምልክት ነው። ፍቅር በህዋ ውስጥ የሚጋልብበት ወይም በህልም ውስጥ በነፃነት የሚከንፍባቸውና አያንዳንዱ ተፈቃሪ እንዲፈላለግ ወይም እንዲሸሻሽ የሚያደርግበት ጊዜያት አሉት። በሌላ በኩል፣ ፍቅር ገና መታወቅ ሲጀምር፣ አንዳች አነስተኛ እንቅስቃሴ፣ ሌላው ቀርቶ ደካማ የእጅ ወይም የክንድ እንቅስቃሴ፣ ሙሉውን ባሪያዎችን ብቻ ከሚጭን መርከብ ላይ ሰንሰለቶችን ለመበጣጠስ ከሚጠይቀው ጥረት የበለጠ ሃይል የሚጠይቅበት ሁኔታ አለ። ይህም ሆኖ ከመጠበቅ በስተቀር ምንም ማድረግ አይቻልም። ፍራንቾይዝ፣ ወጣቱ ሰው ይህን እንዲያውቅ ለማድረግ በአዳራሹ ውስጥ እንደሚተላለፍ ሆና ሄደች። አሊስ፣ በክፍሏ ውስጥ ብቻዋን ሆና ጣቶችዋን ነከሰች።

❧

ካይሮ የሚገኘው የፈረንሣውያን ማህበረሰብ፣ የአውሮፖ አገራት ሕዝቦችን ሁሉ የሚያቅፍ ነው። የፈረንሣይ፣ የጣሊያንና የእንግሊዝ እንዲሁም የሌሎች አገሮች ተወላጆችን የሚያቅፍ ነው። አጠቃላይ ቁጥራቸው በብዙ መቶ ከሚሆኑት ከነዚህ ሕዝቦች መካከል



ብዙዎቹ ነጋዴዎች ናቸው። ከአውሮፖውያን አገሮች መካከል ተወካይ ያላቸው ሁለት ብቻ ሲሆኑ፣ እነርሱም እንግሊዝና ፈረንሣይ ናቸው። ይሁን እንጅ፣ በዚህ ወቅት ላይ የእንግሊዝ ልዑካን ቁጥር እንደተለመደው ፍፁም ስለቀነሰ፣ ቆንሲል የለውም። ስለዚህም ላቅ ያለውን ቦታ የያዘው የፈረንሣውያኑ ነው።

የፈረንሣይ ቆንስላ፣ በአስተዳደሩ ጥላ ሥር የሚገኙ ፈረንሣውያን ላይ ቀጥተኛ ባለሙሉ ሥልጣን ሲሆን፣ በሌሎች አገሮች ዜጋዎች ላይ ግን ሥልጣኑ ቀጥተኛ አይደለም። እነዚህ ሰዎች፣ በቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑና ራሣቸውንም መከላከል የማይችሉ እንደ ማሮናይት ክርስቲያኖች ያሉ ስለሆኑ ፈረንሣይ ትጠብቃቸዋለች። በሌላ በኩል፣ ካይሮ ውስጥ ለጋሲዮን ለሌለው አገር ፈረንሣይ ለነዚህ ዜጐች የመንግስትነት ሚና እንዳላት አድርጋ ትገምታለች።

በነዚህ ማህበረሰብ አባላት ውስጥ ያለት ሰዎች፣ የቆንሲሉን ስልጣን፣ ሁሉም እኩል አይቀበሉም። በምስራቅ ሜዲትራኒያን የአውሮፖውያንን ማህበረሰብ ቁጥር ከፍ የሚያደርጉት ነጋዴዎች፣ ለቆንሲሉ ሥልጣን ያላቸው ክብር የማያስደስትና ፈቃደኛነትም የማይታይበት ነው። ይሁንና ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም። በቆንሲሉ ሥልጣን ሥር እንዲሆኑ ያደረጋቸው፣ ቁርኮች፣ በእስላማዊ አገር ውስጥ ለመኖርና ለመነገድ የሚችሉት በዚህ መልክ ሲሆን ብቻ እንደሆነ ስለፈቀዱ ነው። ነጋዴዎቹ፣ ለቆንሲሉ ሥልጣን ተመጣጣኝ የሆነ አቅም እንዲኖራቸውና የነርሱንም አቤቱታ የመቀበል ዕድል ከፍ ለማድረግ ሲሉ የማህበረሰባቸውን ተወካይ እንደራሴ ይመርጣሉ። የቆንስላው ባለስልጣኖችም፣ ፈረንሳውያንን የሚመለከት ማንኛውንም ጉዳይ ለመቀበልና ለመስማት ግዴታ ይኖርባቸዋል። ቀደም ባሉት ጊዜያት፣ ቆንሲሎቹ ሥልጣናቸውን በተወካይ እንደራሴው ላይ ለመጫን ይሞክሩ ነበር። ይህ ድርጊት ግን፣ ውጤቱ መጥፎ ነበር። ሙሴ ማይሌ ሥራውን ለመጀመር ሲመጣ፣ ማህበረሰቡ ያደረገለት አቀባበል ቀዝቃዛ ነበር። ከርሱ በፊት የነበሩት ቆንሲሎች ተመርጠው የወጡት ከራሱ ከማህበረሰቡ ውስጥ ሲሆን የርሱ ሹመት የመጣው ግን ከቬርሣይለስ ነው። ስለዚህ፣ ከመነሻው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የተወካይ እንደራሴውን የግል ድጋፍ ለማግኘት ደፋ ቀና በማለት ጥረት አድርጓል። በዚያን ጊዜ ተወካይ የነበረው ግለሠብ ብሬሎት ይባላል። ይህ ወፍራም ነጋዴ፣ ካይሮ ውስጥ ከሚካሄደው የሃር ንግድ ተካፋይ የነበረና ሥራውን የጀመረውም ሲዶንስ በምትባለዋ የፈረንሣይ የሃር ከተማ ውስጥ ነበር። ሃብታም ቢሆንም፣ የሚያስፈልገውን ነገር በተመለከተ ሲበዛ ቆጣቢ ነው። እንደሚወራው ከሆነ፣ የወለዳቸው ልጆቹ፣ በቤት ውስጥ ለማኝ

እንኳ የሚጠየፋቸውን የተበሣሱና የተቀዳደዱ ልብሶችን ይለብሣሉ። ቅንጦትን በተመለከተ ደግሞ፣ ፍፁም አባካኝ ሰው ነበር። ሊያስከብረውና ከፍ ከፍ ሊያስደርገው ከቻለ፣ የሃብቱን መጠን ማሣወቅ ውድ አይሆንበትም ነበር። በተለይም ከፍ ማለቱንና ክብሩን ሊሠጠው በሚችለው ካይሮ ውስጥ በሚገኘው አንድ እውቅ ሰው ዘንድ ከሆነ ችግር የለበትም። ይህም ሰው ቆንሲሉ ነው።

ስለዚህም፣ ሙሴ ማይሌ፣ በሚቀጥለው ቀን የኢትዮጵያን አምባሳደር ለመቀበል በነበረው ዝግጅት ፊቱን ወደ ብሬሎት መለስ ማድረጉ፣ ሙሉ በሙሉ ተገቢ ነበር። እያደገ የሚታየውን እውቅናውን ከፍ ከፍ ከሚያደርጉለት መገልገያዎች አንዱ፣ ዳሚየታ ከተማ ውስጥ፣ ብሬሎት፣ ከአንድ የባንክ ሰራተኛ የገዛትና ጣሪያዋ ወደ ኋላ ሊታጠፍ የምትችል ውብ የእንግሊዝ መኪና ነች። ምስኪኑ እንግሊዛዊ፣ ኪሣራ ሲገጥመው ወደ ማርሴይ ሊያደርሰው በሚችል መርከብ ላይ ለመሣፈር እንባ በአይኖቹ እንደሞላ መኪናዋን ባልሆነ ዋጋ ሸጣት።

ብሬሎት፣ ለምክክር በሚል ወደ ቆንስላው ጽህፈት ቤት ከሰዓት በኋላ በተደጋጋሚ ተጠርቶ ተመላለሰ። ምሽት ላይ የተቀባዮቹ ስም ዝርዝር ተጠናቀቀ። ከፍተኛ ሰው መምጣቱን የሚያናፍሰው ወሬ በማህበረሰቡ መንደር ውስጥ ተሠራጨ። ጥቂቶቹ ፖንሴ መመለሱን ያወራሉ። ብዙ ነጋዴዎች፣ አልመሰለን አለ በሚል አኳኋን በቆንስላው ዙሪያ ማንገርበብ ጀመሩ። ነገር ግን፣ በሚቀጥለው ዕለት አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን ለመቀበል ሙሴ ዴ ማይሌ እየተዘጋጀ ስለሆነ፣ ሁላቸውም በየቤቶቻቸው እንዲቆዩ፣ በመንገድም ላይ አንዳችም መንፈስ የሚረብሽ ነገር እንዳይፈፅሙ፣ የተባለውን አምባሣደር ለመቀበል አንድ ጓድ በመኪና እንደሚወጣ፣ በዚህም ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉት በዝርዝር የተመዘገቡት ብቻ እንደሚሆኑ ሙሴ ማቼ ወጥቶ ማሣሰቢያ ሰጠ።

በሚቀጥለው ዕለት ጧት፣ ጆን ባፕቲስት በሚያስደስት ስሜት፣ ሌሊቱን ሙሉ ባገኘው ሰላማዊ ዕንቅልፍ ይበልጥ ተጠናክሮና ብቁ ሆኖ ነቃ። ያለፈውን ዕለት ሁኔታዎች መልሶ መላልሶ ፈተሻቸው። አሊስንም በጥድፊያ አለማየቱ ለበጐ ሣይሆን አይቀርምና ፍራንቾይዝ ያመጣችለት ዜና ድንቅ እንደነበረ ደመደመ። ቆንሲሉ ያደረገለትን አቀባበል በተመለከተም፣ ይጠብቀው የነበረው ነውና እቅዱ ግቡን መትቷል። ከዚህ በኋላ አቀባበል ከሚያደርገው ሠልፈኛ ጋር በትህትና ሄዶ አምባሣደር ሙራድን ይቀበላል። ከዚያም አርመናዊውን፣ አስቀድሞ በነደፈለት መንገድ እየመራ ይወስደዋል። ቆንጆ ቀይ ሙሉ ልብሱን፣ ትናንሽ



ቀዳዳዎች ያሉበት የሚመስል ንድፍ ባረፈበት ለስላሣ ሸሚዝ ላይ ለብሷል። በቁም ሣጥኑ ውስጥ አስቀምጦት የነበረውን ባርኔጣውን አራግፎ አጠለቀ። ጉራዴውን በጐኑ ላይ ታጠቀና ፈረሱን ሊጭን ወጣ።

እርሱ ቆንስላው ግቢ ሲደርስ፣ ተቀባዩ እድምተኛ ተሰብስቦ ቆይቷል። ከበላይ የሚታየው የፈረንሣይ ቆንሲላ ግቢ ሃላፊ የሆነው፣ ሙሴ ፍሌሃው ነበር። ምንም እንኳ ከሙሴ ዴ ማይሌ ጋር ተመሣሣይ የሆነ ዲፕሎማሲያዊ መደብ አባል ቢሆንም፣ በጣም ዝቅ ባለ ደረጃ የሚሠሩ ተራ የሂሣብ ሥራና ደብዳቤዎችን ከመላክ ሌላ ሲሠራ፣ ጆን ባፕቲስት አይቶት አያውቅም። ሰውዬው፣ ጥልፍ ያለበት ሙሉ ልብስ ለብሶና ላባ የተሠካበት ባርኔጣ አድርጓል። በህይወቱ እንዲህ አምሮ አያውቅም። በስተቀኙ፣ የቆንሲሉ ዋና አስተርጓሚ፣ ሙሴ ፍሬሴቲ አለ። አስተርጓሚው፣ሙያውን በከተማው ውስጥ በመለማመድ፣ የንግድ ሥራ ትርጉሞችን እየሠራ የመኖሪያ ገቢውን ያገኛል። አንዳንድ ጊዜ፣ ቆንሲሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ የትርጉም ስራ እየሠጠው በርሱና በኦቶማን ባለስልጣኖች መካከል የሚተላለፉ ኦፊሴል ደብዳቤዎችን እንዲተረጉም ሾሞታል። ከሙሴ ፊሌሃው በስተግራ፣ ለንጉሡ ተብሎ ቀሚስ በለበሰ ፈረስ ላይ፣ ብሬሎት ተቀምጧል። ብሬሎትን በፈረሱ ላይ ለማስቀመጥ ብዙ ሰዎች ተሸክመውታል። የብሬሎት ግዝፈት የመጣው፣ የሠውነት መገጣጠሚያዎችን በሚያሣብጥ በሽታ ነው። ይሁን እንጅ፣ በቡኒው ረዥም ሠው ሠራሽ ፀጉሩና በሀብቱ ምክንያት በለበሠው ሙሉ የሃር ልብስ የተነሣ፣ የመጠኑ ልኬት ጥሩ ነው። እርሱን ተከትሎ መኪናዋ አለች። ከመኪናው ውስጥ ከነጅው በስተቀር ሌላ ተሣፋሪ የለበትም። በመልስ ጉዞ ላይ ብሬሎት ከአምባሣደሩ ጐን የመቀመጥ ክብር ይኖረዋል። በመጨረሻም፣ ዝቅተኛ ጥራት ባላቸው ፈረሶች ላይ፣ በሁለት ተርታ የተቀመጡ ነጋዴዎች አሉ። የነዚህ ነጋዴዎች ምርጫ ረዥም ድርድር ተደርጐበታል። ሁለቱ ቬኒሲያውያን በዚህ አጀብ ውስጥ የመሣተፍ እድል ያገኙት አልፍኝ ታዳራሽ የሆነውን ቤታቸውን ለአቢሲኒያው ባለስልጣን ማረፊያነት ስለሠጡ ነው። የፕሮቶኮል ደረጃን በተመለከተ በተደረጉት ውይይቶች፣ አንድ ነጥብ ግን ያለምንም ጭቅጭቅ ተቀባይነት አግኝቷል። ፖንሴ የመጨረሻውን ስፍራ ይይዛል። እርሱም ይህን ቦታ በፈቃደኝነት ተቀብሎታል። ደህ አነስተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊት በአራት ሰዓት ላይ ተንቀሣቀሰ። ብዙም ሣይቆይ የመልዕክተኛውን ጓዝ ያገኛሉ። ወዲያውም ተቀባዮቹ አጅበውት፣ በቆንስላው ሠንነት ሥር በማለፍ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈር ይመለሣሉ። ሙሴ ዴ ማይሌ መልዕክተኛውን የሚቀበለው እዚያ ነው። ዲፕሎማቱ፣ የሹመት ደብዳቤውን አቅርቦ እስኪያስረክብ ድረስ ምንም ዓይነት የቅርበት ንክኪ ማድረግ

ክልክል ነው። አምባሣደሩም፣ ባሊያኖች በሚኖሩበት የፈረንሣውያን ማኅበረሰብ መኖሪያ ውስጥ «የቬኒስ ወረዳ» እያሉ ወደሚጠሩት ቤት ያመራል።

የቱርኮችን አትኩረት ሳለመሣብ ሰልፈኛው አሮጌ ካይሮን ትቶ በመክላከያ ምሽጉ ግድግዳ አቋርጦ ተጓዘ። ምክንያታቸውን ባያውቁም ደማቅ ሰልፎች ሲደረጉ፣ ቱርኮች ሁልጊዜም ይጠራጠራሉ። ሠራዊቱ የድመት በር በሚባለው መውጫ አድርጐ በአቅራቢያው ወዳለው ቀበሌ ሲደርስ፣ በምድረበዳ ውስጥ እየተጓዘ መሆኑን አወቀ። ከከተማው አጥሮች አንድ ማይል ከአሩብ ያህል ርቀት ከተጓዙ በኋላ ቆሙ። ይህ ሥፍራ ፖንሴ ከትናንት በስቲያ በጨረቃ ብርሃን በፈረስ ላይ ሆኖ የተጓዘበት የቤተመቅደስ ቦታ ነው። ቀኑ ሞቃት ነበር። ከምድረበዳው የሚመጣው ነፋስ የአቧራ ደመና ስላስነሣ አይኖቻቸውን ይቆረቁራቸው ጀመር። ብዙም በተንተን ሣይሉ፣ የእድምተኛው አባላት ጥላ በመፈለግ መዝናናት ጀመሩ። የአገሩ እይታ ያልተለመደ ዓይነት ነው። ከወደምድረ በዳው በኩል በነፋስ እየተጠረጉ የተፈጠሩ ታላላቅ የግሪክ ምስሶዎች ሽቅብ አስግገው ይታያሉ። ከበስተኋላቸው ደግሞ በፈረሶቻቸው ላይ በፀጥታ የተቀመጡና እንቅስቃሴ አልባ የሆኑ ፈረሰኞች፣ በሣብታም ልብሶቻቸውና በረዣዥም ሰው ሰራሽ ፀጉሮቻቸው ሥር በላብ ተዘፍቀው ይታያሉ። ጥቂቶቹ አድማሱን ባለማቋረጥ ይመለከታሉ። ሌሎች ደግሞ ራሱ ላይ ጥምጣም ያደረገ ሽማግሌ እረኛ ያለ ዓላማ የሚነዳቸው በጐች ያንጠባጠቧቸውን ጥቋቁር በጠጦች በመቁጠር ትኩረታቸውን በዚያ ላይ አድርገዋል።

ጥበቃው በመቀጠሉ፣ ምናልባት አስቸጋሪ ጥያቄዎች ያቀርቡ ይሆናል በሚል፣ ፖንሴ ስለተጨነቀ ከፊት ለፊት ያለውን መንገድ ለመቃኘት እንዲቻል ሃሣብ አቀረበ። ፈረሱን ኮርኩሮ ለአንድ ሰዓት ያህል ጋለበና ምንም ሳያይ ቀስ እያለ እየሰገረ ተመለሰ።

የዕለቱ ከሰዓት በኋላ፣ በሰላም እየተገባደደ ነው። ባለስልጣኖቹ ከፈረሶቻቸው ወርደው የደረቧቸውን ኮቶቻቸውንና ጃኬቶቻቸውን አውልቀው በሸሚዞቻቸው ሆነው፣ በውሃ ጥም ተቃጥለውና ቁጣቸውን ሊሰነዝሩበት ተዘጋጅተው አገኛቸው።

«ሊገባኝ አልቻለም፣አንዳች አስቸጋሪ ነገር አጋጥሞ መሆን አለበት።» አለ።



በዚህ ጊዜ ሌሎች፣ ሌላው ቀርቶ አምባሣደር የተባለው ሰው ከቶውንም ስለመኖሩ መጠራጠር መጀመራቸውን ተረዳ። እነርሱ ሰውዬውን ስለማያውቁት ቢጨነቁም፣ ፖንሴ ግን ስለሚያውቀው በሌላ ምክንያት የሙራድ እጣ ፈንታ አሣሰበው።

«አሁን አሥር ሰዓት ሆነ፣ ወደ ቤት እንድንመለስ ሃሣብ አቀርባለሁ። ምናልባት መልዕክተኛው በምሽት የሚደርስም ከሆነ ጠብቀው እንዲያሣውቁን ሁለት ጠባቂዎችን እንልካለን» አለ ጆን ባፕቲስት።

ባለው ሁኔታ ምላሹ ጥሩ እንደማይሆን ስለተረዳ ላቀረበው ሃሣብ የሚሰጠውን ምላሽ ሳይጠብቅ ፈረሱን ኮርኩሮ ወደ ካይሮ ነጐደ።

# 4

በተሰይ በዚያን ዕለት፣ የድመት በር የሚባለውን የሚጠብቁት ሁለቱ ተረኛ ሽማግሌ የአረብ ዘቦች፣ ሰውነታቸው ሁሉ በክብር ምልክቶች ተሞልቶ፣ በጣም ተደስተው ነበር። የሚሊሺያዎች አዛዥ፣ ለወታደራዊ ጀግንነታቸው ምስጋናውን ለማሳወቅ፣ በዚህ ሰላማዊ ጣቢያ ላይ ሕይወታቸውን ሙሉ እንዲቆዩ ፈቅዶላቸዋል። በዚህ ጊዜ፣ ካይሮ ከውጭ ከሚያጋጥማት ወረራ ይልቅ የውስጥ የሕዝብ አመፅ ይበልጥ ያስፈራት ነበር። በየበሩ ያሉት ዘበኞች ዋናው ሃላፊነታቸው፣ በምሽት፣ ጅቦችና ሌሎችም አራዊት ከምድረበዳው ተነስተው ወደ ከተማ እንዳይገቡ በሮችን መዝጋት ነው። ቀን ሲሆን ግን፣ ሁለቱ ሽማግሌዎች ከመሬት በታች ባለው ጥላ ቦታ ላይ ምንጣፋቸውን ዘርግተው፣ እግሮቻቸውን አመሣቅለው በመቀመጥ ቼዝ ሲጫወቱና በቅርባቸው ካለ ሱቅ አንዲት ባዶ እግሯን የሆነች ትንሽ ልጅ የምታመጣላቸውን ሻይ እየጠጡ ይውላሉ። ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን በሕዝብ ትርምስ መሃል ሰፊ ቦላሌና እንደ ኩርዶች አለባበስ ሰፋ ያለ የወገብ መታጠቂያ የለበሰ ሰው ወደ ከተማዋ ሲገባ ያያሉ። ሰውዬው ሥጋው የደለበና በምስኪኗ በቅሎው ላይ ከባድ ጭነት ነበር። እንስሳይቱ፣ ወደ በሩ ከሚያመራው መውጫና መውረጃ መሃል ስትደርስ ቀጥ ብላ በመቆም አንዲት እጥቅ እንኳ ላለመንቀሳቀስ አሻፈረኝ አለች። ሰውዬው፣ በፍጥነት ተንቀሣቅሶ ብዙ ቦታ ስብርብር ባለና በቅሎይቱን ሊያስገድዳት በማይችል በደካማ እርፖሜ ይገርፋት ጀመረ። ማንም ሰው ኑበያዊ ናቸው ሊል የሚችላቸው፣ነገር ግን ቀርፃቸው ለየት ያለ፣ ሦስት ጥቋቁር ሰዎችም የበቅሎይቱን ውዴላ ይዘው ቢገፏትም እንስሳይቱ በቁጣ እነርሱ ላይ ተሽከርክራ ዞረችባቸው። የመጨረሻው ጥረታቸው ግን እንስሳይቱ እስከነአካቴው እንዳትተናኛባቸው መጠበቅ ሆነ። በዚያው መስመር ፈንጠር ብለው በሰላም አብረው የተቆራኙ ሦስት አህዮች እምቢነገር ተጭኖባቸዋል። ሌላ አንድ በቅሎም እንደሁ በመንገዱ ዳር ባሉት ድንጋዮች መሃል ብቅ፣ ብቅ ያሉትን ስለታም ሣሮች ትመለከታለች።

በመጨረሻም ሰውዬው ከበቅሎይቱ ላይ ወረደና ወደ በር ጠባቂዎቹ ተራምዶ ፊት ለፊታቸው ሲደርስ ቆመ። ከበቅሎው ወርዶ አስር እርምጃዎች በመራመዱ ቀና ቀና ይተነፍሣል።



«እ! ውድ ወዳጆች፣ ወንድሞች» አለ እያለከለከ «ይህች በቅሎ እዚህ ድረስ እንድትራመድልኝ ልትረዱኝ ትችላላችሁ። ዕድሜዋን ሙሉ በከተማ መግቢያ በር አልፋ የማታውቅ እንስሳ ነች። በጣም ስለፈራች ምንም ዓይነት ምክንያት ማዳመጥ አትፈልግም»

ሰውዬው የሚናገረው አረብኛ የሶርያ ዘዬ ነው

«እንዲያው ለመሆኑ እናንተ ከወዴት ናችሁ? በከተማችሁ መግቢያ፣ በሮች የሏችሁም?» ሲል አንዱ ዘበኛ ጠየቀ።

«እኔ የመጣሁት፣ አናቶሊያ ከሚገኘው ከቫን ከተማ ነው። በዚያም ብዙ በሮች አሉን። ነገር ግን እኔና በቅሎዬ ሁለት የተለያየን ነገሮች ነን። ይህችን በቅሎ የገዛኋት አረቢያ ከሚገኘው ፊሊክስ፣ ከአንድ ባላገር ላይ ነው።»

«አሃ! እንግዲያውስ ማንበብ የማትችለው በቅሎይቱ ነች ማለት ነው!» አለ ሽማግሌው በሣቅ እየተንከተከተ

ሁለተኛው ሽማግሌ፣ የተሰጠው አስተያየት ምን አስቂኝ ነገር እንዳለበት እርግጠኛ ባይሆንም፣ በጓደኛው በሣቅ መንከትከት ተሸንፎ አብሮት መንከትከት ጀመረ። መንገደኛው፣ ሁለቱም ሰዎች ሲስቁ ተመልክቶ፣ እርሱም አብሯቸው ቢስቅ መልካም እንደሚሆን አሰበ፣ የሃር ጥምጣሙ ከጭንቅላቱ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ከልቡ ፍርስ አለ።

«ከዚህች ማንበብ ከማትችል እንስሳ ጋር እንግዲያውስ ወዴት ነው የሚሄዱት?» ሲል የመጀመሪያው ሽማግሌ ጠየቀ። ሣቁ ጣሪያ የሚደርስ ስለነበረ በአካባቢው የነበሩ ተላላፊዎች ቀልዱን ለመካፈል ተሰበሰቡ።

«ወደ ፈረንሣውያን ቆንሲል» አለ መንገደኛው

«እሃ! ምናልባት በቅሎዎ ላቲንኛ ማንበብ መቻልዋን ለማወቅ ፈልገው ነው!» አለ ሌላኛው ሽማግሌ። በዚህም ሁለተኛ ዙር ሣቅ ሲቀጥል፣ ባለ በቅሎውም በደስታ የሣቃቸው ተካፋይ ሆነ።

ፀጥታ እስኪሰፍን ድረስ ሁለት ወይም ሶስት የተለያዩ ጉዳዮች በዚህ ዙሪያ ሲያጫውቷቸው ቆዩ። በር ጠባቂ ዘበኞችም በተጨማደዱ አይኖቻቸው ላይ የተጠራቀሙትን

በመምጣት እንዲህ ያለ ነገር ዳግመኛ እንዲያከናውኑ እንዳይገደዱ ሲነግሩት ተጣደፉ። የተቀበሉቸውና ያስተናገዱቸው እንዲህ ያለ ቀርፋፋና ባለጌ የንጉሡ ባለሥልጣን መሆኑ ሲያምኑት ከሚችሉት በላይ ነው። ቆንሲሉ ላይ አንዳችም የመከነን ነገር ሣያሣርፉ፣ ፖንሴን የማጭበርበር ስራ ሰርቷል በሚል ከሰሱት። ይህን አይነት አስደንጋጭ ትዕይንት እየተከናወነ ሣለ፣ የብሬሎት ተወካዮች ተመለሱና ሁሉም በፖንሴ ላይ ቁጣቸውን አወረዱበት። ምን እንዳጋጠመ ከተረዱ በኋላ የሴለን መልዕክተኛ እንዲጠብቁ ያደረጋቸውን መድሃኒት ቀማሚውን መክሰሳቸውን አቁመው፣ ቅሬታቸውን የሚያስተካከልላቸውን መዝናኛ ተቀሳቀሱ። በወቅቱ ሰፍኖ የነበረውን ትርምስ በመጠቀም ጆን ባፕቲስት ከቆንስላው ሾልኮ ወጣ።

«ክቡራን፣ ፀጥታ» አለ፣ ቆንሲሉ፣ ከፍ ባለ ድምፅ። «ከዚህ በኋላ ከድካማችሁ አረፍ እንድትሉ እጠይቃለሁ። በተጨማሪም ለድጋፋችሁ አመሰግናችኋለሁ»

ሌላ የተቃውሞ ጫጫታ ተቀሰቀሰ። ቆንሲሉ በአካላዊ እንቅስቃሴው አበረዳቸው።

«ይህ ሰው የአንድ ታላቅ ንጉስ መልዕክተኛ ነው። በርግጥ ንጉሡ ለብዙ ዘመናት ከስልጣኑ ተቆራርጦ ኖሯል። ቸርነታችንንም ማሣየት ያለብንም ለዚሁ ነው። ከሁሉም ነገር በላይ የዚህ መልዕክተኛ እዚህ መድረስ በራሱ ትልቅ በዓል ነው። መልዕክተኛው በማንኛውም መልኩ ከያዘው መልዕክት በታች የሚገመት ነው። የአቢሲኒያው ንጉሥ ምን እንደሚነግሩን ነገ እንሰማለን። »

ቆንስላውን ከለቀቀ በኋላ፣ ፖንሴ፣ በቀጥታ ወደ ቬነስ ወረዳ ሙራድን ለማየት ሄደ። የቬነስያውያን የእንግዳ መቀበያ ክፍል መቀመጫዎች በሙሉ በግድግዳው የውጭ አካል በኩል በሙራድ ትዕዛዝ እንዲከመሩ ተደርጓል። በነጋዴው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ የቀሩት፣ ምንጣፎችና ከባለመደገፊያው ወንበር ላይ ወርደው ወለሉ ላይ የተበታተኑት ትራሶች ናቸው። ሙራድ፣ እግሮቹን አጣምሮ፣ በመስተዋት ጨሌ በተጌጠው በትልቁ መብራት ሥር፣ ብዛት ባላቸው የብር ትሪዎች፣ አብረቅራቂ ጉድጓዳ ሣህኖች፣ ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው ማንቆርቆሪያዎች ተከብቦ ተቀምጧል።

ጆን ባፕቲስት፣ የበቅሎዋን ባህርይና ባልታሰበ መንገድ የመጣበትን ታሪክ እንዲያወጋው ጠየቀው። የፈረንሳውያን ማህበረሰብ እንዴት እንደተቀበለው የሙራድን ሃተታ ሰማ። ሁሉም ነጋዴዎች አስነዋሪ ብልግና ያሣዩት መሆኑን አርመናዊው ይገምታል። ከእንግዲህ በኋላ እቤቱ ዳለ እድርጉ እንዲገምትና ስጦታዎችንም ካበረከተለት በኋላ ሁለቱም ያንን ማንጓጠጥና



ብልግና ሊያረግቡና ይህን ንብረት እንዴት እንደሚጠቀምበት ተወያዩ። ምንም ነገር እንደሚፈልጉት አልነበረም። በአትክልቱ ሥፍራ ያሉት በቅሎዎች ወይም ከክፍሉ የተነሣው የቤት ውስጥ ቁሳቁስ፣ ወይም በአቢሲኒያውያን ስልት ፊት ለፊት ባለው መድረክ ላይ በሚገባ በተቀጣጠለው እሣት ላይ የፈላው ቡና እንደሚፈልጉት አልነበረም።

የሙራድን ቁጣ ባባባሰው በዚህ ታሪክ ከልብ ከሣቀ በኋላ፣ በፀባዩ ላይ አንዳችም ነገር እንዳይለውጥ ጆን ባፕቲስት ነገረው። በሚቀጥለው ቀን ከቆንስላው የሚመጣ ሰው አግኝቶት ስለሹመት ደብዳቤው ቢጠይቀው፣ ምን ማለትና ማድረግ እንደሚገባው በጣም ግልፅና ትክክለኛ የሆነ መመሪያ ሰጠው።

ከዚህ በኋላ፣ ጆን ባፕቲስት ወደ ቤቱ ፈጥኖ ሄደ። ከአሊስ፣ በአንድ ወይም በሌላ መልክ መልዕክቷን ይጠብቅ ነበር። ከትናንት በስቲያ ጀምሮ ስላላያት፣ የሚያስበውም ይህን ብቻ ስለነበረ በጣም ጓጉቷል።

ፎቁን በጨለማው ውስጥ ወጣውና ሻማውን አበራው። እንደገመተውና እንደጠበቀውም አራት ቦታ የታጠፈ መልዕክት በሻማው ሥር አገኘ። መልዕክቱ ከፍራንቾይዝ የተላከ ማስታወሻ አልነበረም። ማስታወሻው የቤተክርስቲያኑ ደወል ሁለት ጊዜ እንደተደወለ በማህበረሰቡ ዋና መንገድ መጨረሻ ላይ ባለው የአትክልት ሥፍራ እንዲያገኛቸው የሚያዝዝ ነበር።

# 5

አሊስ፣ በጨለማው ክፍሷ ውስጥ ቆማ የቀጠሮውን ሰዓት ትጠብቃለች። በዚያ ምሽት፣ ብርማዋ ጨረቃ ፣አልፎ አልፎ በከባድ ደመና እየተጋረደች አለች። እንዲህ ባለ ድቅድቅ ጨለማ ሌሊት እስከመናፈሻው ድረስ በመንገዶች ላይ መጓዝ እንደማያስፈልግ ፍራንቾይዝ አሰበች። በዚህም፣ ከቆንስላውና ከሰላዮቹ ቢያንስ ትንሽ ራቅ ይላሉ። ገና አመሻሽ ሲጀምር፣ ወጣቷ ልጃገረድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ከበቂ በላይ ጊዜ ስለነበራት፣ ወደዚያ ወደተባለው መገናኛ መሄድ የጅል አስተሣሰብ እንደሆነና ክብሯንም ዝቅ እንደሚያደርግባት ለራሷ ስትነግር ቆየች። ሰዓታት እያለፉ ሲሄዱ ግን እርሷም ይህን ሃሣቧን ልክ እንደ ሌባ ሲያጠቃህ ሲመጣ ገፍትረህ ግርግዳ ላይ እንደምትወረውረው ሁሉ አሽቀንጥራ ጣለችው። ለራሷም እንዲህ አለች። ለመሆኑ በሙሉ ልቤ አላፈቅረውም?

ከዚህ ውሳኔዋ በኋላ፣ ቀጠሮውን አፈርሣለሁ ከሚለው ሃሳቧ ይልቅ፣ አከብረዋለሁ፤ በሚለው ውሣኔዋ ርግጠኛ ነበረች። በአሁኑ ጊዜ በአዕምሮዋ ውስጥ የሚመላለስባት የክርክር ነጥብ፣ የጥንቱ የዕድገትዋ ጉዳይ ሣይሆን፣ ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ራሷ ያገኘችው የአሁኑ አዲሱ ፅኑ እምነትዋ ነበር። ከፍራንቾይዝ ጋር በተጨዋወተችባቸው ረጅም ወራት ውስጥ፣ በጥቅም ሣይሆን በጥልቅ የስሜት ፍቅር የሚመራውን የእውነተኛ ፍቅርን ክብር ተገንዝባዋለች። ክብርን በተመለከተ ከሆነ፣ በሚገባ ልትጠብቀው የቻለችው እናትዋ ጥሩ ምሣሌ ናት። እርሷ ግን፣ እንደራሱ የግል ንብረት ሳደረጋት ሰው ባሪያው ካልሆነች ምን ልትሆን ነው? ልብሷን እየለበሰች ይህን የመሰሉ አደገኛ ሃሣቦች፣ በአሊስ አዕምሮ ውስጥ አለፉ። ይህ ሁሉ ግን በፍራንቾይዝ የማነሣሣት ተፅዕኖ የመጣባት ሃሣብ ነው ብሎ ማሰቡ ትክክል አይሆንም። ሁለቱ፣ በማድቤቱ መግቢያ በኩል ተሹልከው ከወጡና በመንገዱ ላይ ካለው ጭለማ ጋር የራሣቸውን ጥላ ካመሣሰሉ በኋላ፣ አሊስ የደስታ እንቅጥቃጤ ተሰማት። ይህ መንቀጥቀጥ የተፈጠረባት እያደረገችው ባለው ነገር ሃሣብ አልነበረም። ይልቁንም በጉዳዩ ላይ ያለው ጥልቁ የተግባር ዕውቀት፣ አሁን እያከናወነችው ያለው ተግባር፣ አደጋ፣ ምናልባትም የመስዋዕትነት መልክ ያለው አደጋ፣ ፍፁም እውነተኛ የሆነና በሥልጣኔ ቅንጣት ታህል ያልተሸፈነ፣ በአጭሩ፣ የርስዋ እውነተኛ ባህሪ የፈጠረባት ነው።



መገናኛውን እየጠበቀ፣ ጆን ባፕቲስት በትውስታ ወደ ኋላ ተመለሰ። ሁልጊዜም ቀላልና ብልጭ ብሎ የሚያልፍ የፍቅር ግንኙነቶች እንደነበሩት ትዝ አለው። ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያ ግንኙነቱ እንደሚታወቀው ሁልጊዜም የመጨረሻ ይሆናል። የውድድር ዓይነት ትርዕ ነበረው። የውድድሩ ተሣታፊዎች እያንዳንዳቸው ግልፅ የሆነ ለማሸነፍ ወይም ለመቋቋም ያለመፈለግ ቅዝቃዜ ይታይባቸው ነበር። በመሆኑም ጨዋታው የተቻለውን ያህል ለረዥም ጊዜ ከመደባበቅ ባለፈ እውነተኛው ሃሣብ ሣይገለጥበት ቀረ። ይህ ከሆነ በኋላ እያንዳንዱ በጥልቀት ያለውንና ሌላኛው ሰው ምን እንደሚሰማው ማወቅ ቻሉ። የማሸነፍ ወይም የመተው ጥያቄ አልነበረም። መደረግ የነበረበት በውስጣቸው ተፀንሶ የነበረውንና ለረዥም ጊዜ አውግዘውት የነበረውን ፍቅር፣ ለዓለም ግልፅ ማድረግ ነበር። መደረግ የነበረበት፣ ቃላትና የሰውነት እንቅስቃሴዎች የሚያስተጋቡትን ፍቅር ፍንትው አድርገው በአየር ውስጥ በግልፅ ማሣየት ነበር። ይህን የማድረጉ ሃላፊነት ገልጃጃ እንዳደረገው ተሰማው።

ሰዓቱ በጭለማው ውስጥ ሁለት ጊዜ እንደደወለ፣ ሁለቱም ፍቅረኛሞች ወደመገናኛው አቀኑ። አሊስና ፍራንቾይዝ፣ ከመግቢያው በስተግራ በኩል ሲደርሱ፣ በአትክልት ስፍራው በስተጀርባ ተሸሽጐ የነበረው ጆን ባፕቲስት፣ ከውስጥ በኩል ብቅ አለ። ሁለቱም እንክት በሚልና ሊጠገን በማይችል ውድ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ መስሎ ተሰማቸው። ይህ ደግሞ የተገነባውን ቃል ኪዳን በማመልከቱ አይደለም። ምክንያቱም፣ ቃልኪዳኑ ከረዥም ጊዜ በፊት የተፈፀመ ነው። ነገር ግን ዳግመኛ አይፈፀምም የሚል ስጋት ስላላቸው ነው። እያንዳንዳቸው በየበኩላቸው፣ ይህ ጊዜ በተቻለ መጠን ረዥም እንዲሆን ለማድረግ፣ ልክ ዳግመኛ ሊታዩት የማትችሉትን ሰው መልክ በህሊናችሁ ቀርፃችሁ ለማኖር እንደምትሞክሩ፣ እነርሱም በትዝታ ኅዳቸው ውስጥ መስርተው ሊያኖሩት ቁርጠኞች ነበሩ። በአጭሩ፣ ግንኙታቸውን በመጣደፍ ሊያሣጥሩት አልፈለጉም። ይሁን እንጂ አካላዊ ጥላዎቻቸው እርስ በእርስ መቀራረባቸውን ሲመለከቱ፣ ሁለቱም ብቻቸውን በነበሩበት ጊዜ ውሣኔአቸው ትቷቸው ጠፋ። ተለያይተው የቆዩበት ጊዜ ረዥም ነበር። ጭለማውና ሰው በሌለበት ቦታ ያደረጉት ግንኙነት ጉጉታቸውን ጨመረው። ፍላጐት አጠጋጋቸው። ወዲያውኑ ተቃቀፉ። እርስ በርሣቸውም በመሣሣም ተሸፋፈኑ።

«ምን ያህል ደስ እንዳለኝ» አሉ፣ ተራ በተራ።

«ፍቅሬ፣ ፍቅረኛዬ» ስትል፣ የጆን ባፕቲስትን ፊት በመሣም እየሸፈነችው፣ አሊስ አጉተመተመች:: «ምን ያህል ደስተኛ እንደሆንኩ ብታውቅ፣ አፈቅርሃለሁ:: በዚህ ሁኔታም ሁል ጊዜ መሆንን እፈልጋለሁ»

የጊዜ መጉተት አስቸጋሪነት ሃሣብ በውስጥዋ በመኖሩ፣ ትጀምረውና መልሣም ከጆን ባፕቲስት ራስዋን በመጠኑ ትገታዋለች:: በእንባ በሚንፀባረቁ ውብ ዐይኖችዋ ተመለከተችውና ዝቅ ባለ ድምፅ አናገረችው::

«ወደ ቬርሣይለስ መቼ እደምትሄድ ከዚያም ደግሞ መቼ ተመልሰህ መጥተህ፣ ይዘኸኝ እደምትሄድ ንገረኝ»

«እህ» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ፊቱን በመጠኑ ኮር በማድረግ

«ምንድን ነው?»

« ሁሉም ነገር ተወሳስቧል:: ወደ ቬርሣይለስ የሚደረገውን ጉዞ ቱርኮች ይቃወሙታል በሚል፣ አባትሽ ወሬው እንዲነሣ አይፈልጉም:: በርግጥ፣ እኛም ነገሮች በትክክል እንዲሣኩ ያደረግነው ጥረት የለም:: ሙራድንም፣ ምን ዓይነት እንደሆነ አይተሸዋል»

« ይህ ማለት ታዲያ . . . ያ ሁሉ ተስፋችን ለዚሁ ፍሬ ቢስነት ነው?»

« አይደለም!» አለ ጆን ባፕቲስት እጆችዋን ጭምቅ እያደረጋቸው፣ «እኔ ተስፋካደረግሁበት ይልቅ አስቸጋሪና ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል ማለቴ ነው»

ጆን ባፕቲስት፣ ዓላማቸው ሁሉ አለመሣካቱን በቀላሉ ለመቀበል አልፈለገም:: ተስፋ የሚያደርግበትን አቅጣጫ ሊለይ ባይችልም፣ በዚያች ሰዓት በአሊስ ፊት ቆሞ ተስፋ ቆርጦ መተው ማለት፣ ከመሸነፍ ይልቅ የባሰ ጥላቻና ተቀባይነትን ማጣት እንደሚሆን ተሰማው::

እነርሱ ካሉበት ቦታ በቀጥታ ከታች ካለው ምድር ቤት መውጫ መድረክ ላይ፣ ጥንዶች በብዙ ቁጥር እየሆኑ በመውጣት ላይ መሆናቸው፣ ደህና ሁኑ እያሉ ከፍ ባለ ድምፅ መሰናበታቸውና የማያቋርጥ የምስጋና ቃላቶቻቸው ድምፅ ይሰማል::

«ስማኝ» አለች አሊስ:: «ብዙ ጊዜ የለንም:: የመጨረሻው ሰረገላ ተንገፍን ሲያሣፍር አንተም መሄድ ይኖርብሃል»



ይህን ተናግራ እንደገና ሳመችውና ቀጠለች

«አንዳች አጣዳፊ ነገር በዚህ ጉዳይ ላይ እንደገባ ደግሞ እንድታውቅ»

«ምን ማለትሽ ነው?»

«አባቴ . . . አ! ይቅር፣ እንድታውቅ አልፈልግም:: ነገሮችን ማወሳሰብ ምንም ፋይዳ የለውም»

«ግዴለም፣ ንገሪኝ»

«ባለፉት ሦስት ቀናት አባቴ ባለማቋረጥ ከፈረንሣይ አንድ ሰው ተልኮለት እንደሚመጣ እየተናገረ ነበር:: ሰውዬው ዲፕሎማት ሲሆን ሮሴታ ወይም ዳሚየታ ውስጥ እንደሆነ ተረዳኘ እንጂ፣ የቆንሲል ሥልጣን የሚጠሰው ነው»

«እናስ?»

«እናማ፣ አባቴ ስለዚህ ሰው ብዙ ጊዜ ይናገራል:: ስለ ትውልዱ ታላቅነት፣ ስለ አስተዳደጉ፣ ስለ ወደፊት ዕድሉ፣ ወደ እኔ በአትኩረት እየተመለከተ ያወራል:: በርግጥ እስከአሁን በግልፅ የተናገረው ነገር ባይኖርም፣ እናቴ እንደነገረችኝ ከሆነ ግን፣ አባቴ በሆነ ጊዜ ሊድረኝ እያሴረ ነው:: አባቴ፣ ዘመዳችን የሆነውን ሚኒስትር፣ እርሱ የሚፈልገውን ዓይነት የሆነ ጨዋ ሰው እንዲልክለትም ጠይቆታል::»

« ታዲያ . . . አንቺ ይህን ሁሉ እንዴት ታስቢዋለሽ?» አለ ፖንሴ::

«እኔ የማስበው፣ ፍቅረኛዬ፣እኔማ አንተንና አንተን ብቻ ነው የምፈልግህ:: ስዚህ ስሚባለው እንግዳ ሰው ከአሁኑ ጥላቻ እያደረብኝ ነው»

«ለመሆኑ እዚህ መቼ ይደርሣል ተብሎ ነው የሚጠበቀው?»

«በአሁኑ ጊዜ በጉዞ ላይ እንደሆነ ነው የሚገባኝ»

ጆን ባፕቲስት ፊቱን ቋጠረ::

«ስሚኝ» አለ ሰውነቱን ሰብሰብ እያደረገ

ጆን ባፕቲስት በጓደኛው አስተያየት ተደስቶና እንደማይቃረነው በማወቅ፣ ወደ ሜትር ዠረሚ ራመድ አለ፡፡ ጓደኛውም ወደርሱ ተራመደ፡፡ ሁለቱም ለወዳጃዊ አለመግባባታቸው ፅዋቸውን አነሱ፡፡ ቬጋው እነርሱን ቁልቁል ሲመለከታቸው፣ የካይሮ ውሾች በከፍተኛ ድምፅ ይጮሃሉ፡፡

ወ

በቀንስላው ግቢ እራቱን ከበላ በኋላ፣ ሙራድ ከፉኛ የራስ ምታት አምሞት ነበር፡፡ ይህም በመጠጡ ሳቢያ ቢሆንም፣ እርሱ ግን በምግቡ ላይ ያሳብብ ነበር፡፡ ከያንዳንዱ የመጠጥ ዓይነት በዛ ያለ ናሙና በመቅዳት፣ በጠረጴዛው ዙሪያ የተቀመጡት ሁሉ አሣፋሪ ነው እስኪሉት ድረስ የሻምፓኝ፣ የባርጋንዲና የመራራ ቅልቅል በአንድ ብርጭቆ ውስጥ በመሥራት ጠጥቷል፡፡

ከሁሉም ነገር በላይ፣ በየማለዳው ፀጉሩን በሰባራ መስተዋት የሚላጨው ኢትዮጵያዊው ባሪያ፣ የሙራድን አናት በምላጭ ሲላጨው ገሽልጦታል፡፡ ሙራድ፣ ለብረት ምላጭ ጥላቻ አለው፡፡ የደረቀ የደም ጠብታ በጥምጣሙ ስር ይታያል፡፡ ከጧቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን፣ ፖንሴ ወደርሱ መጥቶ፣ የጀስዊቶች ቃል አቀባይ እንዲመጡ እንደላከባቸውና ከጥቂት ጊዜ በኋላም እንደሚደርሱ ነገረው፡፡ የንጉሥ ነጋሲን ቃል ያልረሣው ሙራድ በመጀመሪያ ላይ ተበሣጨ፡፡ በኋላ ግን ፖንሴ እቅዱን ሲያብራራለት የመፅናናት ስሜት ተሰማውና ስለ ሆድ ህመሙ ይጠተውት ጀመር፡፡

አባ ፕላንቴይን፣ ከተባለው ሰዓት ጥቂት ቀደም ብለው ደረሱ፡፡ ከሙራድና ከፖንሴ ፊት ደርሰው እንደቆሙ፣ አምባሣደሩ ባመለከታቸው መሠረት፣ ልክ አንድ ግዙፍ በሬ ፍፁም እንክትክት ብሎ እንደሚወድቅ ዓይነት በምንጣፉ ላይ ሰመጡ፡፡ ሙራድ፣ በጨዋ የሲቪል ባህርይ ቡናና ኬክ ጋበዛቸው፡፡ ጀስዊቱም ተቀበሉ፡፡ ግብዣውንም በስልፍ የቆሙት ሦስቱ ኢትዮጵያውያን ባሮች ከጥቂት ጊዜ በኋላ አቀረቡ፡፡

አባ ፕላንቴይን፣ እነዚህን ሦስት ኢትዮጵያውያን ባሮች እንደተመለከቷቸው ወዲያውኑ በጉልበታቸው ቆሙ፡፡



«አምላኬ ሆይ! እንዴት ቆንጆዎች ናቸው!»

ሦስቱን ይመራ የነበረው የሁሉም ታላቅና እግረ ቀልማማው ሲሆን፣ እርሱን ተከትሎ በዕድሜው ሁለተኛ የሚሆነውና በሚያስጠላ መልክ ጠንጋራ የነበረው ነበር፡፡ ከሦስቱ ወጣት የሆነውና የራስ ፀጉሩ ሁሉ በጭርት ሙልጭ ብሎ ያለቀበት ልጅ በመጨረሻ ነበር፡፡

«እንደዚያ ነው የሚያስቡት?» አለ ሙራድ በረድፍ ያሉትን አሣዛኞች እየተመለከተ፡፡

«መንፈሣቸው ይታየኛል» አሉ ቄሱ፣ ዓይኖቻው ረጥበው፡፡ ማርያም ድንግላዊት እንዲባረክ ለመረጠችውና በዋሻ ውስጥ ለነበረ የበግ እረኛ በርህራሄ እንደተገለጠችለት ዓይነት፣ ትኩር ብለው ተመለከቷቸው፡፡

«እንዲህ ከሆነም መልካም፡፡ ንጉሱም እንደዚህ ያለ ዕይታ ስለነበራቸው ዕድለኛ ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስት አገልጋዮች፣ ለንጉስ ሉዊስ 14ኛ ከታሰቡት ገፀ በረከቶች መሃል ናቸው» አለ ፖንሴ

ሦስቱ ባሮች እያነካከሱ ወደ ማድ ቤት እስኪመለሱ ድረስ፣ አባ ፕላንቴይን አይኖቻቸውን ከነርሱ ላይ አልነቀሉም፡፡

«ንጉሥ ነገስቱ፣ ለፈረንሣይ ንጉስ ከላኳቸው ገፀበረከቶች መሃል ናቸው ነው የምትለኝ? ሰመሆኑ ሌሎችም አሉ?»

«እንዴ፣ አባቴ፣ በርግጥ አሉ እንጂ፡፡ ያውም ግዙፍ የሆኑ ናቸዋ» አለ ጆን ባፕቲስት

ቄሱ የተመለከቱትን እንደዚህ ያለውን ስጦታ ሊያስንቅ የሚችል ገፀበረከት ለማሰብ ቸገራቸው፡፡ ፖንሴ የማወቅ ጉጉቱን እያጠናከረ፣ ቀስ ብሎ ኪሱን ከፈተና ደብዳቤ መዘዘ፡፡

«እንደ ዕድል ሆኖ ይህ መልዕክት ከፓሻው ፖሊሶች ዕይታ አመለጠ»

«መልዕክት? መልዕክት ከፓሻው ፖሊሶች ዕይታ አመለጠ»

«በራሣቸው ፀሐፊ፣ እራሣቸው በቃላቸው እየነገሩት የተከተበና የታተመ ነው»

«የሚከታተሏችሁ ነበሩ» ሲል ጆን ባኘቲስት ለአሊስ ሹክ አላት።

እነዚህ ቃላት በልቧ ውስጥ ሽብር ነዙባት። በበሩ አጠገብ ትጠባበቅ የነበረችው ፍራንቾይዝም፣ ያንን ጥላ ተመልክታዋለች። ከዚያም፣ ወደጥንዶቹ ስትቀርብ ጆን ባኘቲስት ሲያስጠነቅቅ ሰማችው። ምናልባት ክፉ ነገር ቢያጋጥመኝ እከላከልበታለሁ በማለት አስቦ፣ ፖንሴ ከቤቱ ሲወጣ በቀበቶው ላይ ፖቤ ታጥቆ ነበር። የፖቤውን እጀታ በፍጥነት ይዞ፣ ያቀደውን፣ ለሁለቱ ሴቶች ነገራቸው።

«ሲከታተላችሁ የነበረውን ሰው ተጋፍጬ ማንነቱን አጋልጣለሁ። ሁለታችሁም ወደ ቆንስላው በፍጥነት ተመለሱ። ነገር ግን እንዳትታዩ እየተጠነቀቃችሁ እንጂ እየሮጣችሁ እንዳትሄዱ። ለመሆኑ የጓሮውን በር ቁልፍ ይዛችኋል?»

«አዎን» አለች ፍራንቾይዝ

«እንግዲያው በጓሮ በኩል ዞራችሁ ሂዱ። ከዚህ በበለጠ ዋናው ቁምነገር ልክ እቤት ከገባችሁ በኋላ፣ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ የወሰዳችሁ ለማስመሰል ሞክሩ። ምናልባት ነገሮች. . .»

«ሂድ፣ ስለሌላው አትጨነቅ» አለች ፍራንቾይዝ

ጆን ባኘቲስት፣ አሊስን በችኮላ ሳማት። የከንፈሮችዋን ጣዕም፣ ልስላሴያቸውን፣ በዓይኖችዋ ውሃዎች ውስጥ የነበሩትን ዕይታዎች በጥልቁ ማስታወሻው ውስጥ ጠብቆ ሊያቆያቸው እንዲችል አጥብቆ፣ ቀመሳቸው። ከነገ በኋላ ለሚቀጥሉት ረዥም ወራት ጠብቆ የሚያቆየው፣ ይህን ብቻ ነው። ከዚያም፣ ራሱን ከርስዋ ለይቶ ጨለማው በጣም ከባድ ወደነበረበት የአትክልት ሥፍራ አቅጣጫ ሮጠ። በፍርግርጉ በር ዞሮ በአንድ የእንጨት በር መግቢያ በኩል ዘለቀ። በዝግታ ወደ ሰፊው ጎዳና ጥግ በማምራት፣ በአንድ ነጠላ ዛፍ ኋላ ተደበቀ። የሁለቱ ሴቶች ብርማ ቅርጽ፣ ቆንስላውን በምታዋስነው በትንሿ የእግር መንገድ ላይ ሲሯሯጥ በግልጽ ማየት ቻለ። የሚያሳድዳቸው ነገር ጥላ፣ መንገዱን አቋርጦ እንደገና በዛፎቹ ጆርባ ከተሰወረ በኋላ፣ ፖንሴ፣ ይህ ጥላ የፈረንሳውያንን የአለባበስ ዘዴ የተከተለ፣ መካከለኛ ቁመት ያለውና ግልጽ ባይሆንም መሣሪያ ያልታጠቀ ወንድ ሰው መሆኑን ለመለየት ጊዜ አግኝቷል። ይህን ሰው ለመያዝ ከተደበቀበት መውጣት እንዳለበትም አውቋል። ለዚህ ደግሞ የተሻለው ዘዴ፣ ሰውዬው ላይ ከኋላው በኩል መድረስ ነው። ምክንያቱም የሰውዬው አትኩሮት በመሸሽ ላይ ወደሚገኙት ሴቶች ነው። ፖንሴ በበኩሉ፣ በርሱና በፊት ለፊቱ ባሉት ሁለት ዛፎች መካከል ያለውን ርቀት በፍጥነት ሸፈነ። ወዲያውኑ ሰውዬው መንገዱን



ከማቋረጡ በፊት ተደብቆበት ከነበረው ዛፍ ሥር ደረሰ። ይህ ማለት ደግሞ ጆን ባንቲስት በትክክል ከሰውዬው ባሻገር በተቃራኒው አቅጣጫ፣ ሰውዬው አትኩሮ ከሚመለከትበት አኳያ ይሆናል።

ለጥቂት ጊዜ ጠበቀና፣ እንጣጥ ብሎ ዘሎ መንገዱን በማቋረጥ በጨለማው ውስጥ ሲንቀሳቀስ የነበረውን ቅርጽ አፈፍ አደረገው። ወዲያውኑ የሰውዬውን እንቅስቃሴ በመግታት ፖቤውን አንገቱ ሥር አስጠግቶ ያዘ። ሊነገር የሚችል ትግል አልተካሄደም። በጨለማው ውስጥ እንደተነካኩ ሁለቱም መሬት ላይ ወድቀው ተንከባለሉ። ጆን ባንቲስት በቀላሉ የበላይነትን አገኘ። በአንፃሩ ባላንጣው ጉልበት ያልነበረው ወይም የፍልሚያ ችሎታ ያልነበረው ስለነበረ ፖቤው አንገቱ ስር እንደተጠጋ ወደብርሃኑ እየተጎተተ በቀላሉ ተወሰደ።

«ድረሱልኝ፣ ድረሱልኝ፣ ጥበቃዎች፣ ጥቃት እየደረሰብኝ ነው»

በፖንሴ የይቅርታ ፈቃድ ስር የተያዘው ሰው በሀይል መጮኽ ጀመረ

«ማቼ!» አለ ጆን ባንቲስት

ማቼ ይበልጥ በሀይል ጮኸ። ቆንስላው በርቀት ላይ ስላልሆነ፣ በመግቢያው በኩል የቅጭልጭልታ ድምጽ መሰማት ጀመረ። ይህ፣ ምናልባት የጥበቃ ሠራተኞች መሣሪያዎቻቸውን ሲወስዱ የተፈጠረ ድምጽ ይሆናል። በየመስኮቶቹ ብርሃን ታየ። ሦስት ሰዎችም መንገዱ ላይ ወጡ። ማቼ አሁንም ይጮሃል። የመጀመሪያው ፖኸት በድንጋጤ ምክንያት እንደተፈጠረ ፖንሴ ያውቃል። የአሁኑ ፖኸት ግን፣ ሊያድኑት የመጡትን የጥበቃ ሰዎች እርዳታ ለመሣብና አጥቂው እንዲያዝለት ለማድረግ ነው። እየጮኸ እያለ፣ ጆን ባንቲስትን ተመለከተው። ፖቤው ጉረሮው ስር በመሆኑ ያለበት ሁኔታ የማያስተማምን ደረጃ ላይ ቢሆንም የፌዝ ሣቅና የዝቅተኛነት ፈገግታ አሣየ።

በርግጥ አሁን የያዝከኝ አንተ እንደሆንክ ታስባለህ? ብሎ የሚናገረው መሠለው።

የጥበቃ ሠራተኞች በሩጫ እየተቃረቡ ነው። ጆን ባፕቲስት ምርኮኛውን ለቅቆ እግሬ አውጭኝ አለ። ሦስቱ ተረኛ ዘቦች፣ ማቼ መሬት ላይ ተቀምጦ ጉረሮውን ሲያሻሽ ሲያገኙት፣ የአግራሞትና የመደነቅ ሕምምታ አሰሙ። እርሱ በበኩሉ፣ አጥቂውን እንዳይከታተሉ ትዕዛዝ ሰጣቸው።

# 4

# የንጉሡ ጀሮ

# 1

ሲጠቀስ የሚችል የረባ ችግር ሳያጋጥማቸው፣ አሌክሳንደሪያ ደረሱ። ጀስዊቱ፣ የሶስቱን አቢሲኒያውያን ተሰፋና ምኞታቸውን ሁሉ ይከታተላሉ። እነዚህ ሦስቱ አንዳችም ቃል ባይተነፍሱም፣ ይህ ሰው እንዲህ በድንገት ለምን ባሪያቸው እንደሆነና በአንፃሩ ደግሞ፣ እነርሱ የርሱ ጌታ ለምን እንዳልሆኑ እያሰቡ የሚገረሙ ይመስሉ ነበር። ቻንስለር ፍሌሃውትን በተመለከተ ሰውዬው በየዕለቱ በነበራቸው ዕረፍት ላይ ፍፁም አፋቸውን ከፍተው አያውቁም። ይሁን እንጂ፣ የምግብ ሰዓት ትንሽ እንኳ ከዘገየ ሞትኩ እያሉ አንድ ሺህ ጊዜ ይወተውታሉ።

በጉዟቸው ላይ የመጀመሪያው አደጋ ያጋጠማቸው አሌክሳንደሪያ ውስጥ ነበር። ሁለቱ ሰረገላዎች ባህሩ ዳር የደረሱት ከመሸ ስለነበረ፣ ሪጉት በሚባል ፈረንሣዊ ወደ ሆቴልነት የተቀየረው፣ ጥንት የመዝናኛ ቦታ ወደነበረው ፈረሶቻቸውን እየሳቡ ሄዱ። ይህ ቦታ የተመረጠላቸው በሙሴ ዴ ማይሌ ነበር። የሆቴሉም ባለቤት፣ ከቆንሲሉ ለሚያገኘው ድጋፍና ጥበቃ ሲል ሁልጊዜም ሪፖርት ያቀርባል። ሰውዬው፣ መንገደኞቹን ተቀብሎ፣ ራትም አቅርቦላቸው በሁለት የተለያዩ የማረፊያ ክፍሎች ውስጥ እንዲያርፉ በማድረግ፣ ራሱ አስተናገዳቸው። እንደአለመታደልም ሆኖ አቢሲኒያውያኑ የተጫኑበትን ሰረገላ ይነዳ የነበረው የአሌክሳንደሪያው ሸማግሌ ሌሊቱን በመኖሪያ ቤቱ ለማሣለፍ ይወስናል። ወደ ቤቱም ሲሄድ የአጐቱን ልጅ በመንገድ ላይ ያገኘዋል። ይህ የአጐት ልጅ፣ በዚህ የሠራተኞች ሠፈር ውስጥ በጣም አክራሪ ከሆኑት ሙፍቲዎች አንዱ ነው። ሽማግሌው ጋሪ ነጅ፣ ስለ አቢሲኒያውያኑና ስለሚያጅቧቸው ፈረንሣውያን ይነግረዋል። ይህ የአጐት ልጅ ተብዬው፣የሰማውን አስደሣች ትንሽ ዜና በጀለቢያው ውስጥ ደብቆ ይዞ ሄደ።

የቤተመንግስቱ ጀልባ በሚቀጥለው ዕለት ከወደብ ይለቅቃል። ወደቡም ደግሞ ሊታመን ከሚችለው በላይ ሽርጉድና ትርምስ የበዛበት ነው። በጭንቅላታቸው ላይ ሚዛኑን ጠብቀው የተሸከሙትን ዕቃ ይዘው በመሸጋገሪያው ላይ የሚወጡና የሚወርዱ ተሸካሚዎች ክምችት ይበዛል። እነዚህ ኩሊዎች ሲጯጯሁ የሚሰማው የገደል ማሚቶ፣ በመርከቡ ወለልና በመርከቡ ማቆሚያ መካከል ይስተጋባል። ለመርከቡ ቀዛፊዎች ከተያዘው ከታችኛው ጨለማ ወለል በኩልም የሰዎች ድምፅ ይሰማል። ፀሐይዋ ቁልቁል በቀጥታ ስለምትመታ፣ ሁሉም ነገር ያንፀባርቃል። ነጭ ቀለም የተቀቡት የወደቡ ሕንፃዎች፣ የፍራፍሬ ሳጥኖችና ሌላው

ከሁለት ቀናት በኋላ ተንዠቹ በሌላ ጥቁር ሠረገላ ላይ ተሳፈሩ። ይህ ሠረገላ ለመንቀሳቀስ እንኳ ደካማ የነበረ ሲሆን፣ ጋሪ ነጂውም እጅግ ዝቅተኛ ክፍያ የሚያገኝ ተቀጣሪ መሆኑ የማያጠራጥር፣ ለቀጣሪ ጌቶቹ አውጥቶ ሊገልፅላቸው ያልቻለውን ተስፋ መቁረጥና ብስጭት ለተሳፋሪዎች የሚወተውት ነበር። ይህ ምስኪን፣ በመንገዱ ላይ በሚገኙት የተቦረቦሩ ቦታዎች ሁሉ ላይ ሆን ብሎ ፈረሶቹን በሙሉ ሀይላቸው እንዲጋልቡ በማድረግ ተሳፋሪዎቹ ከአንድ ጊዜ በላይ አንዳቸው በሌላኛው ላይ እንዲወድቁ የሚያደርግ ይመስላል። በዚህ የተነሳ ያገኙትን ሁሉ በመጨበጥ ሲዋከቡ ተጉድተውና ከፍቷቸው ስለነበረ፣ በመንገዳቸው ላይ ምንም ነገር ማየት ሳይችሉ፣ ሰሶቱ የመንግስት መልዕክተኞች እንዲቀዩበት በማለት ጀስዊት ካህናት ወዳዘጋጁላቸው ቻቴ ዱ ሲሚአኔ በድቅድቅ ጨለማ ደረሱ።

ከበርቴው ዱ ሲሚአኔ፣ ግዙፍና ደስ የሚል ጨዋ ሰው ሲሆን፣ የሚያስደስት የክፍለ ሃገር ቅላፄ ይናገራል። ይህ ከበርቴ እንግዶቹን እስከሚቀጥለው ሁለት ቀን ድረስ ይመጣሉ ብሎ አይጠብቃቸውም ነበር። በተፈጠረው አለመግባባት በጣም ቅር ቢለውም የአደን ልብሱን እንደለበሰና በሚያደርገው ተግባር እንግዶቹ እንዳያዝኑበት በቀላል አቀራረብ ሰላምታ ሰጥቶ ከተቀበላቸው በኋላ ባለቤቱንና ሁለት ወንዶች ልጆቹን አስተዋወቃቸው። ልጆቹ በሚደንቅ ሁኔታ ቁርጥ እናታቸውን ናቸው። ረዣዥምና ሹል አፍንጫ፣ ጥቁር ፀጉርና ክብ ፊት ያላቸው ናቸው። በትዳር ብዙ በመቆየት ብዙ ያተጉዳችና ድቅቅ ያለችው ይህች ሴት በስጦቻቸው ወጣትነትና ቁንጅና ሳቢያ በነዚህ ሁለት ጠንካራ ልጆችዋ ተደግፋ፣ ባልተቋረጠ ሁኔታ በሚሰጧት አትኩሮት እየታደሰች ያለች መሆኗ ሲታይ ያኮራል። በዚያን ዕለት ምሽት ከአደን የተገኘ ምግብ በቢጫ ሰማያዊ የሸክላ ገበታ ላይ ቀርቦላቸው ተመገቡ።

«እያችሁ፣ እንዲህ የተደረገው ልክ እንደቤታችሁ እንዲሰማችሁ ነው» አለ አስተናጋጃቸው እየሳቀ።

ክብ፣ ግዙፍና በጣም በሚያብረቀርቀው ሳህን ጀርባ ላይ የቱርካውያንን ሁኔታ የሚገልፀውን የጌጥ ቅርፅ አሳያቸው። በዚህ ቅርፅ ላይ ሰጉን የሚያድኑ ቱርኮች፣ በአንድ የፏፏቴ ምንጭ አጠገብ ቁርአን ሲቀሩና በረዥም ረድፍ ገብተው ፈረስ ሲጋልቡ የሚያሳይ አለበት።

በሚቀጥለው ዕለት ያህንኑ ከበርቴ ለአደን አብሮት ሊወጣ ይችል እንደሆነ ፖንሴ ጠየቀው። የአስተናጋጁ ልጆችም ተጨመሩና አራት ሆኑ። ደኑ፣ በሞቃት ጭጋግ ተሸፍኖ፣



ወርቃማ ቅጠሎችም ውሃ ያንጠባጥባሉ። በዚህ ወቅት እሾሃማ ቅርፊት ባለው የሰውዝ አይነት የተሸፈነው ወፍራም ብስባሽ፣ የፈረሶቻቸውን የኮቴ ድምፅ ያፍነዋል። ከሌልኘስ ተራራ በረዷማ ነፋስ አፍንጫዎቻቸውን ሲወጋው የጥድ ደንና የጥድ ሽታ መዓዛ ይደርሳቸዋል።

ከመሸ በኋላ ደረሱ። ማዳም ዱ ሲሚአኔን ከጨፍጋጋዎቹ ከፍሌሀውትና ከአባ ኘላንቴይን ጋር የአራት ሰዓት እስኪያልፍ ድረስ ለብቻዋ ትተዋት በመሄዳቸው አፈሩ። ይሁንና በአደናቸው ተደስተው፣ ደክሟቸው ነበር የተመለሱት። ምንም አንኳ ሶስት ቃላት እንኳ በመነጋገር ባይለዋወጡም፣ በአደናቸው ላይ እርስ በርሳቸው ጣዕማቸውን የተዋወቁ ወዳጆች ሆነው በመቆየታቸውም ተደስተው ነበር።

አዳኞቹ ልብሶቻቸውን ለውጠው ቀለል ያለ ዕራት በሉ። የቀሩት ቀደም ሲል ወደየመኝታቸው ሄደዋል። ፖንሴ በሚቀጥለው ቀን በዚሁ መንገድ፣ በዚያው ጥቁር የወፍ ጉጆና የቁራ አሞራ ያለበትን ቦታ ተከትሎ የመሄዱ ሃሳብ ስጋት ቢያሳድርበትም፣ ሙሴ ዱ ሲሚአኔ፣ ፈረስ ከነኮርቻው ቢሸጥለትና በዚያ ሊጓዝ ይችል እንደሆነ ጠየቀው። በርግጥ በዚያ መንገድ በቀን ብርሃን በሠረገላ ሊጓዝ ይችላል።

«ሙሉ በሙሉ እገነዘባለሁ። ወደ ፈረንሳይ ገና መመለስህ ነው። ስለዚህም በታላቅ ደስታ ልትለማመደውና በነፋሱ ውስጥ ልትንሸራሸር ፈልገሃል። እኔ ራሴም ብሆን በቤት ውስጥ መዋል በጭራሽ አልችልም ነበር። ለዚህም ነው በየአደባባዩ የማልገኘው። አሁን ለሽርሽርህ ፈረስ ያስፈልግሃል። ይህንንም ነገ ታገኘዋለህ። ወርቅህን ለሌላ ጉዳይ ስለምትጠቀምበት ያዘው። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ስትመለስ ይህን ፈረስ መልሰህ ታመጣልኛለህ። ወይም ሌላ ወይም ጭራሽም አታመጣልኝም። አንተን እዚህ ቤት ሁልጊዜም ልንቀበልህ ዝግጁ ነን» አለው ከበርቴው።

አራቱም ሰዎች በእሳት ማንደጃው ዙሪያ በአንድ ትልቅ ባለመከዳ መቀመጫ ላይ ተቀምጠው ሳሉ፣ ሙሴ ዱ ሲሚአኔ፣ ስለአቢሲኒያ ጥቂት ነገር እንዲነግራቸው ፖንሴን ጠየቀው። ፖንሴም ሊተርክላቸው ከሚችላቸው ሁሉ አቢሲኒያውያን ዝሆንን እንዴት እንደሚያድኑ ሊነግራቸው መረጠ።

ይህ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም እውነተኛ ሃሣብ ነው::

«ቆንስላው» ብሎ ሲናገር ስለቆንሲሉ እያሰበ መሆኑ ግልፅ ነው::

«እንግዲያው ከአገልጋዮቼ ጋር ብቻ እሄዳለሁ» አለች አሊስ

«የትኞቹ አገልጋዮች? ያች ሁልጊዜም ከጉንሽ የማትለየውና መጥፎ ሪፖርት የሰማሁባት ልብስ አጣቢ ነች?»

የሙሴ ማቼ መራራ ሃሞት በርስዋም ላይ ተደፍቶባታል፣ ስትል አሊስ አሰበች::

«ለመሆኑ እስከዛሬ ምን ጥፋት ፈፀመች፣ አባባ?» አለች ትልልቆቹን ዓይኖችዋን በቆንሲሉ ፊት ላይ በዝግታ እንዲሽከረከሩ በማድረግ::

«ያም ሆነ ይህ» አለ ዓይኖችዋን እየሸሸ « ሁለት ሴቶች አብረው ብቻቸውን እዚያ መቆየት አይችሉም:: ከቆንስላው ሁለት ዘበኞች ያስፈልጉሻል፣ ከመናፈሻው ራቅ ካለው ዳርቻ ላይ የጥበቃ አዛዡ ጥቂት ሚሊሺያዎችን እንዲመድብልኝ ጠይቀዋለሁ::

«ኦ! እንዲህ ከሆነ ፈቃድህን አግኝቻለሁ?»

«ለመልካም ባህሪሽ ስል ነው» አለ በሻካራ ድምፅ:: «እናም እንደቅድመ ሁኔታ፣ እኔ እንድትመጪ ስጠራሽ ወዲያውኑ ለመመለስ ቃል ስትገቢ ነው:: ምክንያቱም ስለማንኑቱ የተናገርኩለት ሰው ብዙም አይቆይም»

አሊስ፣ በዚህ ቅድመ ሁኔታ ተስማማችና በጦርነት ድል እንዳደረገች ያህል ራሷን አሣምና ሄደች::

ሙሴ ዴ ማይሌ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ትዕዛዙን ሰጠ:: ከዚያም፣ እርሱ ራሱ በውይይቱ የረካ ስለሆነ ቀሪውን የማለዳ ሰዓት ለሚያውቃቸው ሰዎች ሦስት ደብዳቤዎችን ሲፅፍ ቆየ:: ከነዚህ አንዱ በፖንሴ ላይ የጥቃት በትሩን እንዲያሣርፍለት የመረጠው፣ ሚኒስትሩ ፖንቻርትሬይን ነው:: ቆንሲሉ፣ ፖንሴን ሲገልፀው ሠካራም እንደሆነ፣ አንዳችም የእውነት ጠብታ የሌለባቸውን ታሪኮች እንደሚፈጥር፣ በምኞት የሚነዳና የባለጌነት ባህርይ



ያለው ነው ይለዋል:: ቆንሲሉ፣ ፖንሴ ወደ አቢሲኒያ መጓዙን በሚገልፀው ትረካውም ላይ፣ ትልቅ ጥርጣሬ አለው:: እንዲያውም ይህ የማጋነንና የመዋሸት አባዜና ዝንባሌ ያለው ግለሰብ ምናልባት ከሲናር አልፎ እንዳልሄደም ሲል ሃሳቡን አስፍሯል:: ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ይደግፉኛልና ማሸነፊያም ይሆኑኛል ያላቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ደካሞች ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ በሚቀጥሉት ተጨማሪ ቀናት የሚደርሱት ሌሎች መረጃዎች ቢኖሩ እንደሚያክል ገልጿል::

የመጀመሪያው የመልዕክተኛ ቡድን ከሄደ በኋላ እንደ ሆነው ሁሉ፣ የካፑቺኖች አለቃ የሆኑት ፒማሙና ግዙፉ መነኩሴ ወንድም ፖስኳል፣ ቅሬታቸውን በቁጣ ሊገልፁ ወደ ቆንሲሉ መጡ:: መነኩሴው አባ ፕላንቴይን፣ ከአቢሲኒያውያን ጋር ወደ ቬርሣይለስ መጓዛቸውን አውቀው ስለነበር «ፈረንሣይ፣ በተለየ ላሉት የስብከት ሥርዓት አራማጆች የምታሣየው አድልዎ» በማለት፣ በሚጠቅሱት ጉዳይ ላይ ተቃውሞአቸውን ያቀርባሉ:: ለዚህ ቅሬታ ሙሴ ዴ ማይሌ ደስ በሚልና በወዳጃዊ መንፈስ ማንንም በተለይ እንደማይደግፍና እንዲያውም በሌላ ምክንያት ሳይሆን በወንድም ፖስኳል ወዳጅነት ሣቢያ የርሣቸውን የእምነት ሥርዓት ጥረት፣ አቅሙ በፈቀደው መጠን እንደሚደግፍ መለሰላቸው::

«ስለትም የደረሰው በጥሩ ሰዐት ነው:: አሁን በቅርቡ ወደ አቢሲኒያ አንድ የጉዞ ዘመቻ ለማድረግ አቅደናል» አሉ ኢጣሊያዊው ካህን

«ሌላ ዘመቻ ልታደርጉ?»

«ሰጊዜው ሲናር እንሰነብታለን:: ከዚያም አልፎ የሄደ ሰው የለም» ካሉ በኋላ በአታላይ ፈገግታ «ሌላው ቀርቶ የርስዎ ተረጂና ተመፅዋችም ቢሆን አላለፈም»

«የኔ ተረጂና ተመፅዋች?»

«አዎን፣ ሲኞር ፖንሴ!»

ቆንሲሉ፣ይህን ዜና ለመስማት የመጓጓት ስሜት አሣየ:: ወንድም ፖስኳል የተናገሩትን እንዲደግሙለትም ጠየቃቸው::

እጅግ በሚታመኑትና፣ ሲናር ከሚኖሩት ወንድሞች በደረሣቸው መረጃ መሠረት፣ ፖንሴ፣ ከሲናር፣ ከሸሸ በኋላ አንድ ሃምሣ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ድረስ ከወሰኑ አልፎ እንደተጓዘና በአንድ የአቢሲኒያውያን መንደር ውስጥ በቀረጥ ኬላ ላይ ሲያገለግል እንደቆየ፣ ከዚያም አልፎ መጓዝ እንዳልተፈቀደለት፣ በዚያው መንደር ውስጥ ብዙ ወራት ሲጠብቅ እንደከረመ፣ በአገሩ ባህል መሠረት በቀላሉ ሲያደርገው የሚችለውን፣ አንዲት የአካባቢውን ተወላጅ ሴት አግብቶ እንደነበረና ጨርሶ ስላላገኘው ንጉሠ ነገስት ብዙ ታሪኮችን ሰብስቦ እንደተመለሰ በማረጋገጥ ቄሱ ተናገሩ።

በዚህ ንግግር ቆንሲሉ ከመጠን በላይ ተደሰተ። እንዲያውም ይህን ሁሉ ከሰሙ በኋላ ለምን ፈጥነው መጥተው እንዳልነገሩት ካፑቺኑን ጠየቃቸው። እርሣቸውም በበኩላቸው፣ ፈረንሣውያን፣ አንድ አርመናዊ የቀድሞ የወጥ ቤት ሠራተኛ የነበረን ሰው፣ እንደ አምባሣደር አድርገው ተቀብለው ራሣቸውን ሲያዋርዱ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ እርሣቸው ጣልቃ የሚገቡበት ሰበብ ስለሌላቸው እንደሆነ በሽሙጥ ተናገሩ። ይሁን እንጂ ዝርዝር ታሪኩን ወደ ሮም እንደላኩና ሁሉም ካፑቺኖች ሌላው ቀርቶ ፖሪስ የሚገኙትም ጭምር እውነቱን እንደሚያውቁ አብራሩ።

«የሚነግሩኝ ሁሉ ታላቅ ጉዳይ ነው» አለ ቆንሲሉ። «ሲናር ከሚገኙት አባቶች ሪፖረት ማግኘት ይችላሉ? ሪፖርቱስ በጽሁፍ ነው?»

«ሲናር ከሚገኙት የመነኮሣት አለቃ የተፃፈ ረዥም ደብዳቤ በገዳሙ ውስጥ አለኝ»

«የደብዳቤውን ቅጅ እንዲሰጡኝ በማክበር እጠይቅዎታለሁ። ሁሉንም ነገር እንዲቋረጥ ለማድረግ አሁንም በቂ ጊዜ አለ»

ካፑቺኑ ምንም ሣይናገሩ ረዘም ላለ ጊዜ ጠበቁ።

ቆንሲሉ ወጥመዱ ውስጥ ከገባ በኋላ፣ ቁጣውንና ብስጭቱን በወረቀት ላይ ማስፈር ጀመረ።

«የተስማማን ስለሆነ ፈቃዴን ሰጥቼዎታለሁ። ያቀዱትን ተልዕኮ ለማገዝ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ»



«ቃል ነው?»

«ቃል ነው»

«ጥሩ። ደብዳቤው ዛሬ ማታ በእጅዎ ውስጥ ይገባል» አሉ፣ የመጡበት ጉዳይ የተሣካላቸው አባ ፖስኳል። «በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ በእቅዳችን ላይ እንዴት ሊረዱን እንደሚችሉ ላነጋግርዎ እመጣለሁ»

ይህን ከተናገሩ በኋላ፣ ኢጣሊያዊው ካህን፣ ሳይታሰብ በድንገት እንደመጡ ሁሉ ወዲያውኑ ቆንስላውን ለቀው ሄዱ ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የካህኑን አጠቃላይ ግልፅነት፣ ጨዋ መስለው በምስጢርና በድብቅ ከሚሠሩት ከአግኖጢዮሣውያን ጋር በማነፃፀር በጣም አደነቃቸው።

ጊዛ ውስጥ ኦና ሆኖ የከረመውን ቤት ለማደስና ለማዘጋጀት፣ አገልጋዮች የጥቂት ሣምንት ጊዜ ወሰደባቸው። መስኮቶቹን ሁሉ ከፍተው ንፁህ አየር በየማረፊያው እንዲገባ አደረጉ። ከዚያም በመቀጠል ሁሉንም ክፍሎች ከትኩሣት ሕመም ነፃ ለማድረግ በመድሃኒት አጠኑ። በመጨረሻም በሁለት ሠረገላዎች ጭነው ያመጧቸውን ዝርግና ጉድጓዳ ሳህኖች፣ኩባያዎችና ሌሎችም ከሸክላ የተሠሩ የቤት ቁሳቁሶችን በክፍሎቹ ውስጥ ሞሏቸው። በአልጋዎቹም ላይ አዳዲስ አንሶላዎችን አንጥፈው አስጌጧቸው።

ቤቱ ተስተካክሎ ካበቃ ከአንድ ቀን በኋላ፣ አሊስ ከፍራንቾይዝ ጋር መጣች። እንደተገመተው፣ የአሊስ እናት ካይሮ ለመሰንበት ወሰነች። የተከተሏቸው ሦስት አገልጋዮች፣ ሙሉ በሙሉ ሁለቱን ሴቶች ለማገልገል የሚታመንባቸው ናቸው። በርግጥ፣ ሁለቱን ሴቶች ተከትለው ለመምጣት መመረጥ የሚችሉ ብዙ ነበሩ። ምክንያቱም በአጠቃላይ የቤት አገልጋዮች በቆንሲሉ ንፉግነትና ለበታቾቹ ባለው ጥላቻ ላይ አቋም ወስደው ነበር። የሚሊሺያዎች አዛዥ የመደባቸውን ጥቂት ቱርካውያን ጠባቂዎችን በተመለከተ የተሰጣቸው መመሪያ፣ ከመኖሪያ ቤቱ ራቅ ባለ ሥፍራ ላይ እንዲሰፍሩና ንብረቱን ብቻ ከውጭ ሆነው እንዲጠብቁ የሚል ነበር።

ማዳሞዜል ዴ ማይሌ፣ በሠረገላ ተሣፍራ ከቀትር በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ላይ ደረሰች። የለበሰችው ተራ ሰማያዊ ጥብቅ የሚያደርግ ልብስና ጥቁር ከፋይ ቀሚስ ሲሆን፣ ጥቅል ፀጉርዋንም በአንድ ነጠላ ሪበን ሸብ አድርጋዋለች። ስለቤቱ ገለፃ ሲደረግ ከመስማቷ በስተቀር በአይኗ አይታው አታውቅም። አሁን ስትመለከተው በውሃ ሙላት ጊዜ ዙሪያውን በውሃ በሚከበብ ከፍ ያለ ቦታ ላይ የተሠራ መሰላት። ሕንፃው ራሱ የቱርካውያን ቤተመንግስት የነበረ ሲሆን፣ በእንጨት ቅስቶች በሹል ቅርፅ የተሠራ ነው። መስኮቶችም የእንጨት ርብራብ መከላከያ ያላቸው ክፍት የጥድ ጣውላዎች ናቸው። ባለስምንት ማዕዘን ረዥምም ጉልላት ሆኖ፣ የኦቶማኖችን የራስ ቁር የመሰለ ጣሪያ አለው። በአሁኑ ጊዜ የማይታይበት በጣሪያው አናት ላይ የነበረው የእስልምና ግማሽ ጨረቃ ነው። ይህ ምልክት በአንድ ዘመን ነበረ። በኋላ ግን ገዥው ፓሻ ቤቱን ለፈረንሣይ ቆንሲል ከአንድ ሃምሳ ዓመት በፊት ሲሰጥ፣ ይህን ምልክት አስነሣው።

ሕንፃው፣ የአባይ የተለመደ ሙላት ከማይደርስበት ከፍ ብሎ በጉብታ ላይ የተሠራ በመሆኑ፣ የወንዙን ግራና ቀኝ ዳርቻዎች ቁልቁል ወሰል አድርጐ ያሣያል። በሦስቱም ማዕዘንና ቤቱን ከብቦ የሚታየው የደለል አፈር ሜዳ፣ ለም መሆኑ ባያጠራጥርም ቆንሲሉ ስራ ላይ አላዋለውም። በዚህ የተነሣ ሰፊ የሣር ምድር ግቢ በመሆኑ፣ ቤቱ፣ ባልተቆራረጠና እጅግ ሠፊ የሣር መስክ ተከብቧል። የቤቱ አራተኛው ጐኑ ወደ ወንዙ የሚያቆለቁል ሲሆን በትላልቅ ዛፎች ተክል የተሸፈነ ነው። የነዚህ ዛፎች ቅርንጫፎቻቸው የተጠጋጉና የተቀራረቡ በመሆናቸው ሌሎች ተክሎች ከስራቸው እንዳይበቅሉ ያግዳሉ። ከዚህ ይልቅ የደረቁ ቅጠሎች እንደ ስጋጃ በጥላው ውስጥ ተነጥፈው እስከ ወንዙ ጠርዝ ድረስ እስካሉት የቁጢማ ተክሎች ተዘርግተዋል። በአባይ ላይ የሚንሳፈፉት ነጫጮቹ ትናንሽ የጠረፍ ጀልባዎች፣ ከቆንሲሉ ንብረት አካባቢ እንዳይቀርቡ የሚከለከለው ቃል፣ ለጀልባ ቀዛፊዎች ሁሉ የተላለፈ ይመስል በርቀት ናቸው። አንድ የእንጨት የመዝናኛና የመሸጋገሪያ ድልድይ፣ ያረጀና ጥቅም የሌለው ተንሣፋፊ ጀልባ ወዳለበት ሃያ ጫማ ያህል ወደ ውሃው መሃል ተዘርግቷል።

አሊስ፣ ቤቱን ተዘዋውራ አየች። በእንግዳ መቀበያ የእንጨት በረንዳ ላይ ቆም ብላ፣ የወንዙን መረር የሚል ነፋስ ወደ ውስጥ በሃይል ሣበች። ይሁንና በዚህ ደስታ ውስጥ ራሷን ብዙም አላቆየችውም።

ፍራንቾይዝን «ነይ» አለቻት። «እቅዳችንን ለመጀመር ሴኮንድ ማባከን የለብንም»



# 3

የህዳር ወር ቀዝቃዛ ነበር። እጆቹን በተቻለው መጠን በፈረሱ ጫንቃ ላይ በማሻሸት ያሟሟቀው ጆን ባፕቲስት፣ ኬላው ላይ ሲደርስ በረዶ ሆኖ ነበር። በራሱ ፍጥነት እየጋለበ ሲሄድና በያንዳንዱ ታላቅ ከተማ መግቢያ ላይ ለመገናኘት ከጉዞ ጓደኞቹ ጋር ተስማምተው ነበር። በመጨረሻም፣ ነፃነትና በራሱ የመመራት ስሜት አድሮበት መንዝ ጀመረ። ወደ መንደሮች እየገባ ከባላገሮች ጋር ይነጋገራል። በየመስኩም፣ ሥራ ፈትተው ከተቀመጡ አዛውንቶች የሚነገረውን ይሰማል። ሊዮንስ ከተማ ውስጥ፣ አንድ የፖስታ ቤት ሰራተኛ መለዮና ቀይ ላባ ያለበት ሰፊ ባርኔጣ ገዛ። እግረ መንገዱንም የእስፖኝ ንጉስ መሞታቸውን ተረዳ።

ከሶስት ቀናት ጉዞ በኋላ፣ ባለሰረገላዎችና ባለፈረሶች፣ የጄስዊቶች መኖሪያ ቤት ወደሚገኝበት ፎንቴይን ብሉ፣ በውድቀት ሌሊት ደረሰ። ሃይለኛ ነፋስ የሠረገላውን የነሃስ ፋኖስ መብራት በተደጋጋሚ ያጠፋው ነበር። በመንገዱ ግራና ቀኝ በመደዳ የተተከሉት ጥቋቁር ዛፎችም ወደፊትና ወደ ኋላ በሃይል ይወዛወዛሉ። ጆን ባፕቲስት፣ የሚወርደውን ቀዝቃዛ ዝናብ ለመጉረስ በሚል አፉን ሲከፍት፣ ከት ብሎ ሣቀ። የተለየ በሆነው በሁናር አውራጃ ምድር ለአመታት በመቆየቱ፣ እዚህ ያለውን የአየር ጠባይ መዘንጋቱን ተገነዘበ። በሚቀጥለው ቀን የቀረጥ ተቀባዮችን የኬላ ዳስ በደቡባዊ መግቢያ በር አልፈው ፖሪስ ደረሱ። ከዚያም ወደ ዮብሬ አቀኑ። በጉናቸው በኩል ዝናቡ እንደገና ከመጣሉ በፊት መጠለያ ወዳለበት ለመድረስ ሲገሰግሱ ጥቋቁር ጥላዎችም እንዲሁ ይጣደፋሉ።

የሉዊስ ሌ ግራንዴ ትምህርት ቤት በሆነው የተለየ ሕንፃ ውስጥ ሠፈሩ። በአቅራቢያው በሚገኘው የአውቴኡል መንደር ቤተሰብ ያለው ፍሌሃው፣ በመጀመሪያው ዕለት ተለያቸው።

ዲፕሎማቱ፣ ያሳደዱት ያህል በጋሪው ተጣድፎ ከሄደ በኋላ፣ «ለፖንቻርትሬይን ሪፖርቱን ሊሰጥ ነው» አሉ አባ ፕላንቴይን ክፋት በተሞላበት አነጋገር።

በዚያን ጊዜ ይነገር የነበረው ታላቅ ዜና፣ የስፔይን ንጉሥ ያደረጉትን የኑዛዜ ቃል ሉዊስ 14ኛ የመቀበላቸው ጉዳይ ነበር። ከአብራካቸው የተገኘ ልጅ የሌላቸው የእስፔይኑ ንጉሲ፣ ዘውዳቸውን ለሉዊስ የልጅ ልጅ፣ ለአንጁ ዱክ ተናዘውለታል። በዚህም የተነሣ ታዋቂው የንጉሡ የልጅ ልጅ፣ የማድሪድን ዙፋን ሊይዝ ስለሆነ፣ የፈረንሣይ ንጉሥ ሁለቱንም ግዛተ

ዘውዶች ሲገዙና፣ በአውሮፖና በመላውም ዓለም እጅግ ሃያሉ ሰው ሲሆኑ ነው። ስለዚህም ጦርነት የማይቀር ነገር ነው። ጄስዊቶቹ ይህን ታላቅ ጉዳይ በደስታ ተወያዩበት። በክርስቲያኑ ዓለም ውስጥ እጅግ ታላቁ የሆነው ንጉሥ፣ ከዚህ በፊት ሲያከናውነው ከነበረው ባላነሰ፣ የካቶሊክ ተልዕኮውን፣ በተለይም በምስራቁ ዓለምና በአቢሲኒያም ውስጥ የጠባቂነት ሚናውን በግድ ይወጣዋል ሲሉ አባ ፕላንቴይን ያስባሉ። ምንም አዲስ ነገር ባይፈፀምም፣ አባ ፕላንቴይን በሕይወታቸው ውስጥ እጅግ ታላቅ ከሚሉት ተግባር ጋር ይህን ሃሣብ አቆራኙት። ይህ ታላቅ ተግባር ደግሞ፣ የተዳከመውን የቅዱስ ሮማና የሃዋርያትን ቤተክርስቲያን እርሳቸው ወደማያውቋትና ከርሣቸውም ምንም ወዳልጠየቀችው አገር ማምጣት ነበር።

ጆን ባፕቲስት፣ ከዚህ ቀደም ጨርሶ ፖሪስ መጥቶ አያውቅም። እዚያ በገባ በመጀመሪያው ምሽት ወደ ሲየን ወረደ። ፈረሱንም በመርከቦች ማቆሚያ ዳር፣ በተቀዛፊ ጀልባዎችና በማጠቢያ ቤቶች መካከል ውሃ እንዲጠጣ አደረገው። በመጀመሪያ ላይ አዲስ የሕንፃ ግንባታ በሚከናወንበት ሰፊ ሜዳ ላይ ቆየ። ከዚያም ኢንቫሊድን አቋርጦ፣ በመርከብ ማቆሚያው አድርጉ፣ ራቅ ብሎ እስካለው እስከ ፖንትኑዩፍ ተጓዘ። ከዚያም በሰሜናዊው ሰፊ የከተማው ጉዳና ረዥም ዙሪያ ክብ መንገድ ላይ እስከ ባስቲል ድረስ ተጓዘ። እርሱ አገሩን ለቅቆ ከሄደ ወዲህ፣ ሰዎች በልብስ ፋሽናቸው ላይ በጣም ትልቅ ለውጥ እንዳደረጉም ተገነዘበ። ይህን በተመለከተ፣ ካይሮ የሚገኙት ፈረንሣውያን በጣም ኋላ ቀር ሆነዋል። የለበሰውን ምርጥ ሙሉ ልብስ ከዋና ከተማው ነዋሪዎች አለባበስ ጋር ሲያነፃፅረው፣ የሚያሣፍር ሆነበት። በሚቀጥለው ቀን ወደ ሴንት ጃክዴስ ሄዶ የብር ጉንጉን ጌጥ ያለበት አረንጓዴ ከፋይ ኮት፣ የሃር ሰደርያ፣ ጥቁር ቦላሌና የእግር ሹራቦችን ገዛ። ይህን የአዘቦት የሥራ ልብስ ለብሶ፣ የከተማዋን እምብርት ዘልቆ ለመግባት ወኔ ተሰማው። ይህን ለብሶ በከተማዋ መሃል ባሉ ጠባብ መንገዶች ላይ የሚንቀሳቀስ ሰው፣ ሌሎች ተንገሮችና ባለሱቆች የሚናገሩትን እርቲ ቡርቲ አስተያየቶች ሁሉ ሊሰማ ይችላል። አቋሙ ደስ የሚል ነው። ኮራጁ ታጥቋል። አይኖቹም የሚያባብሉ ናቸው። አንድም ሰው አንዳችም ማጉረምረም አያደርግበትም።

በከተማው ውስጥ በራሱ ወጭ ማረፊያ ቦታ ለማግኘት ቁርጠኛ ውሣኔ አደረገ። ጄስዊቶቹ፣ እዚህ ድረስ አምጥተውት በቤተመንግስት ስብሰባ ላይ እንዲገኝም ሁኔታዎችን እያመቻቹ ነው። ይህ ደግሞ በቂ ነው። ከዚህ ባሻገር የነርሱ ሽክምና ዕዳ መሆን አልፈለገም። ይሁን እንጂ ራሱን ለመቻል ሃብታም አልነበረም። የዋና ከተማው ኑሮም ከፍተኛና ውድ ነው።



የያዝኩትን የወርቅ ዱቄት ለንጉሡ በገፀበረከትነት ከማቀርብላቸው ይልቅ፣ የራሴን ነፃነት የማውጅበት ይሆነኛል ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ። ንጉሠ ነገስቱም ይህችን ታህል ትንሽ ነገር በስጦታ ስትቀርብላቸው እንደስድብ ሊቆጥሯት ይችላሉ።

ወርቁንም ወደ አንድ በገንዘብ ሊለውጥለት ወደሚችል ሰው ዘንድ አመጣው። ምንም እንኳ ከረዥም ርቀት ቦታ የመጣ ወርቅ ቢሆንም በዚያን ጊዜ ሊለወጥ ከሚችለው በላይ አያወጣም። ባለገንዘቡም በጥርጣሬ ካየውና ከረዥም ዝምታ በኋላ ቀለል ያለ የኢኩስ ክረጢት ሰጠው። ይህ መጠን ከምንም የተሻለ ነው። ለጥሩ ማረፊያም በቂ ነው ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ።

የማረፊያ ክፍል ለማግኘት ባደረገው እንቅስቃሴ፣ በመጀመሪያ በኢል ዱ ላ ሲቲ ዙሪያና ቀጥሎም በሆቴል ዱ ቪሌ አካባቢ ተዟዟረ። በመጨረሻም የሚፈልገውና የሚስማማውን በቅዱስ ኢዩስታች ቤተክርስቲያን አጠገብ አገኘ። ዓይኖቹን የማረከው የመጠጥ ቤት ምልክት ሰርሱ ሁኔታ ፍፁም የሚስማማ ነበር። ምልክቱም በአንድ የብረት ንጣፍ ላይ ከወገቡ በታች ግልድም ታጥቆ ጦር የያዘ የግዙፍ አፍሪካዊ ቅርፅ የተሣለበት ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ ወደዚህ ሉ ቢዩ ኖይር ተብሎ ወደሚታወቀው ቤት ገባ። አስተናጋጁ ባለቤት፣ ረዥም፣ ጉንጮቹ ወደ ውስጥ የተጣበቁበትና አመዳም ፊት ያለው ሲሆን፣ ከራሱ ይልቅ ለደንበኞቹ የተሻለ ጥንቃቄ የሚያደርግላቸው ይመስላል። ወደ መንገዱ አቅጣጫ ካለው ክፍል ውስጥ ሞቅ ያለ እውነተኛ የሣቅ ድምፅ ይሰማል።

«መጋዘኑን የገዛሁት ከአንድ ልብስ አቅላሚ ላይ ነበር» ሲል ሰውዬው ሞቅ ባለ ፈገግታ ይናገራል፡ «እርሱ የፈለገው ያንን ያልተለመደ ምልክት ሲሆን እኔም ልጠብቅለት ወሰንኩ»

ጆን ባፕቲስት ወደ ውስጥ ዘልቆ አንድ የተለቀቀ ክፍል ያገኝ እንደሆነና ዋጋውም ምን ያህል እንደሚሆን ጠየቀ። ሊገኝ የቻለው ከጉረኖ የማይሻል ትንሽ ክፍል ነው። ለዚያውም ኪራዩ ውድ ነው። ይሁንና የራሱ የሆነ የእሣት ማንደጃ ቦታ ያለው ሲሆን፣ ባለቤቱም፣ እንግዳው የሚፈልገውን ያህል ማገዶ ሊያቀርብለት እንደሚችል አረጋገጠለት። ወጣቱ ሰው ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ በቁር ሲቆራመድ የቆየ በመሆኑ፣ የትዝታ ስሜቱም እየዘቀዘቀ ስለነበረ፣ የተነገረውን ዋጋ ተስማምቶ የአራት ቀን ሂሣብ በቅድሚያ ከፈለ። ባለሁለት ክፍል የሆነውን ሻንጣውንና የመድሃኒት ሳጥኑን ለመውሰድ ወደ ጄስዊቶች መኖሪያ ተመልሶ ሄደ። እዚያም፣ ከነርሱ ዘንድ እንደሚወጣ፣ ነገር ግን ፈረሱን ብቻ እንዲጠብቁለት ነገራቸው። አባ

ፕላንቴይን፣ እንዳይወጣና እንዳይሄድ እጅግ አጥብቀው ሞከሩ። ፖንሴ ግን በየዕለቱ ማለዳ በትምህርት ቤቱ አካባቢ በመቆየት ከንጉሡ ጋር ለሚኖራቸው ስብሰባ ይጠሩ እንደሆን ወሬ እያዳመጠ እንደሚቆይ ቃል በመግባት ጥያቄአቸውን ሳይቀበለው ቀረ። ከዚያም ወደ ሌ ብዩ ኖይሬ በመመለስ እስኪጠግብ ድረስ በቂ እራት በልቶ ውስጥ አካሉን በጣም በሚደነቀው የባርጋንዲ ወይን አሞቀው። የማወቅ ጉጉት ያለው የሆቴሉ ባለቤት፣ ጨዋታ ፈልጐ ቀረበው። ጆን ባፕቲስትም፣ ከካይሮ እንደመጣና የፈውስ ሃይል ባላቸው እፅዋት እየተጠቀመ ሰዎችን የማዳን ሥራ እንደሚሠራ ነገረው።

«ሐኪም ነሃ፣ እንግዲያው!» አለ የመጠጥ ቤቱ ባለቤት በአክብሮት ጐንበስ እያለ።

«ከሞላ ጐደል።» አለ ፖንሴ፣ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ጥያቄን ጉዳይ ላለመቀስቀስ አስቦ

«ኦ! ጌታዬ ሙሉ በሙሉ እንጂ፣ ያለ ስህተት ሙሉ በሙሉ። ከሕክምና ትምህርት ቤት የሚወጡትን እነዚያን ጨካኞችማ አውቃቸዋለሁ። ሊገድሉን እንኳ ባለ በሌለን ላይ ይደራደሩናል። ወዳጄ፣ እኔ በዕፅዋት ተአምራዊ ሃይል በተለይም ከምስራቅ በሚመጡት ላይ እምነት አለኝ»

ጆን ባፕቲስት ነገሩ እንዳይሰፋ ወይም ሰውዬውም ወሬውን እንዳይቀጥል ለማድረግ ተጠንቅቆ፣ ጨዋታውን አልቀጠለም። ወደ ፎቁ እየወጣ ሳለ፣ የሆቴል ቤቱ ባለቤት ሙያውን ከአንዱ ጠረጴዛ ወደ ሌላው እያደነቀ ሲነዛ ሰማው። የአክብሮት አይኖችም ዱካውን ተከተሉት።

ይህ ሥራ ደንበኞችን ይስባል ብለን ተስፋ እናድርግ፣ ሲል አሰበ። እዚህ ከተማ በሚታየው የገንዘብ አወጣጥ፣ የያዝኩት ክረጢት ሙሉ የወርቅ ብናኝ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቀልጦ ይጠፋል። ለዚያውስ እዚህ ምን ያህል እንደምንቆይ ማን ያውቃል? ሲል አሰበ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ጄስዊቶች እጆቻቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም። እስፔይን ውስጥ ያጋጠመው ታላቅ ጉዳይ ቤተመንግስቱን ግርግር ውስጥ ስለከተተው፣ የንጉሡን ስሜት ሙሉ በሙሉ ይዞባታል። ይሁን እንጂ ቀሣውስቱ፣ የኢትዮጵያን ጉዳይ በከፍተኛዎቹ መሪዎቻቸው በኩል የማሰማት ዕድል ለማግኘት ጊዜአቸውን ሁሉ በማሣወቅ ስራ ላይ እያዋሉት ነበር። በፈረንሣይ ውስጥ ለሚገኙት ለብዙዎቹ ታላላቅ ሰዎች የንስሃ አባቶች የሚሆኑት የእየሱስ ማህበረሰቦች ንጉሡንም ይጠቀልላሉ። በዚህም የተነሣ፣ በተረት የተሰበጠው የአቢሲኒያ የተልዕኮ ቡድን የጀግንነት ጉዞና ዘመቻ ወሬ፣ በመቶዎች በሚቆጠሩ ታላላቅ ቤቶች ውስጥ



እንዲሰራጭ አደረጉ። ለነዚህ ታማኞች ብዙ የእራት ግብዣዎች በየታላላቁ ሰው ቤት ተዘጋጅቶላቸዋል። ፖንሴ ግን፣ የራሱን ታሪክ ከሁሉ በፊት ለንጉሡ ማሰማት አለብኝ በሚል አቋም የእራት ግብዣዎችን ሣይቀበል ቀረ። ይህን ጠባዩን፣ አባ ፕላንቴይን ደከም ባለ ወቀሣ ይነግሩታል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ ቄሱ፣ ወደነዚህ ስመጥር ቤቶች ብቻቸውን በመሄዳቸው ታላቅ ክብር ይሰማቸው ነበር። በተመስጦ በሚያዳምጧቸው ሃብታሞች፣ ባለማዕረግ ሰዎችና በውብ ወይዛዝርት መሃል፣ በአጭሩ በሚያንፀባርቁ የሕብረተሰቡ አባላት መሃል መገኘታቸውን፣እንዲህ ባልተቋረጠ ሁኔታ ሲጋበዙ፣ ፈረስ ነጋዴዎች የነበሩት ቅድመ አያቶቻቸው ቢያዩዋቸው ኖሮ እጅግ ይኮሩ ነበር። ቀሣውስት በአጠቃላይ የሚደነቁበት ነገር ቢኖር፣ በተአምር ላይ ብዙ ማለት መቻላቸው ነው። ከፖንሴና ከአባ ዱ ብሬቬደንት የጉዞ ታሪክ ከሚያውቁት ትናንሽ የታሪክ ቃርሚያዎች፣ አባ ፕላንቴይን የሚያቀነጠንጥ ታሪክ ይሰሩበታል። በትረካቸው ጊዜ የሚዘልሏቸው ጉዳዮች የራሣቸው ሌላ ድንቅ ተአምር ይሆኑና በድል አድራጊነት ሃሣብ ሲቋጐ፣ሐቀኛ አማንያን ከሆኑ መላው መኳንንት ጋር ያቀራኙታል። ታሪኮች፣ ደግመውና ተደጋግመው በመሣፍንቱ ዙሪያ በመነገራቸው የተአምርነትን ክብር ሲይዙ፣ ፖንሴ ከዕይታ ውጭ ሆኖ ቆየ።

ይህ ሁሉ ሲከናወን ጆን ባፕቲስት፣ ሌ ቢዩ ኖይሬ ሆቴል ውስጥ አብረውት እራት ከሚበሉ ሰዎች ጋር እግሮቹን በእሣት ማንደጃው አጠገብ አድርጐ ካርታ ይጫወታል። ይህም ካልሆነ፣ በቱ ኢሌሪየስ መናፈሻ ውስጥ ለመንሸራሸር ፀሐይዋ ብልጭ ስትልለት ይወጣል። ከዚያም መስኮቱ ላይ ያለውንና የዘራውን የቆንጥር ፍሬ ውሃ ለማጠጣት ይመለሳል። ወደዚህ ሆቴል የገባ ዕለት የመጀመሪያው ታካሚ ህመምተኛ መጣለት። ሕመምተኛው፣ የአንዲት ምግብ አሣላፊ ሴት ልጅ ሲሆን፣ ያመጣውም የሆቴሉ ባለቤት ሙሴ ራኦል ራሱ ነበር። ሕፃኑ ከባድ የጉረሮ ምርቀዛ አለበት። ጆን ባፕቲስት፣ ትንሽ መድሃኒት ሰጥቶት ካከመው በኋላ ክፍያ ሳይቀበል ቀረ። ከሁለት ቀን በኋላ፣ ሕመምተኛው ህፃን፣ ተፈጥሮ በራስዋ መስመር ያለድጋፍ እንደምታደርገው ሁሉ፣ በእግሮቹ ቆመ። ሐኪሙ፣ ይህን ጉዳይ ለራሱ ውለታ እንዲሆንለት ለማድረግ ቻለ። ዝናው ወዲያውኑ ናኘና ከዚህ ሥራ ጥቂት ትርፍ ማግኘት ጀመረ።

በዚህ ዓይነት በዋና ከተማው ውስጥ በቆየበት በመጀመሪያው ሣምንት ውስጥ፣ ጆን ባፕቲስት ሁለት በጣም የተራራቁ ዝናዎችን አተረፈ። በማያውቁት መሣፍንትና መኳንንት አካባቢ አምባሣደር ነው ተብሎ ተመሰገነ። ሁለተኛም፣ ጊዜውን በሚያሣልፍበት የድሆች

መኖሪያ አካባቢ ፈዋሽ ተባለ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ሦስተኛም የሚገባው ዝና ነበረው፡፡ ይህኛውን ግን እርሱም አያውቀውም ነበር፡፡ ቢያውቀው ኖሮ ግን ቅር ይሰኝበት ነበር፡፡ የቤተመንግስቱ ስብሰባ በመዘግየቱ የተነሣ በሙሴ ዴ ማይሌና በካፑቺኖዎች የተፃፈው ደብዳቤ፣ የመንገደኞችን እግር ተከትሎ በመድረሱ የነርሱን ዝና መናድ ጀመረ፡፡ ሚኒስትሩ ዴ ፖንቻርትሬይን፣ እነዚህን ሰዎች በተመለከተ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ስለደረሰውና ግንኙነታቸውን ከጀስዊቶች ይልቅ ለሮማ በሆኑ ካህናት፣ እስካሁን የተከናወነው የኤምባሲ ጉዳይ የፈጠራ ሥራ እንደሆነና ፖንሴም አስመሣይ አጭበርባሪ ነው የሚል ወሬ አናፈሰ፡፡

ምንም እንኳ እስከአሁን በጣም ጠንካራ መሠረት ባይዝም፣ ይህ አስከፊ እንቅስቃሴ መቀጨት ይገባዋል ሲሉ አባ ፕላንቴይን አሰቡ፡፡ ከንጉሡ ጋር ሊኖር የሚችለው የስብሰባ ግንኙነት ለጥቂት ጊዜ ሊከናወን ባይችል፣ እስከዚያው ድረስ መጠበቁ ግን ጅልነት ይሆናል፡፡ ግርማዊ ንጉሥ ነገስት፣ የልጅ ልጃቸው ወደ እስፔይን እንዲነግሥ ዝግጅት እያደረጉ ሲሆን ምናልባትም ጥቂት መሠረታዊ የአገዛዝ ሐሣቦችንም እየመዘኑት ይሆናል፡፡ ስለዚህም አባ ፕላንቴይን በትምህርት ቤቱ አጠገብ ወደ ሚገኘው መኖሪያቸው ፖንሴን ጠሩት፡፡ ሐኪሙም፣ በአንድ ማለዳ ሁለት ህመምተኞች ትቶ ደረሰ፡፡ ጉንጮቹ በቅዝቃዜው የተነሣ ገርጥተዋል፡፡

«ውድ ወዳጄ» አሉ አባ ፕላንቴይን ከአንገት በላይ በሆነ አነጋገር፣ «የሆኑ ቅናት ያንገበገባቸው ቡድኖች፣ አንተ ወደ አቢሲኒያ ያደረግኸው ጉዞ ሙሉ በሙሉ የፈጠራ ነው ብለው ለመናገር ወኔ አግኝተዋል፡፡ እኛ እንኳ በጥላቻ የተሞላውን ትችታቸውን በሃይማኖታዊ መስመራችን በሚገባ እናውቃቸዋለን፡፡ ይህን ስህተታቸውን አሁኑኑና በማያጨቃጭቅ መልኩ ማጋለጥ ይኖርብናል፡፡ ስለሆነም መልካም ፈቃድህ ከሆነ እንግዲህ እዚህ ደርሰናልና ንጉሡ የሰጡህን ደብዳቤ ስጠኝ፣ በእስቶኪዴ ሳስተረጉመውና የተረጋገጠ ሳስደርገው፡፡ ከዚያም በኋላ በጋዜጦች ላይ እንዲታተም በማድረግ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የዓላማችን እውነተኛነት እንዲሰራጭ እናድርገው»

የፖሪስ ግርግርና ሁካታ፣ ጆን ባፕቲስትን ሁሉም እንዲምታታበት አድርጎታል፡፡ ለመገናኘት ወደተቃጠረበት ወደ ቅዱስ ጃኩይስ ሲያመራ በፍጥነት እየሰገሩ የሚያልፉትን ሰረገላዎች፣ ግራጫ የለበሱ የንጉሡ የክበር ዘበኞዎች ስኳድሮንና ተኳኩለው የወጡ ወይዛዝርትን ፈዝዞ ሲመለከት፣ ከጀስዊቶች ጋር ያለውን ተልዕኮ፣ በተለይም ሊይዘው ይገባው የነበረውን ደብዳቤ ፈፅሞ ረስቶታል፡፡ በርግጥ ይህ ደብዳቤ የሚባለው ከአንድ ቁራጭ ወረቀት



የማይበልጥ፣ ለዚያውም እርሱ ራሱ የፃፈው ሆኖ በእሣት መቀስቀሻ ሰም አቅልጦ እንደማህተም የሠራው ነው፡፡

«የንጉሡ ደብዳቤ?» አለ አይኖቹ ቡዝዝ እንዳሉ፡፡ ከዚያም ትዝ አለው፡፡ «አ! አዎን፡፡ ይቅርታ ያድርጉልኝ፡፡ ይህ ቅዝቃዜ አዕምሮዬንም አደንዝዞታል፡፡ አዩ አባቴ፣ ይህ የማይቻል ነው»

«ለምን ቢሉ?»

«ጠፍቶብኛል»

መብረቅ ወርዶ ክፍሉን ቢመታውና ኮርኒሱንም ለሁለት ቢከፍለው ኖሮ ይህን ያህል አባ ፕላንቴይን የሚናገሩትና የሚሉት አያጡም ነበር፡፡

«እንዲህ በቀላሉ! ጠፋ ነው የምትለው፡፡ ለመሆኑ የምትናገረው ምን ሊሆን እንደሚችል ትገነዘባለህ?»

ከዚያም፣ ጥቁር ዘርፋፋ ቀሚስ የለበሱት ሰው፣ ራሣቸውን ከተቆጣጠሩ በኋላ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገሩ፡፡ «ና፣ ና፣ ና! ልታገኘው ይገባሃል፡፡ የምትለው ሁሉ ሊሆን አይችልም፣ በቃ ሊሆን አይችልም፡፡ በሁሉም ዕቃ ውስጥ ፈልገው፡፡ መመለስ ካለብህም አይኖችህን መሬቱ ላይ ተክለህ እስከማርሴይ ድረስ ትሄዳለህ»

«አይሆንም» አለ ፖንሴ፣ በትንሿ ታሪኩ ላይ ጉዳዩን ሊዘጋ ፈልጎ፡፡ «ይመኑኝ፣ ምንም አያደርግልንም፡፡ የጠፋብኝ ደግሞ በጀልባው ላይ ነው»

«ወደ ማርሴይ አንድ መልዕክተኛ እንላክ፡፡ ጀልባው እስከአሁን ድረስም ምናልባት እዚያው ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም እንዲያቆመው ሊያደርግ የሚችል ሌላ ፈጣን ጀልባ ልንልክ እንችላለን»

ጆን ባፕቲስት ጭንቅላቱን አነቃነቀ

«እየነገርኩዎት፣ ጥቅም የለውም»

አንድ ወንበር ሳብ አደረገና በጉን በኩል አንዱን ክርኑን በጀርባው በኩል አሣርፎ፣ መጠጥ ቤት ውስጥ ያለችግር እንደሚዝናና ሰው ተቀመጠበትና የሚከተለውን ታሪክ ነገራቸው

«ሣርዲኒያን ዞረን ልንጨርስ ስንል ነበር፡፡ እርስዎ እንደተለመደው በመርከቡ ፊት ባለው ክፍል ውስጥ እንደነበሩ በሚገባ አስታውሣለሁ፡፡ እንደሚመስለኝ ይፀልዩ ነበር፡፡

የለም፣ ምሣሌዎችን ያነብቡ ነበር። አዎን ልክ ነኝ። ምሣሌዎችን ያነብቡ ነበር። የባህሩ ወለል ቢያንስ ሦስት ጫማ ርዝመት ያህል ባለው ትልቅ አሣ እንቅስቃሴ መስመር ያበጃል፡ ስንመለከታቸው የሚከተሉን ይመስል ነበር። ወደ ምግብ ማብሰያው ክፍል ወርጄ የደራረፋ የዳቦ ቅርፊቶች በማምጣት አቅጣጫቸውን ሳስለውጣቸው እችል እንደሆነ ለማየት ወረወርኩላቸው»

«እናስ?» ሲሉ ጄስዊቱ ይበልጥ እየከፋቸው

«እንደገመትኩት ሠራልኝ! አሦቹ አቅጣጫቸውን ለወጡ! ወደ ዳቦው ቀጥ ያለ መስመ ሰሩ»

«ከአሣህ ጋር ዲያብሎስ ይውሰድህ» አሉ አባ ፕላንቴይን «እና ደብዳቤው ምን ሆነ»

«ከኪሴ ወደቀብኝ»

«መርከቡ ወለል ላይ»

«አይደለም ውሃው ውስጥ»

ካህኑ ራሣቸውን ለማረጋጋት እጆቻቸውን በሾላው ጣውላ ጠረጴዛ ላይ አሣረፉ

«እናም ከነዚያ ውስጥ ሶስት የሚሆኑ ጭራቆች ወረቀቱ ላይ ሲራኮቱና ወረቀቱ ብጭቅጭቅ ሲያደርጉት አየሁኝ ብልዎ ያምኑኛል፣ አባቴ» አላቸው ፖንሴ እየተሟሟቀ

ጄስዊቱ እጃቸውን ልባቸው ላይ አሣረፉ። የሚተነፍሱ አይመስሉም።

«እና ምን ገጠመዎት አባቴ፣ አመምዎት እንዴ» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቃቸው።

ጄስዊቱን በራሱ ወንበር ላይ እንዲቀመጡ ካደረጋቸው በኋላ፣ አንድ አገልጋይ ከስኳር የሚዘጋጅ አንድ ብርጭቆ ጠንካራ የአልኮል መጠጥ እንዲያመጣ አዘዘ።

አባ ፕላንቴን፣ ወዲያውኑ ጠንካራ ጣውላ ሆነው ከድንገተኛው ሕመማቸው ተሻላቸው። ፕላንቴይንን ሊረዷቸው የመጡ ሌላ ቄስ፣ ሕመምተኛው እርሱን ሲያዩት የስሜት መረበሽና ቁጣ የሚፈጠርባቸው መስሏቸው፣ ፖንሴ ለቅቆ እንዲወጣ ምልክት ሰጡት።



እስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ ጆን ባፕቲስት የሚመርጣቸው ታካሚዎቹ ቤት የለሾችና ሥራ አጥ በመሆን ብሉ ቢዩ ኖይሬ ውስጥ አባቢዎች ከሆኑት መካከል ነበር። የሆቴሉ ጥቂት ክፍሎች የተከራዩት ለአነስተኛ ነጋዴዎችና በማይታወቅ ሥራ ላይ ለሚዞሩ የውጭ አገር ሰዎች ነው። መጠጥ ቤቱ በጋሪ ነጂዎች፣ በወታደሮችና በአቅራቢያው ባለው ቦታ ላይ የሚሠሩ ወዝ አደሮች ባለማቋረጥ እንደተሞላ ነው። ሙሴ ራኦል፣ በወዳጃዊ ሁኔታ ሰላምታ ያቀርብላቸዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ከፕላንቴይን ጋር ከነበረው ግንኙነት በተመለሰ ምሽት፣ የሆቴሉ ባለቤት ይጠብቀው ነበር። ወደ አንድ ተአምረኛ የሆነ ሕመምተኛ ቤት ሊወስደው ስለፈለገ ስለህመምተኛው ሲናገር እንኳ በአክብሮት እሸሸ ይላል።

የሰውዬው መኖሪያ በዚያው መንገድ ላይ ነበር። እንዲያውም ከመጠጥ ቤቱ በቀጥታ ባሻገር ነው። የመኖሪያ ቤቱ ፊት ለፊት የድንጋይ ሕንፃ ከፍታ፣ ግልብጥ የሚል ከሚመስለው ግማሽ የጣውላ ስሪት ከሆነው ከሌ ቢዩ ኖይሬና በዙሪያው ካሉ ደሣሣ ጎጆዎች ጋር ተቃራኒ ነው።

«ከግማሽ ምዕተ አመት በፊት» ሲል ባለ ሆቴሉ ቀጠለ «ንጉሡ በጠመንጃም ይሁን በጕራዴ መፋለምን ህገወጥ ከማድረጋቸው በፊት፣አሁን የምወስድህ ቤት ፖሪስ ውስጥ ታላቅ የሻቦላ ግጥሚያ ማዕከል ነበር።»

«ኧረ! እንዲህ ከሆነማ ጕራዴዬን ማምጣት ነበረብኝ!»

«በዛሬው ዘመን እንዳችም የሚያስፈራ ነገር የለም» አለ ሙሴ ራውል ወደ ሕመምተኛው ቤት ከመድረሳቸው በፊት፣ ለፖንሴ ጥቂት መረጃዎች ለመስጠት እያስቀመው፣ «ቤቱ እጅግ ለተከበረና በፖርላማው ውስጥ ለረዥም ዘመናት ሕግ አውጭ ሆኖ ይሠራ ለነበረ ከበርቴ ነበር የተሸጠው። ባለቤቱ፣ ከሃያ ዓመቶች በፊት በወረርሽኝ ሳቢያ ሞታበታለች። ይህ አጋጣሚ ሰውዬውን በእግዚአብሔር እንዳያምን አድርጎታል ብለው ያወሩበታል፣እኔ ግን አላምንም። በጣም እርግጠኛ የሆነው ግን ሁለቱን ልጆቹን በሚገባ ማሣደጉ ነው። ልጆቹ በአሁኑ ጊዜ ያደጉ ስለሆኑ እዚህ የሚመጡት አልፎ አልፎ ነው። ሴት ልጁ፣ የውጭ ተወላጅ ስላገባች፣ የምትኖረውም ውጭ አገር ነው። ወንድ ልጁ በኢስት ኢንዲስ ክፍለ ጦር ውስጥ በማገልገል ላይ ነው። ሰውዬው አሁን የሚኖረው ብቻውን ቢሆንም፣ ፍልቅልቅ ፀባይ ስላለው በመኖሪያ ቤቱ ውስጥና አልፎ አልፎም ወጣ እያለ መዝናናት ይወዳል። ባለፉት ስድስት

«አነጋግረሽው ነበር?» አለች አሊስ፣ ወደቡ ዳር ተቀምጣና ከጉንዋ ያለችውን ጓደኛዋን እንድትቀመጥ እያደረገቻት።

«አዎን አነጋግሬዋለሁ። ሁሉንም ነገር እስከአሁን ድረስ ገምተሽ ቢሆንም እነግርሻለሁ። እዚህ ወደብ ላይ አሣ የሚያጠምድ በመምሰል ቀኑን ሙሉ ወደኔ ለመምጣት ሳይችል እንዴት እንደሚውል ባየሽው። ትናንት ከሰዓት በኋላ ስሄድ፣ ሁልጊዜም ለቁርጥማት ሕመሙ በማለት የአባትሽን አንድ ጠርሙስ ብራንዲ ከእጁ የማያጣውን ሚካኤልን አግኝቼው ነበር። እኔም ሁለት ዋንጫ ሙሉ ጠጥቼ ወደዚሁ መጣሁ። እኔ መድረሴን እስከሰማበት ድረስ፣ ዠረሚ ፍፁም አንድም ነገር አይሠራም ነበር። ከዚያ በኋላ የማጥመጃ ገመዱን መሣብና ከመንጠቆው ጋር መታገል ጀመረ። ሄጄ ከጐኑ ተቀመጥኩ። አጉረመረመ። እመኚኝ፣ ፈራሁ። መዋኘት ባልችልም ውሃው ውስጥ ዘልዬ ልገባ ነበር። በኋላ ተናገረ። ያ ድምፁ እንዴት እንደሆነ ታውቂው የለ? እንዴት ጭንቀት እንደተሰማኝ ቢገባሽ? አንዳች ነገር ልናገር ስል ያ ከበሮ ድምፅ ጆሮ ግንዴ ላይ ይደልቅ ጀመር።»

«እርሱስ ምን አለ?»

ፀሐይዋ ከፍ ብላለች። የወንዙ ዳርቻዎች ብሩህ መሆን ሲጀምሩ፣ ውሃውም ጠቆር ብሏል። የውሃ ዳር ወፎችም በርረው ሄደዋል።

«ፍራንቸይዝ ሲል ጀመረ። ስሜን ሲጠራው የተሰማኝን ሁኔታ ልነግርሽ አልችልም። «ፍራንቸይዝ፣ ልትነግሪኝ የመጣሽበትን ጉዳይ አውቀዋለሁ። መነጋገሩ ፋይዳ የለውም። አየሽ፣ ወላጆቼ እምነታቸውን በመለዋወጣቸው አሰቃቂ መከራ ተቀብለዋል። ይህንን አንዳችንም አላደረግንም። ይህ ደግሞ የሃይማኖት ጥያቄ ጉዳይ አልነበረም። ሐቁ ተመልሰን ያለፈውን ሕይወታችንን ለመጀመር አቅሙ አልነበረንም። አየሽ፣ እኔ በበኩሌ የራሴን ሰጥቻለሁ» ለአፍታ ያህል ንግግሩን ገታ አደረገው። የማጥመጃ ገመዱንም አስቀመጠውና እጆቼን በእጆቼን ላይ ጫናቸው። ከዚያም «ሕይወት ከቃል ኪዳኔ ልትፈታኝ ትችላለች ብዬ አስባለሁ። ያን ጊዜም ነፃ እሆናለሁ። ያን ጊዜ ቀሪውን ሕይወቴን በሙሉ አንቺ ፈቃደኛ ሆነሽ ልትቀበይኝ ከቻልሽ ቃልኪዳኔን የምሰጠው ላንቺው ነው።»

ፍራንቸይዝ ልቅሶዋን ለቀቀችው። አሊስ፣ እጆችዋን በእጆችዋ ውስጥ ይዛ ልታበረታታት ሞከረች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁለቱም ተያይዘው ወደ ቤት ወጡ።



ይህ ማለት ለርስዋ ደስታ ማለት መሆን አለበት። ግን ምን አይነት ያልታደሉ ፍቅረኛሞች ናቸው፣ ስትል አሊስ አሰበች።

ከጆን ባፕቲስት ጋር ያሣለፈቻቸውን አጭር ጊዜያት መለስ ብላ ተመለከተች። እርሷም ብትሆን ባልተለመደ ሁኔታ ደካማና የማያስደስት የሚመስል ስዕል ነበራት።

ቬርሣይለስ ውስጥ በብዙ የሚወደዱ ወይዛዝርት መሃል ሆኖ፣ ከቶውንም እንዴት ሊያስታውሰኝ ይችላል ስትል አሰበች።

ይህ ሃሣብ በሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ እንድትረታ ሊያደርጋት ሲችል፣ አሁን ግን ፈጣን ግልቢያ እንድታደርግ ቀሰቀሳት።

❦

የሆቴሉ ባለቤት፣ ስለምክር ቤቱ አባል ሮበት ፖሞት ዱ ሣንግራይ የሰጠው አጭር መግለጫ ትክክል ነው። ሰውዬው በተፈጥሯቸው ፍልቅልቅ ከመሆናቸውም በላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲሆኑ ደስተኛ ናቸው። በተለይም ሕመሙ ከለቀቃቸው በኋላ የርሣቸው መገለጫ የሆኑት መልካም ባህርያቶች ሁሉ ጐልተው መውጣት ጀምረዋል። ለጆን ባፕቲስት ምስጋና ይግባውና ይኸው ለመጀመሪያ ጊዜ የሕመማቸውን ስቃይ የሚከላከሉበት መሣሪያ አግኝተዋል። ይህም ሳይሆን ቢቀርና የአጭር ጊዜ ከስቃይ የመዳን ዕድል ቢሆንላቸውም እንኳ፣ ለጆን ባፕቲስት ታላቅ ውለታ አለባቸው። የተሰጣቸው ሕክምና የሕመሙን ምልክቶች ረዘም ላለ ጊዜ አስታገሰላቸው። ጊዜ ባለፈ ቁጥር የመዳን ስሜታቸው እርግጠኛ እየሆነ መጣ። በዚህ ምክንያት ለምስጋናቸውም ወሰን አልነበራቸውም። ከዚያም፣ መድሃኒት ቀማሚው፣ ፖሪስ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ መክረሙ እንደማይቀር በማሰብ፣ የዚህን ቆይታውን ወጭ በሙሉ እንደሚሸፍኑለት አረጋግጠው ሠላሣ የወርቅ ኤኩስ ሰጡት።

አንዳንድ ጊዜ፣ ታላቅ ርህራሄ በሰዎች ውስጥ ያለውን ጥርጣሬ ሁሉ ያስወግዳል። የሃብታሙ ሰውዬ ወዳጅነት፣ በጆን ባፕቲስት አይኖች ሲታይ ለአገልግሎቱ በቂ ክፍያ ነበር። ያንሰኛል ብሎ ቢጠይቅ እንኳ የራሱ ስሜት ይጐዳበታል። በዚህ ሳቢያ የተሰጠውን የገንዘብ ቦርሣ ተቀብሎ ከዚህ በኋላ ምንም እንደማይቀበል አረጋገጠ።

ጆን ባፕቲስት፣ በየዕለቱ ከሰዓት በኋላ እየመጣ ሕመምተኛውን ይጐበኛቸዋል፡ የመንቀሣቀስ ነፃነታቸው የተመለሰላቸው ዱ ሣንግራይ፣ በከተማው ውስጥ ሲዞሩ እየዋሉ ወደ ቤት የሚመለሱት በየዕለቱ ላላቸው ውይይት ሲሉ ብቻ ሆነ። በዚህ ሳቢያ እንደእውነቱ ከሆነ ማን ማንን እንደሚጐበኘም ግልፅ አልነበረም ማለት ይቻላል። አንዳንዴ ሐኪሙና ሕመምተኛው ከተለያየ አቅጣጫ በመምጣት በሩ ላይ የሚገናኙበትም ጊዜ ነበረ። ውይይታቸውና ጭውውታቸውም ከሕመም ጉዳይ አልፎ፣ በሁለት ጓደኞች መካከል እንደሚኖር ነፃና የፈለጉትን ጉዳይ እያነሱ ወደ መነጋገር ደረጃ ዓይነት ደረሰ።

«እንዲያው ልጠይቅህና፣ ለምን እዚህ ቤት ውስጥ አትኖርም? ሌ ቢዩ ኖይር ጥሩ መጠጥ ቤት ቢሆንም፣ ከሁሉም አቅጣጫ እንደሚሰማው ደስ የማይል ሆቴል ነው» ሲሉ በአንድ የሣምንት ማብቂያ ዕለት አማካሪው ጠየቁት።

«በመጀመሪያ ነገር ሁለታችን እንድንገናኝ ያደረገንን የሆቴሉን ባለቤት ውለታ መርሣት ይሆናል»

«ከርሱ ጋር ያለውን እኔ አስተካክለዋለሁ። በርግጥ ምግብህን ማቅረቡን ይቀጥላል። እኔም ብሆን፣ የፍራንቾይዝን መረቅ የመፈለጌና የመጋቴ ነገር እያበቃ ስለሆነ፣ ለኔም ጭምር ምግብ እንዲያመጣ እነግረዋለሁ። በዚህ ሳቢያ ጥሩ ደንበኞቹ ሆነን እንቀጥላለን። በሌላ በኩል፣ በዚህ ወቅት ባሉት ትርኢቶች ሳቢያ ያንተን ክፍል ወዲያውኑ ያከራየዋል።» .

ጆን ባፕቲስት ተስማማ። አማካሪውም፣ አንድ የመኝታ ክፍል በፎቁ ላይ እንዲዘጋጅለት አዘዙ። ክፍሉ፣ ሙሉ ዕቃ የገባለትና ቀለል የሚል ነበር። በፊት ለፊቱ በኩል፣ሥራ ብዙ ወደሆነው መንገድ የሚያሣዩ ሁለት ረዣዥም መስኮቶች አሉት። ከዚህም በላይ፣ አማኒያን በየበረንዳው ስር ወደ ቅዱስ ኢዩስታች ቤተክርስቲያን ሲመጡና ሲመለሱ ይታይበታል። በኢጣሊያ እምነበረድ የተሰራው ትልቅ የጢስ ማውጫ ባለመደፈኑ፣ እሣት ግር አድርጐ በማንደድ ራሱን ማሞቅ እንደሚችል በማወቁ ጆን ባፕቲስት ተደሰተ። ቤቱ በጀርባ በኩል የመኝታ ክፍል፣ ሁለት ትንንሽ ክፍሎችና ለስሙ ያለውን ሽንጣውን፣ የመድሃኒት ቦርሣውንና የገዛቸውን ጆሮዎች የያዘበትን ሳጥን ሊያስቀምጥ የሚችል ቁምሣጥን አለው።

«ይህን የከተማ ቤት ስገዛው፣ ለአስር ዓመት ያህል ተዘግቶ የኖረና ለባለቤቶቹም እጅግ የሚጠላ ነገር ሆኖባቸው የነበረ ቤት ነበር።» ሲሉ እንግዳቸውን ለማየት የመጡት ሳንግራይ ተናገሩ።



«ሰዎች እዚህ ይፋለሙ ነበር መሰለኝ?»

«ክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ የጠራ ክብር አለን ለሚሉ ሰዎች የመገናኛ ቦታቸው ነበረ። በክብሯቸው ላይ ማንም ሰው ጥርጣሬ አልነበረውም። ነገር ግን የጥራቱ ጉዳይ፣ የማያላውሱ ሕጐች ነበሩበት። ሕጐቹንም እነርሱ ለሚያከናውኑት የግፍ ግድያ ሲሉ ራሣቸው ያወጡት ነበር። እዚህ ያለውን ተራ ጭሰኛ አስበው። ዶ ሞንት ሞሬንቺያ ቦቴቪል የተባለው ባለስልጣን፣ በሃያ ሰባት ዓመት ዕድሜው ሃያ ሁለት ጊዜ ፍልሚያ አድርጐ ነበር። የመጨረሻው ፍልሚያውን ያደረገው በሪቼሊዩ የከተማ ትልቅ ቤት ውስጥ ነበር። በዚህ ዕለት ማለትም ልክ በበጋው አጋማሽ ዕለት ሐምሌ 24 ቀን በዚሁ ፍልሚያ ላይ ታረደ»

«አክራሪ ገድል ነው» ሲል ፖንሴ ተቁነጠነጠ

«እንደዚያ ታስባለህ?»

«አዎን፣እነዚያ ሰዎች በዕውነት የኖሩ ነበሩ? ብዬ አስባለሁ»

«ብዙ ጊዜ ግን ይሞታሉ። ሌሎችንም ይገድላሉ። ሁሉንም ነገር እስከዛሬ ድረስ በሚገባ አስታውሣለሁ። የፍሮንዴ አሰቃቂ ግድያ ትዝ ይለኛል። በሕዝባዊው ንቅናቄ ጊዜ ገና ሕፃን ነበርኩ። ሆኖም ግን፣ በወቅቱ፣ ሃይል ሕዝቦችን ይገዛ የነበረበትን ትርምስ ፈፅሞ አልረሣውም። የለም፣ አየህ ዶክተር፣ እኔ የሕግ ሰው ነኝ። የሚዛን ሰው ነኝ። ራሴን ሳስበው የነዚያ አውሬ መናፍስት ጠባቂያቸው ሳልሆን አሣሪያቸው እንደሆንኩ ነው»

ከመጀመሪያ ጀምሮ እኒህን በትዕግስት የተሞሉና ሁሉንም ነገር በነፃ አዕምሮ የሚቀበሉ ጨዋ ሰው፣ ጆን ባፕቲስት ትልቅ እምነት አሣድሮባቸዋል። ወደ አቢሲኒያ ያደረገውን የጉዞ ታሪክ ነግሯቸዋል። ትረካውን ሁለቱም ሰዎች የድመት የመሰለ የእግር ቅርፅ ባለው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ሆነው፣ እግሮቻቸውን ወደ ነሐሱ የእሣት ማንደጃ ዘርግተው ለብዙ አስደሳች ምሽቶች ዘልቋል።

እነዚህ ምሽቶች ካበቁ በኋላ ራሣቸውን በፅሁፍ ሥራ ላይ ለማሰማራት ወሰኑ። ሣንግሬይ ጀምረውት የነበረውን የተለያዩ የሰው ልጆች ሕጐችን ለማጠናቀቅ ተዘጋጁ። በሣንግራይ ማግባባት፣ ጆን ባፕቲስትም የጉዞውን ታሪክ በጽሁፍ ለማስፈር ወሰነ። ሥራቸውንም በሁለተኛው ቀን ጀመሩ።

አማካሪው፣ ከመፅሐፍት አጥኚ በላይ ናቸው። ሕመማቸው ፊፅሞ ከተዋቸው በኋላ ሕይወትን ሁሉ መፈተሽ ጀመሩ። በዚህም ያልዳሰሱት የደስታ መስመር አልነበራቸውም። በፖላስ ሮያሌ በተዘጋጀው የደመራ ምሽት ላይ የቻርትሬሱ መስፍን ያውቋቸው ስለነበረ ተጋብዘዋል። ማንግራይ ይህን የደስታ ምሽት ለመካፈል በጣም ደስ ስላላቸው፣ ጆን ባፕቲስትም አብሯቸው እንዲሆን በፈንታቸው ጋበዙት።

ሁለቱ ሰዎች በሰውነታቸው አቋም ቢለያዩም፣ ቁመታቸው ተመሣሣይ ነበር። አማካሪው፣ ለአንገዳው፣ በወርቅ ጥልፍ ያማረ ሙሉ ልብስና ያሸበረቀ የአንገት ፎጣ አዋሱት። ጋሪ ጭምር የሚያከራየው የሆቴሉ ባለቤት ሙሴ ራኦል፣ አንድ ሠረገላ ከነነጂው ላከላቸው። በጊዜ ለዕራት ለመድረስ ሄዱ።



# 5

በዚያን ዘመን የቤተመንግስቱን ሕይወት የሚያሣየውና፣ ፖሪስ ውስጥ በብቸኝነት የቀረው ፖላስ ሮያሌ ነበር። የተቀሩት የቤተመንግስት ተግባራት ሁሉ፣ በንጉሡ ዙሪያ እንዲሆኑ ተብሎ ወደ ቬርሣይለስ ተዛውረዋል። ፖላስ ሮያሌ ውስጥ እጅግ የደመቀ በዓል ቢደረግም፣ የሚያስፈራ አምባገነን የሌለበት ስነስርዓት ነበር። የቻርትሬሱ መስፍን፣ የንጉሡ የአጐት ልጅ ሲሆኑ በዙሪያቸው ለሚገኙት ሰዎች ሁሉ ፍቅርና ወዳጅነትን የሚያሣዩ ሰው ነበሩ። በዚህም የተነሣ በበዓሉ ላይ የነፃነት መንፈስ ሰፍኖ ነበር። እንዲህ ባለው ሞቅ ያለ የወዳጅነት ቦታ፣ እጅግ ውብ የሆኑ ዕፅዋት ከቬርሣይለስ ይልቅ እዚህ ይበልጥ ይደምቃሉ። እንደልብ በአንድ ላይ ሆነው የሚገኙት ውበት፣ ወጣትነትና ለዛ በዚያ ቦታ ቡበዙ ድንቅ ሰዎች ዘንድ፣ በተለይም በሴቶች ውስጥ ተዋህደው ይገኛሉ። ማንግራይ፣ አጃቢውን ከቻርትሬሷ ልዕልት ጋር አስተዋወቁት። ባለቤታቸው የቻርትሬሱ መስፍን ግን፣ የዚያኑ ዕለት ጥቂት ቀደም ብሎ፣ እነርሱ ከመድረሳቸው በፊት ወደ ቬርሣይለስ ተጠርተው ስለሄዱ ሊያስተዋውቋቸው አልቻሉም።

በአራት ሰዓትና ከዕራት በኋላ የነበሩት ጥቂት እንግዶች፣ በሣሎን ውስጥ ተሰብስበው በነበረበት ጊዜ፣ ፖንሴ ጥንቃቄውን በመጠኑም ቢሆን ላላ አደረገው። ውብ ሴቶች ያሉበት አንድ ቡድን በጥግ በኩል በዙሪያው ተከለከለ። ስለነዚህ ወይዛዝርት ማንነት የሚያውቀው አንዳችም ነገር ባይኖርም፣ ከሁሉም ታላቅ የሚሆኑትን አንዷን ሴት ግን፣ ማዳም ማርኩስ ብለው ሌሎች ሲጠሯቸው ሰማ። የጆን ባፕቲስት ድንቅ አቀራረብና የትንግርቶች መፍለቂያ ስለሆነው ስለዚህ ቦታ ማስረዳት በመቻሉ፣ አንዳች ተአምር የሆነ ነገር የተደበቀበትን ማሽተት የሚችሉበትን ልዩ ተሰጥኦና፣ ባላቸው የማወቅ ጉጉት የተነሣ ይህን አዲስና ያልተደመደ ነገር ሰብረው ለመውጣት ስለጓጉ፣ ሴቶቹ ፖንሴን መሣላቸው አስገቡት። እርሱም፣ እውነቱን ተናጋሪው እርሱ ብቻ ስለሆነ እነዚህ ድንቅ የቤተመንግስት ሰዎች ባሉበት፣ አክብሮታዊ ፍርሃትን ለማስወገድ ሲል በወጥመዳቸው ውስጥ ሆን ብሎ ገባላቸው። አቢሲኒያን ሲገልፃት ለራሱ ፍፁም ሥልጣን ሰጠው። የተነገረውም ነገር ብዙ ሺህ የአግራሞት ጥያቄዎችን አስነሣ። አንዱን እያነሣ ሌላውን እየጣለ በሚገለባበጠው ማህበራዊ ጭውውት፣ ጆን ባፕቲስት ይህን ውብና ማራኪ ነገር ከሚያስፈልገው በላይ በማስፋት ስህተት ሠራ። አቢሲኒያውያን

አብረቅራቂ ያለበት ትልቅ ጥቁር ደመና፣ በረዶ ለመጣል እያንገረበበ ሲሆን ብርሃኑን ሁሉ ውጦታል:: በቤተመንግስቱ መግቢያ ግንብ የሚጠብቁት ስዊሳዊ ዘበኞች፣ ሦስት እጥፍ በሆነ ክት ተጠቅልለዋል:: በቤተመንግስቱ ጣሪያ ላይ የሚገኙት ጭስ ማውጫዎች ሁሉ ጢስ ቢትጉለጉልባቸውም፣ እነዚህ እንግዶች በቅጥር ግቢው ውስጥ ማንንም አላገኙም::

የአየሩ ጠባይ ለጆን ባፕቲስት ተስማምቶታል:: እንዲህ ባለ ውብ ቀን፣ አብረቅራቂ የወርቅ ቅቦችና ጌጣጌጦች፣ የመናፈሻ ስፍራዎች ህብር፣ የሕንፃዎች ሽብረቃ የድል ብስራታቸውን የሚጭኑበት ይሆኑ ነበር:: ቢሆንም፣ ይህ ጢስ የሞላው ዋሻ አንዳች ትህትና ያለው ይመስላል:: ንጉሡ፣ ያላቸው የሚመስላቸው ታላቅነት ሁሉ፣ እርሣቸውም ለወቅቶች ሃይል ተገዥ ስለሆኑ ራሣቸውንና በጉጆአቸው ውስጥ ያሉትን ነፍሳት ሁሉ ከዚህ ከሚለዋወጥ ባለጌ ዝናብና ቅዝቃዜ መከላከል ይኖርባቸዋል:: በክረምት የቆፈን እጅ ውስጥ ያለችው ቬርሣይለስ፣ ለደስታና ለፈንጠዝያ የምትሆን ሳትሆን፣ ዜጐችዋ ሁሉ ለዘብ ባለው እሣት ዙሪያ በተራ የድንጋይና የሸክላ መጠለያዎች ውስጥ፣ ክረምቱ እንዲያልፍ ጆርባቸውን አጉብጠው የሚጠባበቁባት ከተማ ነች::

በታላቁ የእምነበረድ መውጣጫ ደረጃ በኩል ገቡ:: አድርጉ የተባሉትን ለማድረግ ፈቃደኞች የሆኑት ሰዎች፣ ቀለል ያለ ልዩ ልብስ ለብሰዋል:: እጆቻቸው በቅዝቃዜው ሰማያዊ ሆነውባቸዋል:: ትልቁና ረዥሙ የመወጣጫ ደረጃ፣ ሲራመዱበት የበረዶ ርጥበትና የሠምና የአስክሬን ሣጥን ሽታ ሲሸትት፣ ከበላዩ የታፈነ የገደል ማሚቶ ድምፅ ይመጣበታል:: ጉብኘ ዎቹ፣ ደረጃውን ጥብቅ በሆነ ሥርዓት ሽቅብ ይራመዱታል:: ከነርሱ መካከል አንድም እንኳ የወርቅ ቅብ የተቀባውንና የፅጌሬዳ ቅርፅ ያለውን የብረት መደገፊያ የደረሰ የለም:: ላይኛው ማረፊያ ላይ እንደ አጋጣሚ የሚያንሾካሹኩ አጃቢዎች አሉ:: የሚቀሰቅሣቸው ማንም ይሁን ማን፣ የጉብኚዎቹን መድረስ ግን፣ አንድም ያስተዋለው ያለ አይመስልም:: የመጨረሻውን ደረጃ ከወጡ በኋላ፣ ይህ ጥቂቶች ያሉበት ቡድን የሚቀጥለውን ደረጃ ሳያስቡት ሽቅብ ተመለከቱት:: አሁንም ገና በነርሱና በጣሪያው ኮርኒስ መካከል ብዙ ርቀት እየቀረ፣ የደረሱ የመሰላቸው ግራ የሚያጋባ ነው:: ልክ በዚህን ጊዜ፣ አባ ዴ ላ ቾይዝ እነርሱ ካላስተዋሉት መጋረጃ ውጥተው ተቀላቀሏቸው:: የማይማርክ የካህን ልብስ ለብሰው፣ ከጥቁር አብረቅራቂ ሃር የተሠራ ቆብ በጭንቅላታቸው ላይ ደፍተዋል:: ሰውዬው ባለማቋረጥ ፈገግ ይላሉ:: የማይለዋወጠው የፊት ገፅታቸው በመጀመሪያ ላይ የስሌት ሁኔታ መስሏቸው ነበር:: በኋላ ላይ ግን ፍርሃት ለቀቀባቸው:: ከአኳኋናቸውና ከአግበ ንግግራቸው፣ ሰውዬው በነገሮች



የመጨረሻ ሰዓት ላይ ታላቅ መሆናቸውን ለማሣወቅ የሚጥሩ መሆናቸው ይታወቅባቸው ነበር:: ለንቋሳው ቁመናቸው ከታላቁ ሕንፃ አኳያ ሲታይ እንከትክት ማለታቸው የማይቀር መሆኑን ያጋልጥባቸዋል:: ፖንሴን በአይናቸው ቂጥ በፍርሃት ይመለከቱታል:: ከሠረገላው ውስጥ ገና የሚወርዱና የሚመጡ ሁለት ሣጥኖች መኖራቸውን አባ ፕላንቴይን ለፖንሴ ሲነግሩት፣ አባ ዴላ ቾይዝ ደግሞ ሁለት ምን ልታዘዝ የሚሉ ሰዎችን ጠሩ:: ወዲያውም ካስተርና ቁርጥ ያለ ምልክት ሰጧቸው:: ይህ ድርጊታቸው በሰውዬው ውጫዊ የርጋታ ሰውነት ስር ዘልቆ ያለውን ጥላቻና ወዳጅነት አለመፈለግን ያመለክታል:: አባ ፕላንቴይንን ወደ ዳር ወስደቻቸውና ወደ አንድ ትልቅ የጌጥ ቅርፅ ማውጫ በመዞር፣ በዝቅተኛ ድምፅ የሆነ ነገር ነገሯቸው::

የንጉሡን የንስሃ አባት ተከትለው፣ የዘቦች ወደ ሆነው ወደ መጀመሪያው ክፍል አመሩ:: አባ ዴ ላ ቾይዝ፣ የመስኬቶ ጠመንጃ ሳነገተው ተረኛ መኮንን ሁለት ሰዎች ተሸክመው የሚያመጡት ሣጥን አለ ብለው ሲነግሩት ሳጥኑም ወዲያውኑ ደረሰ::

በመቀጠልም ወደ መጀመሪያው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ገቡ:: ይህ ሰፊ ክፍል፣ ንጉሱ በአብዛኛው እራት የሚበሉበት ነው:: የነሐስ ግድግዳ ብርሃን ይተፋል:: መስኮቶቹ፣ በመስተዋቱ ውስጥ ምንም ባያንፀባርቁም፣ እየባሰ የሚጠቁር ብርቱካንማ ሰማይ ይታይባቸዋል:: ኒየርት የተባለው ድንክ፣ አጭርና ሰው ሰራሽ ፀጉር ያጠለቀው የንጉሡ ቀደማይ የልፍኝ አስከልካይ፣ እንግዶቹን ለመቀበል በሩ አጠገብ ቆሟል:: ተከትለውትም ወደ ሌላ ክፍል ሄዱ:: ይህኛው ክፍል መብራት ባይበራበትም፣ ደብዘዝ ባለ ግራጫ ብርሃን የተሞላ ነበር:: በተቃራኒው ጐን፣ ገርበብ ያለና የሠላሣ ሻማዎች ከባድ ብርሃን እየተንቦገቦገበት ያለውን ራቅ ያለ ክፍል የሚያሣይ ባለሁለት ተከፋች በር አለ:: የልፍኝ አስከልካዩ፣ ከዙፋን ፊት የሚቀርቡትን ሰዎች በሰልፍ ካዘጋጃቸው በኋላ፣ በሩን ወለል አድርጐ ከፍቶ ለንጉሡ አቀረባቸው::

በዛሬው ዕለት እጅግ በመታመማቸው ምክንያት በመካከላችሁ ሊገኙ ባለመቻላቸው አዝነዋል። ይሁን እንጂ የቱርካውያን አገዛዝ ውስጥ ከሚገኙት አገሮች መካከል በተለይም በግብፅ፣ እኛን በመወከል ከባድ ሃላፊነት ተሸክመው ያሉትን አባ ፕላንቴይንን ሳቀርባቸው ታላቅ ክብር ይሰማኛል»

አባ ፕላንቴይንም ሰፊውን ግንባራቸውን እንደገና አንድ ጊዜ ዝቅ አደረጉና እጃቸውን ልባቸው ላይ አሣረፉ።

«እናም ግርማዊነትዎ በአርቆ አሣቢነትዎ፣ ወደ አቢሲኒያ የሚደረገው ተልዕኮ እንዲንቀሣቀስ ያዘዙትና የረዱትም ከዚህ አገር የተንቀሳቀሰ ነበር» ሲሉ የንጉሡ የንስሃ አባት ቀጠሉ። «በዚህች ያልታደለች የክርስቲያን አገር ውስጥም ጥሩ መሠረት ለመያዝ ድጋሚ ሙከራ ተደርጓል። እንዳለመታደል ሆኖ በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ፣በተሣሣተ አስተሣሰብ፣መናፍቃን በሚል ሰበብ ብዙ ወንድሞቻችን ተጨፍጭፈውበት ነበር። ልዑላን ሆይ፣ሕዝቦች ከስህተትና ከማይምነት ካልተላቀቁ በስተቀር ለዘለዓለሙ ተፈርዶባቸው፣ ተኮንነው፣ እንደሚቀሩ በማወቅ የኛ የሃይማኖት ሥርዓት ያከናወናቸውን እጅግ ከባድ ጥረቶች ታውቃላችሁ። መልካም ፈቃዳችሁ ቢሆን ስትመኙት የነበረውን ተልዕኮ በተመለከተ አባ ፕላንቴይን ጥቂት መግለጫ ይሰጣሉ»

ንጉሡ፣ የአረንጓዴውን ጃኬታቸውን እጅጌ ሰብሰብ አድርገው በመዳፋቸው መሃል በትንሹ አሣሉ። ምንም እንኳ እንቅስቃሴው በጣም ፈጣንና አይን የማይገባ ቢሆንም፣ ንጉሡ የአፋቸውን የቀኝ ዳርቻ በእጅጌአቸው ጨርቅ ጠርገው ሲጠርጉት ተመለከተ። ከንፈራቸውም በዚያ አቅጣጫ ጣል በማለቱ አፋቸው ሙሉ በሙሉ አልተከደነም።

«አባ፣ ይናገሩ። በዚህ ጉዳይ ላይ ትልቅ ፍላጐት አለን።» አሉ ንጉሡ

«ጃንሆይ» አሉ አባ ፕላንቴይን ግንባራቸው እየቀላ። «ይህን ጀግንነት የሚጠይቅ የሃይማኖታችንን ተስፋ ወደዚያ እሩቅ አገር ለማድረስ የወጡት በአሁኑ ሰዓት በዚህ ዓለም የሌሉ መሆናቸውን በሐዘን መግለፅ ይገባኛል። በዚያ ፈታኝ ጉዟቸው ላይ እግዚአብሔር ወደራሱ ጠራቸው። መስዋዕትነታቸው ግን እንደመታደል ሆኖ በከንቱ አልቀረም። የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት ቀሪዎቹን መልዕክተኞች በታላቅ አክብሮት ተቀብለዋቸዋል። ንጉሠ ነገስቱ ለካቶሊክ እምነት በሚገባ ዝንባሌ እንደነበራቸው ገልፀው፣ አሁን ግን ሊቀላቀሉ እንደማይፈልጉ አጥብቀው ተናግረዋል። ከዚህም በላይ በግርማዊነትዎ መማረካቸውንና በዓለም



ላይ ሃያሉ የክርስቲያን መሪ መሆንዎን ተቀብለዋል። አክብሮታቸውን ለመግለፅም እስከ ካይሮ ድረስ አንድ የመልዕክተኛ ቡድንና በራሱ ሕዝብ መካከል ደረጃው ባይታወቅም አምባሣደር ሊባል የሚችል ሰው ልከው ነበር»

«እንግዲያውስ ሰውዬው አሁን እዚህ ለምን የለም» አሉ ሉዊስ 14ኛ

«ጃንሆይ፣ እኛም ልናመጣቸው ከልባችን ፈልገን ነበር። ነገር ግን ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው፣ አውሮፖዊ ተወላጅ ያልሆነ ሰው፣ ወደ አውሮፖ እንዳይጓጓዝ ቱርኮች ብዙ እንቅፋቶችን ይፈጥራሉ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ አምባሣደሩ የመጡት ብቻቸውን አልነበረም። አጅበቻቸው የመጣውና አሁን እፊትዎ የሚያዩት ሙሴ ፖንሴ ነበር»

አባ ፕላንቴይን ወደ ጆን ባፕቲስት ዞር አሉ። በክፍሉ ውስጥ ቀደም ሲል ሰፍኖ የነበረው ውጥረት እንደገና አገረሸበት። የዚህ ሁሉ ማዕከላዊ አትኩረት እርሱ እንደሆነ ጆን ባፕቲስት ተገነዘበ።

«ሙሴ ፖንሴ፣ በምስራቅ ሜዲቴራኒያን ጣቢያዎች የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ይሠራል። በአሁኑ ጊዜ መኖሪያው ካይሮ ውስጥ ነው። ለግርማዊነትዎ ቀደም ሲል የገለፅኳቸው ነፍሣቸውን ይማረውና አባ ዴ ብሬቬደንት፣ ወደ አቢሲኒያ ጉዟቸውን ያደረጉት ከርሱ ጋር ነበር። ያን ጊዜ ንጉሠ ነገስቱ ታምመው ስለነበር አውሮፖዊ የመድሃኒት አዋቂ እንዲያያቸው ጠይቀው ነበር። በዚህም መሠረት በሙሴ ፖንሴ አማካይነት አቢሲኒያውያን፣ ንጉሥ እያሉ ወደሚጠሯቸው መሪያቸው ዘንድ የመድረስ ዕድል አገኙ። ከዚያም፣ ከዚሁ ከሙሴ ፖንሴ ጋር የአቢሲኒያውያን መልዕክተኞች የመልስ ጉዞ አደረጉ»

ይህን ተናግረው አባ ፕላንቴይን ወደ ኋላ ተራመዱና ጆን ባፕቲስትን ተመለከቱ። ሉዊስ 14ኛም በተራቸው ዐይኖቻቸውን ወደ ሐኪሙ ወረወሩ። የንጉሡ ከፍተኛ ባለስልጣን አጃቢዎችም እንደመሪያቸው አደረጉ። ጊዜው ደረሰ።

ጆን ባፕቲስት፣ ለአመል ያህል ወደፊት ተራምዶ ከወገቡ ጐንበስ ካለ በኋላ ቀጠለ።

«ጃንሆይ፣ የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት ለግርማዊነትዎ እንዲያደርሱት የላኩትን መልዕክት፣ አምባሣደሩ እዚህ ሊገኙ ባለመቻላቸው እኒያ ከፍተኛ ገዥ፣ በዚህ ቤተመንግስት እንዲሰማላቸው የፈለጉትን መልዕክት የማቅረብ ሃላፊነት በኔ ላይ ወድቋል። በዚህም ላይ ማከል የምፈልገው፣ ንጉሠ ነገስቱ፣ ግርማዊነትዎ መልስ እንደሚልኩላቸውም ትልቅ ተስፋ

በቆንሲል ማዕረግ ወደ ሮቤታ ተላከ። ሮቤታ ወደብ በመሆንዋ ከበቂ በላይ የንግድ እንቅስቃሴ ቢታይባትም በምስራቅ ሜዲተራኒያን ከሚገኙት ጣቢያዎች ሁሉ፣ አነስተኛ ክፍያ የሚደረግባት ነች። እርሱ ግን ደመወዙን በቀላሉ እጥፍ ማድረግ እንደሚችል ለራሱ ነገረው። ያሰበውንም ወዲያውኑ ጀመረ። እንደ ደረሰ ምንም ሳይቆይ፣ በእነከን የለሽ ጥሩ ስሙ ሳቢያ፣ ሚስትና ለመሥሪያ ቤቱ የሚሆን ሕንፃ ተሰጠው። ለማንኛውም ዓይነት ዓላማና ተግባር ሁለት ነገሮችን ታደለ።

የሚያጋጥሙ ነገሮችን ስርዓት ሳያጠብቁ ከማከናወን አስቀድሞ፣ በበቂ ሁኔታ ማሰብ ጠቃሚ ነው። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የተከበረ እኩያና የሚመጥን ሰው ስለሆነለት፣ ለሴት ልጁ የሚጠይቀው የጥሎሽ ጉዳይ ላይ ሊጣደፍ ይችላል። ዱ ሮውሌ ደግሞ ፈጥኖ ለመታሰር አይቸኩልም። በአሁኑ ሰዓት የርሱ ትልቁ ፍላጎት አቢሲኒያ ነች። ስለ አቢሲኒያ የሚያውቀው ትንሽ ቢሆንም፣ በተደጋጋሚ ወርቅ፣ የከበሩ ድንጋዮችና ቅመማ ቅመም እንደሷት ተነገሯል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ባልተለመደ ከፍተኛ ጉጉት የፈረንሣይን ኢስት ኢንዲያ ካምፓኒ፣ ወደ አቢሲኒያ ለማስፋፋት እቅድ አውጥቷል። ይህን ያደረገው ዱ ሮውሌ ከርሱ ይልቅ ለሌላ ሰው ለማገልገል ይሄድብኝ ይሆናል ከሚል የተሣሣተ ሀሣብ በመነሣት ነው። ይህ ፈረሰኛ ግን ይህን የሚያደርግ አይደለም። ምክንያቱም እርሱ በበኩሉ የራሱን ሀብት ማግኘቱን እንጂ፣ ትክክለኛ ነገር በመስራት በራሱ ላይ መሰናክል እንዲፈጠርበት ሀሳቡም የለውም። ወዲያውም በውስጡ የተፈጠረውን ጥርጣሬ ሲገነዘብ፣ በርሱነቱ ኮራ። ይሁን እንጂ በራሱ መንገድም እንኳ ቢሆን፣ ይህ አስተዋይ ሰው ህልመኛ ነው። አገኘዋለሁ ብሎ ስለሚያስበው ሀብት የሚታወቅ ነገር የለም። ነገር ግን ልክ የመጀመሪያዎቹ እስፓኒያውያን አሜሪካ ውስጥ እንዳደረጉት ወይም ፈረንሣዊው ኘርኒስ፣ በማላሬኔ ደሴቶች ላይ እንዳደረገው የርሱ የግሉ የሆነ ግዛተ ዘውድ ይመሠርታል። እርሱም፣ መጠነ ሰፊ በሆነ ሀብት ላይ ንጉስ ይሆናል። በዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ደግሞ ማዳሞዜል ዴ ማይሌ ልትመጥነው ስለማትችል ፈራ። ስለዚህም የንግስታትን ልዕልቶች አሰበ። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ፈጣን ውሣኔ ላይ ለመድረስ ምንም አልተቸገረም። መጀመሪያ ጉዞው ይደረግ። ከዚያ በኋላ ጥያቄው የሚቀጥል ከሆነ ጋብቻውን ማድረግ፣ ሲል ደመደመ።

ይሁን እንጂ ይህ እቅዱ፣ አሊስ በውስጡ ቀስቅሳበት የነበረውን ጠንካራ ስሜት ሊያሸንፍ አልቻለም። ከአንድ ሣምንት በኋላ እንዲህ ሲል ለራሱ ተናገረ። እርግጥ ነው፣ ጋብቻው የሚማርከኝ አይደለም። ሆኖም ግን ከዚህች እርብትብት ሕፃን ጋር ለመደሰት ማንኛውንም ነገር እከፍላለሁ።

እንዳለመታደል ሆኖ አሁን እርሱም ያለው በቤተሰቦቹ የአገር ቤት ግንብ ውስጥ አይደለም።የቆንሲሉም ሴት ልጅ፣ እንዳፈቀደው ሊያንከባልላት እንደሚችላት የዝቤሬ ልጅ አይደለችም። አስቀድሞ በሕግ ሊያገባት ይገባል፣ ይህን ደግሞ አይፈልገውም። ቆንሲሉ በተዘዋዋሪ ያቀረበለትን ያልተነገረ ስጦታ እርሱም አድበስብሶ ለማለፍ ስላልፈለገ ከመውጣቱ በፊት ከልጅቷ ጋር ወሲባዊ ስሜትን የሚቀሰቅስና ምንም ዓይነት ቃል ኪዳን የሌለበት የጨዋታ ጊዜ የሚያገኝበትን ዘዴ ፈለገ። ሲከታተላት ቆይቶ፣ ቀስ በቀስ አንድ ዕቅድ ነደፈ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የርሱን ኢምባሲ መክፈት እንዳረጋገጠለት፣ ወጣቷ ወይዘሪት የሆነ ቦታ ላይ አንድ ምስጢራዊ ፍቅር እንዳዳበረች ድ ሮዉሌ ርግጠኛ ስለሆነ የታሰበውን ጋብቻ እንደርሱ ሁሉ፣ በእርስዋም ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ይሆናል። ለዚህ ባለጌ ሰው ይህ መፅናኛው ሆነለት። ለሌላ ሰው ያላትን ፍቅር፣ ተባባሪዬ ነው ብሎ ዱ ሮውሌ የመዘገበው ሙሴ ማቼ፣ ፈጥኖ ስሙን ነገረው። ይህ ለሌላ ሰው ያላት ፍቅር፣ እርሱ እንደተገነዘበው በጣም ጠንካራ ስለሆነ፣ ምናልባት የራሷን ስሜት እንድትከተል ያስገድዳት ይሆናል። እርሱ ደግሞ ልምድ ያለው ሰው በመሆኑ፣ ይህን ጉዳይ በብልሀት ወደራሱ አቅጣጫ መመለስ ይኖርበታል።

ከገበታው ላይ ብድግ ብላ ነፍሷን ስታ በመውደቁ፣ ከእይታ ከተሰወረች ከብዙ ቀናት በኋላ፣ አሊስ ተመልሣ ብቅ አለች። ዱ ሮውሌ፣ በሄደችበት ሁሉ በዓይኑ ይከተላታል። ሙሴ ዴ ማይሌ ምንም እንዳላስተዋለ እየስመሰለ ውስጡ በደስታ ሞላ። ልጁን ግን፣ ንፅህናዋን ባለመጠበቋና እንግዳቸውንም ባለማስተናገዷ መውቀሱን ተያያዘው። ታዲያ አሊስ የአባቷን ጡቆሣ ተቀበለች? ወይስ ደግሞ ተፈጥሮአዊው ውበቷ ፣ ላላ ተደርጐ የተሠራው ፀጉርዋ፣ ተራው ልብስዋና ሆን ብላና ምክንያት ፈጥራ ታምሜአለሁ ከማለቷ በስተቀር፣ የተሟላው ጤንነትዋ፣ የጀግኖችን ስሜት አላነሣሣም ይሆን? አይናፋርነትዋና ፍርሃትዋ እውነተኛውን የዱ ሮውሌን ስሜት አጋግሎ ምንም ዘንድ ለመድረስ እንደገፋፋው፣ ማለትም ይህን ባህርይ በወሲባዊ ግንኙነት ፍላጎት ለመለወጥ አላነሣሣውም?

ከቆንሲሉ ፅህፈት ቤት የኢምባሲ ሹመቱን ገና ተቀብሎ ሲወጣ፣ ፈረሰኛው፣ አሊስን በደረጃው ላይ ስትወርድ አያት። ወደ ሙዚቃው ክፍልም በፍጥነት ተከተላት። እርስዋ ግን በርያኖው ላይ የነበረ አንድ የሙዚቃ ድርሰት ዕሉፍ በፍጥነት አነሣች።

# 10

ጆን ባፕቲስትን ለመመርመር ከምሁራን የተመረጡት ሰዎች፣ ማንግራይ ከገመቱበትና ከአዲሱ ዓመትም ጥቂት ቀደም ብለው ተሰበሰቡ። ቬርሳይለስ ውስጥ የዚህ እጅግ ልዩ የሆነ ታሪክ የሚነገርለት የውጭ አገር እስረኛ ቆይታ መራዘም፣ እየዋለ እያደር አስቸጋሪ መሆኑ ይታወቅ ጀመር። ጉዳዩ እስከመንግስት ምክር ቤት ድረስ ሲቀርብ ፣ንጉሡ ራሣቸው የተፋጠነ ርምጃ እንዲወሰድ አዘዙዋል። ፖንሴ፣ በርግጥም አታላይና አጭበርባሪ ከሆነ በፍጥነት ቢቀጣ ጥሩ ነው። ነገር ግን መልካም ሰው ሆኖ፣ በርግጥም የንጉሡ መልዕክተኛ ከሆነ እንደስድብ ሊቆጠር የሚችለውን ጉዳይ በጣም በአጭሩ ማድረጉ የተሻለ ነው።

ከሕዝብ መካከል የተመረጡ አራት ምሁራን ዳኞች አሉ። ሁለቱ የዩኒቨርሲቲ ሰዎች ሲሆኑ፣ ሁለቱ ደግሞ ከካህናት መካከል ናቸው። አራቱም ሰዎች በጥንታዊ ታሪክ፣ በቋንቋዎች ትምህርትና ጥናት የዕውቀት ዘርፍ የታወቁ ምሁራን ስለሆኑ ትምህርታቸውን ሊፈታተን የሚችል አንድም ሰው የለም።ምንም ይሁን ምን እነርሱ የሚሉት ታምኖ ተቀባይነትን ያገኛል። እነርሱ ብዙም አይናገሩም። ቢናገሩም በተቻለ መጠን ከስተር ባለ ድምፅ ነው። በሌላ መልክ፣ በነርሱ አስተያየትና ትምህርት ውስጥ ባልተካተተ ወይም በተለየ አስተያየትና ትምህርት ላይ መርዛቸውን ይተፋሉ።

እነዚህ ከሕዝብ መካከል የተመረጡ ዳኞች፣ ለፖንሴ ጉዳይ ጠላቶች ናቸው ማለት ጉዳዩን ማጣጣል ይሆናል። እውነተኛው ነጥብ፣ ፖንሴ፣ ንጉሡን ያስቀየማቸው መሆኑንና፣እነርሱ ደግሞ ንጉሡን ለማስደሰት መፈለጋቸው ነው። ከዚህም በላይ፣ ስለዚህ ተንኛ ስለተባለው ሰው ያዳመጡት ፕሮፖጋንዳ፣ አስተሣሰባቸው በርሱ ላይ ተቃራኒ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ይሁን እንጂ በታዋቂነታቸውና በዝነኛነታቸው ምክንያት በቀላሉ ተፅዕኖአቸውን ያሣድራሉ።

በመጀመሪያው ችሎት ላይ ሲቀርብ፣ ጆን ባፕቲስት ንጉቶ ነበር። ማንግራይ፣ ከነጭ ጥጥ የተሠራውን ልብስ እንደ ትንኮሣ ሊቆጠርበት ስለሚችል፣ እንዳይለብስ መክረውት ነበር። በዚህም የተነሣ የተለመደውንና ተቀባይነት ያለውን የሱፍ ልብስ ለብሶ ሄደ። የፊት ለፊቱ ተቃውሞ በሶርቦኔ ውስጥ በሚገኝ አንድ ትልቅ ክፍል ውስጥ ተጀመረ። የክፍሉ ግድግዳ በተቀረፀና በወርቅ በተለበጠ እንጨት ያጌጠ ነው። ተመራጭ ዳኞች የተቀመጡት ከእንጨት



በተሠራ መድረክ ላይ ሲሆን፣ ፕሮፌሰሮች የመምህርነት መለያቸውን፣ ቀሳውስቱም የክህነት ካባቸውን ለብሰዋል። ተጠርጣሪው፣ ከፊት ለፊት ከመድረኩ በታች ተቀምጧል። ጠባቂዎቹ፣ በግራና በቀኝ በኩል ሆነው ይከታተሉታል። ከበስተጀኋላው ባሉት ሁለት ተርታ መቀመጫዎች ላይ፣ አነስተኛ ቁጥር ያለው የችሎት ታዳሚ ሲገኝ፣ ከነዚህ መካከል ዓይኑ እየሸሸው ያለውን ፍሌሀውትን፣ ከሶስት ሌሎች ጄስዊቶች ጋር ታጅበው አባ ኘላንቴይንንና ሌሎች እንግዶችን ጆን ባፕቲስት ተመለከተ። ክረምት በመሆኑ ምክንያት ክፍሉ ቀዝቃዛ ነበርና አድማጮች ሊያስላቸው ይቃጣል።

ሁሉንም ሰው ያስጨነቀው ሥርዓት፣ የፍርድ ቤት ያልሆነውን ሥራ የፍርድ ቤት ማስመሰል ነበር። ሂደቱ፣የአንድ ሰው እውቀት መገመቻ የባለሙያ ሥራ ነበር። ጥያቄው ጆን ባፕቲስት በርግጥ ወንጀል መፈፀሙን ለማረጋገጥ ሳይሆን፣ ጆን ባፕቲስት አከናውኜው ተመልሻለሁ የሚለውን ጉዞ፣ በርግጥ አከናውኖታል ወይ የሚል ነው። እንደዚሁም ደግሞ ግልፅና ያልተደበላለቀ የእውነታ ምርመራው፣ ሌላ ገፅታ ቢኖረውስ የሚለው ነው። ጆን ባፕቲስት ሐሰተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ ይኸው ተመልክቶ በፍርድ እንዲወሰንበት ወደ ማረፊያ ቤት ይተላለፍና እዚያ ሰዎች እውነቱን እንዲናገሩ የሚደረግበት ሌላ ዘዴ አለ።

የምርመራው ሂደት እየተከናወነ እያለ አጠራጣሪ ነገሮች ግልፅ ነበሩ። የምርመራው አጣሪዎች «ተከሣሽ» ስሙን፣ ትውልዱንና ሥራውን «ፈቃደኛ ከሆነ» እንዲገልፅ ጠየቁት። ይሁን እንጂ የምርመራ አጣሪዎች ፕሬዚዳንት፣ ይህን ጥያቄ ባይመልስ አዳጋች እንደሚሆንበት በራሱ አገላለፅ አስረዳው።

«ስሜ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ ይባላል። ወላጆቼን አላውቃቸውም። የተወለድኩት ግሬኖብል ውስጥ ሰኔ 17 ቀን 1672 ዓ.ም ላይ ነበር። ላለፉት ሦስት ዓመቶች ያህል ካይሮ ውስጥ እፅዋት በመሰብሰብ ስራ ላይ በመሠማራት ኖሬአለሁ»

ፕሬዚዳንቱ፣ ከፊት ለፊት ያሉትን ወረቀቶች ፈተሻቸው። የፍርድ ሂደቱ ፀሐፊ፣ በመድረኩ ጠርዝ ላይ በብዕሩ ቧጨረ።

«እንዲህ ከሆነ ወደ አቢሲኒያ ተጉዣለሁ ብለህ እየገለፅክ አይደለም እንዴ?»

«እየገለፅኩ ሣይሆን እያረጋገጥኩ ነው»

«እንዲህ ከመሰለ ጉዞ ተመልሰናል እያሉ በጉራ የሚናገሩ ጥቂት ክርስቲያኖች በዛሬው ዘመን እንዳሉ ታውቃለህ?»

ፖንሴ፣ ገና ከጨቅላነቱ ጀምሮ አስራ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ያሳደጉት በገጠር የሚኖሩት ሴት አያቱ ነበሩ። አዛውንቷ ኑሯቸውን የሚደጉሙት ቅርጫት እየሠሩ ነበር። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት የሴቶች ስዕሎች ሁሉ ከርሱ የተዋሱትን ብርሃን መልሰው ያንፀባርቁበት ነበር። ወንድ እምላክን በማምለክ ፈንታ ሴት ጣኦትን ቢያመልክ ኖሮ፣ ጳጳስ ሊሆን የሚችልበትን ሃይል ያገኝ ነበር። ይህን በተመለከተ ከርሱ ሊሻል የሚችል ማንም እንዳልነበረ ትዝ ሲለው ለራሱ ፈገግ አለ።

የቅዳሴ ስነስርዓቱ ሲካሄድ እንደ አስፈላጊነቱ ጆን ባፕቲስት ይቀመጣል፣ ይቆማል፣ ወይም ይንበረከካል። በያንዳንዱ የእንቅስቃሴ አቅጣጫ ለውጥ፣ በቀዝቃዛው የድንጋይ ወለል ላይ ያረፉት ወንበሮች ይንጓጠጣሉ። በቁርባን ጊዜ፣ በካህኑ እጠገብ ቆሞ የነበረው ዲያቆን እንዲት ትንሽ ቃጭል ሲያንቃጭል ድምፁ በቀዝቃዛው አየር ውስጥ የደወል ያህል ተስተጋባ። ተንበርክኮ የነበረው ጆን ባፕቲስት፣ ከአፉ ውስጥ ጭጋግ የመሰለ እንፋሎት ሲወጣ ይመለከታል። ጭንቅላቱን ትንሽ ቀና ሲያደርግ አንዱ ገጨው። እንዲህ ያሉ ሰዎች ማን መሆናቸውን እንኳ ሳታጣሩ በፊት ወዲያውኑ፣ ለዘለዓለም ሳትለወጡ እንድትኖሩ የሚፈልጉ ዓይነት ሰዎች ናቸው።

ዓይኖቹ አንድ ታላቅ ነገርን ያገኙ ይመስል ብልጥጥ ብለው ሣለ፣ ተንበርክኬአለሁ ሲል አሰበ። አዎን! ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ ይህን ኃላፊነት ከተቀበልኩበት ጊዜ ጀምሮ እንደተንበረከክሁ ነኝ። ወይም ደግሞ ምናልባት አሊስን ካየኋት ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ፣ አንድ ነው። ነፃ ሰው ነበርኩ። በላዬ ላይ ሰተሜነብኝ ማየው፣ አንድም ባለስልጣን ተሸንፌ አላውቅም ነበር። ቆንሲሉም ቢሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ማየው፣ ወደኔ የመጣው እርሱ ነበር እንጂ፣ እኔ ወደርሱ አልሄድኩም። በአንድ ዛፍ ስር አረፍ ብዬ እቤቱታውን በማዳመጥ ውለታ ነበር የሠራሁለት። እንዲያ ላደረግሁለት ሰው አሁን ተንበርክኬ እገኛለሁ።

ቄሱ ምልክት ሲሰጡ፣ ተንበርክኮ የነበረው ሁሉ ብድግ ብሎ ቆመ። ከበስተኋላው ጠመንጃ አንጋች አጃቢዎቹም ብድግ ሲሉ መሣሪያቸው ሲንኳኳ፣ ጆን ባፕቲስት ሰማ። እርሱም እንደሚመቻቸው ሆነላቸው።

ይኸው አሁን ደግሞ ተነስቼ ቆሜአለሁ። ይህንንም ያደረግሁት ስለታዘዝኩ ነው። ቆንሲሉ ተቀመጥኩም፣ ቆምኩም ሁልጊዜም እንደተንበረከክሁ ነኝ። ይህ ደግሞ ሽንፈት ነው። ቆንሲሉ



ራርቶልኝ ሴት ልጄን ይሰጠኛል ብዬ እጠብቃለሁ። ንጉሡም የመሣፍንት ዘር ብለው እንዲመርቁኝ እጠብቃለሁ። እነዚህ ምሁራኖችም አስተያየታቸውን እንዲሰጡ እየጠበቅሁ ነኝ። እነዚህ ደግሞ ሊወነጅሉኝ ነው። ንጉሡም ሲረዱኝ የሚያደርጉት አንዳችም ነገር የለም። ቆንሲሉም ሴት ልጁን ይከለክለኛል። ይህ ሁሉ ሲሆን የምንበረከከው በሚያፈቅረኝ ሕዝብ ፊት ሳይሆን፣ በነዚህ እጅግ መጥፎ ባለሥልጣናት ፊት ነው። ከዚህ ሁሉ የሚከፋው ግን፣ እኔ ይህን አለማመኔ ነው። የመሣፍንት ወገን ተብሎ በአንድ ንጉስ ውዳሴ ማግኘት ሌሎችን ለመጫን ከሆነ፣ ይህን ክብር ነው ብዬ አልቀበለውም። ይህም ሃይማኖት ከሌለው የተሻለ ነው ብዬ አላምንም። ማንም ሰው እምነቱን በራሱ ፍላጎት ሊመራ መቻሉን ባምንም፣ ቤተክርስቲያን በሰዎች አስተሣሰብ ላይ፣ በተለይም በኔ ላይ ሥልጣንዋን እንድሸከም እንድታስገድደኝ ፈፅሞ አልቀበልም። ይህም ሆኖ ግን ይኸው ተንበርክኬ እኖራለሁ።

ካህኑ ቡራኬ ሰጥተው ካሳረጉ በኋላ፣ ምዕመኑ እጆቹን በየኪሱ ውስጥ እየወሸቀ ተጣድፎ ወጣ። ምእመናኑ ሲወጡ ግን በሃሣብ ጭልጥ ብሎ፣ በሁለት ታጣቂዎች ይጠበቅ የነበረውን ወጣት ተመለከቱት።

ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው፣ ቆንሲሉ ፊት ስለተንበረከክሁ ነው። ያለጥርጥር ሁሉም ነገር ከዚሁ የሚመነጭ መሆኑ ግልፅ ነው። ጉድቀቴ የጀመረው ያን ጊዜ ነው። ነፃነቴን አሣልፌ የሰጠሁበትና የካድኩበት ጊዜ በትክክል ያን ጊዜ ነበር። አባት፣የሴት ልጁን ፍላጐት ተቀብሎ፣ አይዞሽ ግፊበት ይላታል ብዬ ሳስብ ነበር። እንዲት ሴት አፈቀርኩ ብዬ ለራሴ እያረጋገጥኩ እያለሁ፣ የርሷን መኖርና ነፃነትዋንም እየካድኩ እንቀሣቀሣለሁ። የአሊስንና የኔን ሕይወት፣ በዚያ ክብር በሌለው አባቷ እጅ ውስጥ ጥዬዋለሁ። ስለዚህም ተዋርጃለሁ። ተንበርክኬአለሁ።

«የለም» አለ አንዱ ታጣቂ ወዲያውኑ

ጆን ባፕቲስት እንደማፈር ብሎ ይህን የመጨረሻ ቃል ጮክ ብሎ መናገሩን ተገነዘበ።

ወደ አቅሉ ከተመለሰ በኋላ «ኑ ጌቶቼ፣ ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ ፊት ሁልጊዜም ዝቅ ማለት አለበት» አላቸው።

ከዚያም ከክብር ተከታዮቹ ጋር እብስ አለ።

ይህ ሃሣቡ የሚያስከፋ ቢመስልም፣ በጆን ባፕቲስት ላይ ግን ከባድ ተፅዕኖ አሣደረበት። እዚህ ውስጥ ከተዘራች ህዋስ የሚበቅልና መላውን መፃኢ ተግባሩቱን ሁሉ የሚቀይርበት አዲስ መንገድ፣ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ራሱን ያሣውቃል።

ያሉበት የመናፈሻ ስፍራ አለ። ከሆነ አጠር ያለ አጥር በስተጀርባ ይጮሁ የነበሩትን የጥበቃ ተረኞችን ውሾች፣ በጥንቃቄ አለፏቸው። ወዲያውኑ ይህን አጥር አልፈው ወደ ቻርኒ በመውጣት ባዶ፣ ነፃና ገላጣ በሆነው አካባቢ ውስጥ ገቡ። ጉዟቸውን በረባዳው የእግር መንገድ ላይ በማድረግ በደን ውስጥ በማቋረጥ ግራና ቀኟን የደረቁ ቅጠሎች የተንዘራዘሩባትን ትንሽ ምንጭ ዘልለው አብስ አሉ።

እስከአሁን ድረስ ጨረቃዋ ስላልወጣች ከሰማይ የሚመጣ ምንም ብርሃን አልነበረም። በአንድ ሰፊ መንገድ ውስጥ ገብተው ወደ አንድ አጥር ዘንድ ሲቃረቡ፣ በእንቅልፍ ላይ ያለች ላም አልፎ አልፎ ስትጮህ ይሰማሉ። የቻርኔን መንደር ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ወደ ቀኝ እጥፍ አሉ። እርጥበት አዘል ከሆነው አየርና ከሚንኮሻኮሸው የቅጠላቅጠል ድምፅ በመነሣት በደን ውስጥ እየተጓዙ መሆናቸውን፣ ጆን ባፕቲስት አወቀ። አንድ መስክ ላይ ፈረስ ሲያናፋ ተሰማቸው። ሞርቲየር ምልክት ሲያሰማ በጭለማው ውስጥ ያለ ሌላ ሰው በፉጨት መልስ ሰጠው።

«አንተ ወስላታ፣ አንተነህ እንዴ?»

«ሌላ ማን ይሆናል የኔ ወሮበላ?»

የሰውዬው፣ ስልል ያለችና ቀጭን፣የምትንቀጠቀጥ፣ምናልባትም ሽማግሌ ሣይሆን እንደማይቀር የምታጋልጠው ድምፁ፣ በቅርብ ካለው ጨለማ ውስጥ ትሰማለች።

«አውሬውንስ አምጥተኸዋል?»

«አውሬስ አንተው ነህ፣ ጆሮ የለህም እንዴ? እጅህን ወደዚህ አቅርብ። ይህ የምትዳስሰው ቆቅ ይመስልሃል እንዴ?»

«አንተ ቀልደኛ ሽማግሌ። ልጓሙን አቀብለኝ። ዶክተር፣ ይኸውልህ። ፈረሱ ተጭኖልሃል። መሄድ ትችላለህ።»

ጆን ባፕቲስት፣ የቆዳ ርካቡን በዳሰሳ ካስተካከለው በኋላ ኮርቻው ላይ ዘልሎ ወጣ። ሞርቲየር፣ ዱብ አግኝቶ ፈረሱ ላይ ሊወጣ እንዲችል በማለት መንገዱን ይዞ ወደፊት ሄድ አለ። ኮንትሮባንዲስቱ፣ ምንም ዓይነት ገንዘብ ላለመቀበል አሻፈረኝ ቢልም፣ ጆን ባፕቲስት የሙጢኝ ሳይለው፣ ነገር ግን ሰውዬው ሳያስተውል አንድ ገንዘብ ያለበት ቦርሣ በኮቱ ውስጥ በዘግታ ጣል አደረገለት።



ድምፅ ሳይለዋወጡ ተጨባበጡ። ከዚያም ከልብ በመነጨ ስሜት ተመሰጋገኑ። ፖንሴ፣ የፈረሱን ጉን በእርካቡ ኮረኮረውና መንገዱ ውስጥ ገባ። በመጀመሪያው መስቀልኛ መንገድ ላይ ሲደርስ፣ ከቀደሞው ውሣኔው ፈፅሞ ላለማፈንገጥ ሲል ወደ ደቡብ ታጠፈ። ገና ጉዞውን እንደጀመረ እጅግ ጨለማ ስለነበረ ግልቢያውን ቀዝቀዝ ሊያደርግ ዳድቶት ነበር። በኋላ ግን ብርማዋ ጨረቃ በሰማይ ላይ ብቅ ስትል፣ ከፊት ለፊቱ ያለውን የመሬት አቀማመጥ ልታሣየው በቂ ሃይል ነበራት። ፈረሱ፣ረጋ ብሎ ደስ የሚያሰኝ ግልቢያ ያደርጋል። ጆን ባፕቲስት፣ ከዚህ በፊት እንዲህ ለእስር የተቃረበበት ጊዜ ፈፅሞ አልነበረውም። አሁን ግን የንጋቱ ሁሉ ሃያል የሆኑትን ንጉሥ አሻፈረኝ ስላለ ይፈልጉታል፣ ያሣድዱታል። በአንፃሩ እርሱ ደግሞ በዛፍ ቅርንጫፍ ቢገረፍና ዓይኖቹም በእንባ ጅረት ቢሞሉም፣ በዚህ ቀዝቃዛ ምሽት የተሰማውን ነፃነትና በራስ መተማመን ስሜት መቼውንም ቢሆን ተሰምቶት አያውቅም ነበር።

# 5

# የቁጥቋጦው ሠደድ

# 1

አሊስን ከምንም ነገር በላይ የሚያሳስባት፣ የርስዋ የራስዋ ውስጣዊ ንፅህና፣ የስሜቶችዋ መልካም ስምምነትና ሙሉ በሙሉና በታማኝነት ለማፍቀር የመቻልዋ ጉዳይ ነበር። እነዚህን ግላዊ ስጦታዎችዋን መጠበቅ በራስዋ ፈቃድ ላይ ብቻ የተወሰኑ ናቸው። አንዳች አጋጣሚ በሰውነቷ ላይ ቢደርስ እንደማይበላሽባት ስታስብ በውስጧ ጤነኛ ትምክህት ተሰማት። በልቧም ውስጥ እውነተኛ ልጃገረድነትዋ ሃያልና ጠንካራ ሆኖ ቆየ።

ሕብረተሰብ፣ የራሱን ወጣት ትውልድ ነፃነት በመፍራት፣የሚያከብረውን ቁሣዊ ድንግልና ጠብቃ በማቆየት ራስዋን ባሪያ የምታደርግበት አስፈላጊነት የለም። በእንፃሩ፣ እስከዛሬ ድረስ ጠብቃው ያቆየችውን ቅድስናዋን በረገኟቸዋቹ የመስንከያ ቀሚሶችና ቀፈትን መሰብሰቢያ ባለብረት ቀበቶ ሙታንታዎችን መልበስ፣ በእንግዳ ሰዎች ፊት አይኖችዋን መስበርና ሲመሽ እንደደነገጠች የምትታደን እንሰሳ እንድትሮጥ የሚያደርጋት ያንን አስቂኝ ነገር ለመከላከል ነው፣ ስትል በስጨት ብላ አሰበች።

አሁን ግን እግርጠኛነትን፣ ብርታትንና ክህሎትን፣ ጊዛ ውስጥ ተምራለች። ስለዚህም ይህንን የሚያስራትን ገመድ ወዲያ ጥላ፣ራስዋን ነፃ ማድረግ ይኖርባታል። በዚህ ረገድ፣ ጆን ባፕቲስት ያለ አንዳች ማወላወል መንገዱን እንዲቀድድላት ትመርጥ ነበር። ይሁንና አሁን የሚቻል አይደለም። ከዚህ ይልቅ በተቃራኒው፣ እርሱን ሳይዘገይ ነፃ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ለማከናወን ያለ የሌለ ሃይሏንና ጉልበትዋን ሁሉ ለማዋል እንድትችል፣ ያገኘችውን ማንኛ ውንም ወንድ ልትጠቀም ፈለገች። ፈረሰኛው ሮውሌ፣ እንደተማረከችለትና የግሉም ሊያደርጋት እንደሚችል አምኗል። እርሷ እራስዋ የቋመጠችለትን ጉዳይም፣ ለመፈፀም እያዘነ ፈቀደ። ምንም እንኳ የረዥም ጊዜ ልምድ ቢኖረውም ይህ ቅንዝረኛ ፈራ። ይህ የሆነው ምናልባት አብሯት ባሳለፈው ምሽት፣ የአሊስ ቅዝቃዝ ማለትና የውሣኔዋ ሁኔታ የፈጠረበት ይሆናል። ለማንኛውም የዚህን ግጥሚያ አስፈሪ ውጤት ለማሳካት ፈረሠኛው ነፃ ሆኖ ሲያስብ ቆየ።

በመጀመሪያ ደረጃ ተፈጥሮአዊ ሁለንተናዋን ከወሲባዊ መስህብ፣ ከትልቅነት፣ ከጋለ ስሜትና ከነፃነት ጋር አደበላልቃ ማከናወን በቻለችው በዚህች ውብና ሃፍረተቢስ ልጃገረድ

# 7

የካይሮ ፓሻ ከሚኖርበት ምሽግ በስተጀርባ፣ ከቤተመንግስቱ ረዥም ግንብ በታች፣አንድ ጭር ያለ መንገድ አለ:: ወደዚህ መንገድ ምንም አይነት ነገር ማለትም በርም ይሁን መስኮት እንዲከፈት አይፈቀድም:: በዚህም የተነሣ የቤተመንግስቱ ጀርባ በአንድ በኩል እና እንዲሁም ግድግዳ ብቻ የሆኑት የከተማው ቤቶች በሌላው ወገን ሆነው ሲያዩት፣ መንገዱ በሁለት በማይቋረጡ ግድግዳዎች መሃል እንደ አባብ እየተጥመለመለ ያለ የመስኖ ቦይ ወይም ተራ ቦይ ይመስላል:: ጠባቂዎች ቀንና ሌሊት ይቃኙታል:: ይህን የምስጢር መንገድ አንድም ሰው አይደፍረውም:: ይህም ሆኖ ፍፁም ከሌላው በጣም በተነጠለው የጠባቡ መንገድ መሃል አካባቢ፣ አንድ በብረት ቁልፎች የተቆለፈ፣ ነገር ግን በፊት ለፊቱ በኩል የመክፈቻው ቀዳዳ የሌለበት መግቢያ አለ:: የዚህን ታላቅና ሰፊ ግንብ በሸነቆረው በዚህ መግቢያ በኩል፣ ማንም ሰው ወደ ቤተመንግስቱ አደባባይ መዝለቅ ይችላል:: በዘመናት ውስጥ የተለዋወጡት ፓሻዎች በዚህ መግቢያ ላይ የያንዳንዳቸውን ባህርይ ሊገልፅ ለሚችል ለተለያየ አገልግሎት ተጠቅመውታል:: ፖንሴ፣ ወደ አቢሲኒያ ለመጓዝ ከከተማው እንደለቀቀ፣ ከፈረስ ላይ ወድቆ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሞተው እንደ ሁሣይን ያሉት፣ ይህን መሹለኪያ የከፈቱት ማንነታቸው ሣይታወቅ ወደ ከተማው ዘልቀው ለመግባትና በጉዟቸውም ላይ ሰዎች ምን እንደሚሉ ለመስማት፣ በሃሩን አልረሺድ ስልት ሴረኞችንና ተንኮለኞችን ለማሣደድ ይጠቀምበት ነበር:: ሌሎቹ ደግሞ ባልተቋረጠ ቅኝት ውስጥ ተቆልፎ እንዲቆይ አድርገውታል:: እንዲህ የሚያደርጉት ለነፍሣቸው በጣም የሚፈሩት ናቸው:: እንግዲህ የሰዎችን ውስጣዊ ስሜትና ፍላጐት፣ ሁልጊዜም የሚያረካቸውን ነገር የሚያውቀው አሳህ ሲሆን፣ እነዚህ ለሕይወታቸው የሚሰጉት ፓሻዎች፣ ብዙ ጊዜ የሚሞቱት በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች እጅ ነው:: አንዳንዶቹ ደግሞ ይህን የጓሮ በር በአፈሌል የማይቀበሏቸውን ሰዎች የሚያስገቡበት አደረጉት:: የመሃመት ቤይም የዚህን በር አጠቃቀም ይህን ይመስላል:: ዙሪያውን በፀሎት፣ በተስፋ፣ በግብፅ ውስጥ በሚገኙ ወግ አጥባቂ ሙፍቲዎችና ኢማሞች የማፅናኛ ቃላት ቢታጀብም እርሱም ቢሆን አልፎ አልፎ ሃማበ ግትርነቱን ለሰለስ ያደርግና፣ ጠንቃቃ የውጭ ጉብኚዎችን በዚህ በር በኩል እንዲገቡ ይፈቅድላቸው ነበር:: እነዚህ ጠያቂዎች እንዲገቡ የሚያደርጉት በመሹለኪያው በኩል ነው::



መሀመት ቤይ፣ በእስልምና ሕግ አራት ሚስቶች አሉት:: ከነርሱም አሥራ ሁለት ልጆችን አግኝቷል:: እነዚህ የተቆጠሩት ልጆች በሕይወት ያሉት ብቻ ናቸው:: እንዳለመታደል ሆኖ ታዲያ መሃመት ቤይ ሊገታ የማይችል የውጭ አገር ሴቶችን የማደን ስሜት አለው:: ይህን አይነት ፍላጐት ያደረበት፣ አውሮፖ ውስጥ በዘመቻ ላይ ሣለ ነበር:: እነዚያ የተባረኩና ከረዥም ዘመናት በፊት የነበሩ ጊዜያት ቀላል ነበሩ:: በነዚያ ጊዜያት አረማውያን ቆነጃጅትን በምርኮ ይቀበላቸዋል:: ይህን ድርጊት አይሆንም ብሎ የሚቃወምና የሚያጠቃም አልነበረም:: ሁሉም ዓይነት ቁመናና ዕድሜ ያላቸውን ፈረንሣውያን ሴቶች ንብረቱ አድርጓቸው ነበር:: እውነቱ ይነገር ከተባለ፣ ለርሱ ሁሉም ምንም ልዩነት የላቸውም:: መሃመት ቤይ ደስ ይለው የነበረው፣ የሌላ እምነት ተከታዮች የሆኑ ካቶሊኮች፣ አይሁዶች፣ ኦርቶዶክሶች ወይም እምነት የለሾችም ቢሆኑ እግሮቻቸውን አንፈራጥጠው ሲቀመጡ የሚሰማው ስሜት ነው:: ይህን ሲያከናውን የራሱን እምነት በመተው አይደለም:: በእምነቱ በኩል አይታማም:: የራሱን እውነተኛ አማኒያን ፍሬዎች፣ ቀደም ሲል ሌሎች አርሰውና አለስለሰው ያዘጋጁትን ትልም በመንጠቅ በዚያ ላይ መትከል ለነብዩ ትሁት አገልጋይ የሆነ ያህል ይሰማዋል:: ሙፍቲዎችም፣ ፓሻው የሃይማኖት መልዕክተኛ ያህል የሚያከናውነውን የጋለ ፍቅር ስለተቀበሉት ሌላውን ተግባሩን የተመለከቱት በሌላ መልክ ነው:: ይሁን እንጂ በዚህ የቱርካውያን ግዛተ ዘውድ አካበቢ ያለውን የሞራል ትክክለኛነት፣ ተገቢነትና በተለያዩ እምነቶች መካከል ያለው ሚዛናዊ የመንፈስ እርካታ ስላለ፣ በተቻለ መጠን የፓሻውን የተለያየ ስሜትና ዝንባሌ ለማስደሰት ይሞክራል:: ትንሿ የስርቆሽ በር የምታገለግለውም ለዚሁ ነው::

በውትድርና ዘመኑ ከቦታ ቦታ ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች፣በአካሉ ላይ ከባድ ጉዳት ጥለውበት አልፈዋል:: በዚህም የተነሣ ካለፉት ወራት ጀምሮ በሚሰማው ስቃይ ምክንያት፣ሌላው ቀርቶ መጥፎ ወንጀል የፈፀመ ሰው እንኳ ቢቀርብለት ለመቅጣት ብርታቱና ፍላጐቱ አልነበረውም:: እንደዚሁም ሁሉ የፈለገውን ያህል ቆንጆ፣ ወጣትና በሃይማኖቷም የተጠላች ሆና ብትቀርብለት ብርታቱና ፍላጐቱ አልነበረውም:: ባለፉት ሦስት ወራት በዚህ የጓሮ በር ተጠርተው የሚመጡት ሐኪሞች ብቻ ነበሩ:: ከነርሱም መካከል ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ዡረሚ ነበር::

ዡረሚም ከሣምንቱ በተወሰኑ ሰስት ቀናት ውስጥ እኩለ ሌሊት ላይ ይመጣል:: የክላ ዘበኞችም ይህን ስለሚያውቁ «ሄሌቦሬ» የሚለውን የይለፍ ቃል ሲሰሙ ያስገቡታል:: የዚያን ዕለት ምሽትም እንደተለመደው በትልቅ ኩት ተጀቡኖ፣ ሰፊ ባርኔጣ አድርጐ መጣ:: የይለፍ

«እንግዲያው እንዳትዘገይ» አለው ጋሻው፣ ትዕግስት እንዳጣ በሚያመለክት ሁኔታ። «በነገራችን ላይ ዠረሚ ማይነርህ እንደማይቀር ባውቅም፣ እኔም በደንቡ መሠረት ልነግርህ ይገባኛል። ይህን ሁሉ ነገር በተመለከተ አንድም ቃል ትንፍሽ አትልም። በተለይም ለፈረንሳዮች»

«ጌታዬ፣ እኔም እርስዎ ተመሣሣዩን ውለታ እንዲያደርጉልኝ መጠየቅ እወዳለሁ። በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ የኔን መመለስ የሚያውቅ አንድም ሰው የለም። በተለይም ቆንሲሉ አያውቁም። እኔም ብሆን መመለሴ እንዲታወቅ አልሻም። በርግጥ ሸሪኬን የምጐበኘው ማታ ማታ ሲሆን፣ቀን ቀን፣በጥንቱ የአረቦች መኖሪያ ውስጥ በሚገኝ ፔንሲዮን ለጊዜው እየኖርኩ ነው»

«እውነትህን ነው? በጣም ይገርማል» አለ ጋሻው «ንጉሥህን ልታያቸው እንደሄድክና በተልዕኮህም እምነት የተጣለብህ ነበር የመሰለኝ»

«አይ ጌታዬ፣ ታሪኩ ክፉና የሚያም ነው።» ሲል የራሱን መጥፎ ዕድል ሌሎች እንዲሸከሙለት በማይፈልግ ሰው የአነጋገር ቅላፄ «አናም ረዥምም፣ እጅግ ብዙ አስገራሚ ውጣ ውረዶች የነበሩበትና በአጭሩ ሊያደክምዎ የሚችል ታሪክ ነው»

«እስቲ ታሪክህን ንገረኝ» አለው ጋሻው። በአፈ ታሪክ እንደሚታወቀው እንደ ሱልጣን ሻህርያር፣ ልብ አንጠልጣል እንደሆነ ወግ የሚያስደስተው ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ ሁሉ

«ደግ እንግዲያው» አለ ጆን ባፕቲስት «ወደ አቢሲኒያ ሄድኩ»

የጉዞውን ትረካ በረዥሙ ገለፀለት። ከንጉሠ ነገስቱ ጋር መገናኘቱን፣ ከከንፈሮቹ እንደ ውብ ምንጭ ውሃ እየፈሰሱ በሚወጡ ቃላት ሲናገር፣ ጋሻው ዐይኖቹን በከፊል ጨፈን በማድረግ ትረካውን በመስማቱ መደሰቱን የሚያመላክት ምልክት አሣየ። ደስታውን ይበልጥ ለማጣፈጥ ስለፈለገ ጥሩ መዓዛ ያለው ተክል ሻይና ኬክ እንዲቀርብ አዘዘ።

ጆን ባፕቲስት በትረካው ውስጥ ንጉሡ አንድም የውጭ አገር ቄስ እንደማይፈልግ፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም በቋሚነት ከግብፅ ፓትርያርኳን እንድታገኝ ጋሻው መብት መስጠታቸውንና እንደሚያከብሯቸው ዘረዘረለት።

«በተራሮቻቸው ላይ በሰላም መኖር ይፈልጋሉ» በማለት ፖንሴ አጠቃለለ።



«በአሳህ፣ ትክክል ነው? ሳስበው ምክንያታዊነታቸው ዝቅ ያለ ይመስለኝ ነበር። አሁን አንተ የምትነግረኝ በጣም ጥሩ ዜና ነው። ነገር ግን፣ ይህ ሁሉ፣ አንተ አሁን ለምን መደበቅ እንዳለብህ የሚያስረዳ አይደለም።» ሲል መሃመት ቤይ ገለፀ።

«ወደዚሁ እያመራሁ ነው ጌታዬ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ወደ ቬርሣይለስ ተጓዝኩ . . . »

ጆን ባፕቲስት ከዚህ በኋላ ቬርሣይለስ ስላሉት ስለፀሐዩ ንጉስ ቤተመንግስት ረዥም ገለፃውን ቀጠለ። ጋሻውም በደስታ ያዳምጠው ጀመር። ጋሻው፣ አውሮፖ ውስጥ በውትድርና ላይ በነበረበት ዘመን ወደ አንዱ የአውሮፖ ዋና ከተማ የመግባት ተስፋ ብዙ ጊዜ ነበረው። የሚያሣዝነው ግን ብዙውን ጊዜውን በሜዳ መካከል በሚከተም ቦታ ላይ ነበር ያሣለፈው። በሌላ በኩል አንድ ከተማን የመያዝ ዕድል የነበረው ጊዜም ቢሆን ከተማውን የሚያገኘው ከወደመ በኋላ ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ ቬርሣይለስ ስለሚገኙ ሴቶች፣ ስለፀጉር አሠራር ዘይቤአቸው፣ ስለሽቷቸው በሰጠው ገለፃ ላይ ሆን ብሎ በተንኮል ቀስ እያለ ተናገረ። ምስኪኑ ሽማግሌ ወታደር በደስታ አቅሉን ሣተ።

ከዚህ በኋላ ጆን ባፕቲስት ከንጉሱ ዘንድ ያጋጠመውን የሽንገላ ግንኙነት ገለፀ። በዚህ ትረካው ውስጥ አጣርቶ የሚያዳምጥ ጆሮ እንደሌለ፣ የፈረንሣዩ ንጉሥ ደስ ብሏቸው የሚቀበሉት በምስራቅ ሜድቴራኒያን ስላለው ጉዳይ ብቻ ነው ሲል አስረዳ።

በመጨረሻም የፈረንሣዩ ንጉስ፣ ታላቅ ንጉሥ መሆናቸውን ተስማሙ። ይሁን እንጂ፣ ሉዊስ፣ ሙስሊም ባለመሆናቸው መሃመት ቤይ አዘነ። ሆኖም ካለው የጋለ ስሜት በመነሣት፣ ንጉሡ ቢሰልሙ ጥሩ ሙስሊም ሊሆኑ እንደሚችሉ ተናገረ።

«ይህ ሁሉ ነገርህ፣ለምን መደበቅ እንዳለብህ የሚነግረኝ ነገር የለም» ሲል ጋሻው ጉተጐተው።

ምሽቱ እየተገባደደ ነው። አሽከሮች ሁለት ጊዜ በምድጃው ላይ አዳዲስ ጊንዲላ ጨምረዋል። ጋሻው፣ የውሃ ፒፖው እንዲቀጣጠልለትና ከጆን ባፕቲስት ጋር እንዲጋሩው ትዕዛዝ ሰጥቷል። በዚህ ሞቅ ባለ ጭውውታቸው በመሃከላቸው ያለውን የደረጃ ልዩነትም አላገናዘቡትም።

«ወይኔ» አለ ጆን ባፕቲስት «ታላቁ ንጉሣችን፣ ያው ንጉሥ ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ሲነፃፀሩ በጣም ደካማ ንጉሥ ናቸው። በሰማይ ያለው ጌታችን ግን ሁሉንም ነገር ያያል . . . »

«ሃሣባቸው እንዲህ ነው። አቢሲኒያ ሃብታም ነች። ወርቅ፣ አልማዝና እንደልብ የሚገኙ የእንጨት ዓይነቶች ሞልተውባታል። ምንም እንኳ አቢሲኒያ የክርስቲያን አገር ብትሆንም፣ በአንዳንድ የሃይማኖቱ ሕግጋት ላይ የተለየ መስመር አላት። በዚህም የተነሣ ለሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን አክብሮቷን አትገልፅም። እንደዚሁም ደግሞ አቢሲኒያ፣ ከቱርኮች አልፋ ማለትም ከርስዎም አልፋ በሩቅ ቦታ ላይ ነው የምትገኘው»

«እና?»

«እናማ ስለዚህ በቁጥጥር ስር መደረግ ይኖርበታል»

«ይኸው ብቻ ነው»

«ይበቃል ካሉ ይኸው ነው። ይህ ደግሞ የተወሰነ ጉዳይ ነው። ነገር ግን እንዴት ዕቅዱ ይሣካል? አቢሲኒያን እምነቷን በማስለወጥ ነው? ይህ ደግሞ ብቻውን በቂ አይደለም። ምናልባትም የተገላቢጦሽ ቢፈፀም የተሻለ ይሆናል። ይኸውም አስቀድሞ በሃይል ማሸነፍና መቆጣጠር። ከዚያ በኋላ ሃይማኖቷን ማስለወጥ። የተመረጠው ዕቅድ ይኸው ነበር»

«ፈረንሣውያን አቢሲኒያን ለመግዛት ይፈልጋሉ ብለህ ነው ሃሣብህን የምትነግረኝ?»

«ሃሣቤን አይደለም የምነግርዎ ጌታዬ፣ እውነቱን ነው የምገልፅልዎ። እኔ በየዋህነት አስቤው ስለኢትዮጵያ ሰላማዊ ንጉሥ የሰጠሁትን ገለፃ፣ ሴረኞቹ በሚገባ የታጠቀ፣ ወርቅና የገፀ በረከት ዕቃዎች ይዞ የተንቀሣቀሰ ሠራዊት፣ ይህችን ኋላ ቀር የሆነች ሀገር ለመቆጣጠርና ለመያዝ በቂ ነው የሚል ሃሣብና እቅድ እንዲያራምዱ ነው የመራቸው። ከአንድ ምዕተ አመት በፊት፣ ጀስዊቶች፣ ንጉሡን ብቻ ለመለወጥ በመቻላቸው፣ አገሪቱን በሞላ ለመቆጣጠር ምንም አልቀራቸውም ነበር። ይሁንና እነርሱ ድላቸውን በጦርነት ለማረጋገጥ መሣሪያ አልነበራቸውም። አሁን ግን አስቀድሞ መሣሪያው ይሰለፋል።»

በመደገፊያው ዙሪያ ባሉ ትራሶች ተከበቦ የተቀመጠው ፓሻ፣ ጆን ባፕቲስትን በጭንቀት ተመለከተው።

«አሁን የምትነግረኝ፣ ይኸ አሁን በመጓዝ ላይ ያለው ኤምባሲ . . . »

«. . . የተወሰኑ ሰዎች አቢሲኒያን እንቆጣጠራለን ብለው ተስፋ ያደረጉበት መገልገያቸው ነው»

«እነዚህ እኮ ሃያ እንኳ አይሞሉም! ይህ ሊሆን የማይችል ቀልድ ነው!»



«ጌታዬ፣ እኔ ወደዚያች አገር ተጉዣለሁ። አገሪቱ፣ በተቀናቃኝ ሃይሎች ፍላጐት የተዳከመች ነች። ገንዘብና ጠመንጃ ያላቸው ሃያ ሰዎች ሠራዊት ሊመሰርቱ ይችላሉ። አለመረጋጋት ሊፈጥሩ ይችላሉ። በዙፋኑም ላይ አሻንጉሊት ንጉስ ሊያነግሱበት ይችላሉ። ወይም ልክ ስፓኒያውያን፣ አሜሪካ ውስጥ ባሉ ኢንካዎች ላይ ባለፈው ክፍለ ዘመን እንዳደረጉት ከራሳቸውም ሰዎች አንዱን ሊያነግሱት ይችላሉ።

«እህህህ!» አለ ፓሻው የመሞላቀቅ ፈገግታ ፈገግ እያለ «ይህ ነዋ ሲከበር የነበረው ሴራችሁ?»

«እኔን ራሴን ፍርሃትና ስጋት ውስጥ የከተተኝም ይኸው ነበር። ምክንያቱም እኔ የዚህ ሴራ ተካፋይ ለመሆን አሻፈረኝ ብያቸዋለሁ። ፈረንሣይንም ለመልቀቅ ተገደድሁ። በዚሁ ሳቢያ በተመሣሣይ ምክንያት ስለፈራሁ እዚህ መኖሬን ሸሽጌ እገኛለሁ»

«ወዳጄ ሆይ፣ እውነቱን ልንገርህና አላምንህም። ይህን ሁሉ ያልከኝ እዚያ በነበርክበት ጊዜ ምናልባት አሳሳቢና አስቸጋሪ አለመግባባቶች አጋጥሞህ ይሆናል። ከዚህም ሌላ፣ አንተ በነበርክበት ቦታ ላይ፣ አንዱ ይህን የማይጨበጥ ዕቅድ አንተ እየሰማኸው ተንፍሶ ይሆናል። ይህ ማለት ታዲያ፣እኔ ራሴው ሰላማዊ የይለፍ የሰጠሁት ቅፍለት፣ መሪውን የአቢሲኒያ ንጉሠ ነገስት ለማድረግ ያቀደ ነው ማለትህ ከእውነታው ፍፁም የተለየና የማይታመን ነው»

«ጌታዬ፣ የእርስዎ ማህተም ለነዚህ ሰዎች ፍፁም አስፈላጊያቸው ነበር። የእንቅስቃሴያቸውን መልክ በሚያሣምንና ግልፅ በሆነ መንገድ ካላረጋገጡ እንዴት ሊያገኙ ይችላሉ። እቅዳቸውንም በአንድ ጊዜ ይፋ ማውጣት ጅልነት ነው የሚሆንባቸው። ለምሣሌ የማይንስ ሰዎችን ብቻ ያቀፈ ጓድ ስለሚባለውስ ምንም ነገር አልሰሙም?»

«አዎን ሰምቻለሁ እንጂ። የምሁራን ስብስብ የሆነ አንድ ቡድን ወደ ስዊዝ በማቅናት ከዚያ ወደ አረቢያ ይሄዳል የሚባል ሰምቻለሁ።»

«እና ከዚያም ወደ አቢሲኒያ ይሄዳል። ያጀባቸው ሰው የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት እንደወኪላቸው አድርገው ከኔ ጋር የላኩት ሰው ነው»

«ያ ውሻ ኩርዳዊ»

«አርመናዊ ነው»

«ያው፣ ያው ነው» አለ ፓሻው። «እርሱ አብሯቸው ሄደ? ይህ አልተነገረኝም ነበር»

«ያልተነገረዎ ሆን ተብሎ ነው። እንግዲህ አሁን ይታይዎ ከሆነ፣ ሰዎቹ ሃያ ያህል ሳይሆኑ ወደ ሠላሳው የሚጠጉ ናቸው። ከነርሱ መካከል ጥቂቶቹ ወርቅና መሣሪያ የያዙ ናቸው። ሌሎቹ የንጉሡን መልዕክተኛና የተከማቸውን የምዕራባውያን ዕውቀት ይዘው ይገባሉ»

ፓሻው፣ ሃሣቡን ሊቆርጥ ያልቻለበትና ግራ የተጋባበት ሁኔታ ላይ ስለሆነ በጣም ተጨነቀ። ጆን ባፕቲስት፣ ርህራሄ ተሰምቶት ሊረዳውና ከውሣኔ ላይ እንዲደርስ ለማድረግ አንድ የመጨረሻ መረጃ ሊሰጠው ወሰነ።

«ሌላም አለ»

«ተጨማሪ?»

ጆን ባፕቲስት ፓሻውን በቀጥታ አይኖቹ ውስጥ አየው።

«አዎን ጌታዬ፣ ከዚህ ቅፍለት በፊት አንድ የካፑቺኖች ቡድን ለምን ቀደም ብሎ እንደሄደስ ራስዎን ጠይቀው ያውቃሉ? ይህ የተደረገው ሲናር ውስጥ ሊጠብቋቸው አቅደው ነው። በዚህም ላይ በኮፕቲኩ ፓትርያርክ የተሰጣቸውን የቅብዓ ሜሮን ዕዋ ለምን ይዘው ሄዱ?»

«ቅብዓ ሜሮን፣ ቅብዓ ሜሮን ደግሞ ምንድ ነው?» አለ ፓሻው በሃይለ ቃል።

«በኮፕቲክ ሃይማኖት፣ ሥልጣንና ሃይል ከአንዱ ንጉሥ ወደ ሚቀጥለው ንጉሠ ነገስት እንዲተላለፍ የሚያደርግ ቅዱስ ዘይት ነው»

«ይህን ያደረጉት ፓትርያርኩ ናቸው?»

«አሁን እተየነጋገርን ባለንበት ጊዜ ካፑቺኖች በጉዞ ላይ ናቸው»

«ለኔ ሣይነግሩኝ? በአሊ ጐራዴ!»

ከፖንሴ ጋር ለሊቱን ለረዥም ሰዓታት ስላወሩ፣ ፓሻው ደከመው። ይሁንና ከንጋት በፊት ይህን ሳይታሰብ የተነገረውን ታሪክ አምኖ ተቀበለ። ከመከዳው ተነስቶ በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ተራመደ። የዕለቱ የመጀመሪያዎቹ የፀሐይ ብርሃን ጨረሮች በሰማያዊው የመስኮት መስተዋት አልፈው በግድግዳው የግርጌ ጠርዝ ላይ የወለሉን ምንጣፍ በሰማያዊ ብርሃናቸው ሞሉት። ድንገት በጆን ባፕቲስት ፊት እንደመፍዘዝ ብሎ ቆመና አመሰገነው። ቀጥሎም፣ በሚቀጥለው ዕለት ማታ መድሃኒቱን ይዞ እንደሚመጣ ቃል ካስገባው በኋላ የሚያብረቀርቅ ንፁህ ውሃ ወዳለው ገንዳ ሄደ ። ሃኪሙ፣ በጀርባው የስርቆሽ በር እንደወጣ፣ መሃመት ቤይ ዘበኛውን ጠርቶ የኮፕቲክ ፖትርያርኩን ከመኝታቸው ላይ ቀስቅሶ፣ በዚያውም ኢማሞችንም ጭምር ከየቤታቸው ጠርቶ እንዲያመጣቸው አዘዘው።



# 8

በሚቀጥለው ቀን ማታ ጆን ባፕቲስት ተመልሶ በተለመደው የስርቆሽ በር ገባ። አንዲት አነስተኛ ቦርሣ ይዟል። ፓሻው፣ ባለፈው ጊዜ በነበረበት ክፍል ውስጥ ሆኖ ሲቀበለው፣ መድሃኒቱን ስላመጣለት ወዲያውኑ እቅፍ አደረገው። ጆን ባፕቲስት ብዙ ብልቃጦችን አወጣ። ዱቄት የተሞሉ የሱረት ብልቃጦችና የደረቁ ሥራስሮችን የያዘ ክረጢት ነበሩበት። ፓሻው ሁሉንም መድሃኒቶች በአንድ ጊዜ እንዳይጠቀማቸው መከላከል፣ የጆን ባፕቲስት ግዴታው ነበር። ቱርኮች መድሃኒት ይዳፈራሉ ብሎ፣ ሜትር ዠረሚ የነገረው ቢሆንም እንዲህ ይስገበገባሉ ብሎ አልገመተም።

«መድሃኒቶችን የሚያዘጋጅልዎ የተለየ አሽከር እንዳለዎት አምናለሁ። እርሱ ቢጠራና እነዚህን መድሃኒቶች እንዴት እንደሚያዘጋጃቸው በቀጥታ ከኔ ሰምቶ ሃላፊነቱን ቢወስድ የተሻለ ይሆናል» አለ ጆን ባፕቲስት

ፓሻው አጨብጭቦ፣ አንድ የሆነ ስም ጮሆ ተጣራ። የቤት ውስጥ ተላላኪው ወዲያውኑ ደረሰ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሽምገል ያለ አሽከር ገባና ለሁለቱ ሰዎች በአክብሮት ጐንበስ አለ። አዛውንቱ፣ አጭርና ቀጭን ሲሆን ባለቤቶቹ ያባረሩት፣ ረዣዥምም ቅልጥሞች ኖረውት ለመሮጥ ፈጣን የሆነ፣ ዓይኖቹ ማተኮር የሚችሉና የአዳኝ ውሻ የመሠሉ ሾጠጥ ያለ ፊት ያለው ነው።

«አብዱል መጅድ። አዳዲሶቹ መድሃኒቶች እኒሁና። እንዴት መጠቀም እንዳለብህ በሚገባ በጥንቃቄ አዳምጥ» አለው ፓሻው።

ጆን ባፕቲስት ሁሉንም ነገር በስፋት ተንትኖ ከነገረው በኋላ፣ ቦርሣውን ሳያስረክበው በፊት የተነገረውን በሚገባ መረዳቱን ለማረጋገጥ፣ አሽከሩ ሁሉንም ነገር መልሶ እንዲደግምለት አደረገው። ፓሻውም የመጀመሪያውን መጠን እዚያው በዚያ ሰዓት ለመውሰድ የሙጢኝ አለ።

«እስከ ብዙ ሣምንቶች እፎይታ አገኛለሁ ብለው አያስቡ» አለ ጆን ባፕቲስት

ይሁን እንጂ፣ ፈሣሽ መድሃኒት የመውሰዱ ጉዳይ በፓሻው ላይ አንዳች ሃይል ማሣደሩ አልቀረም። ኪኒን ከሚሠራበት የሲንኮና ዛፍ ቅርፊት የተዘጋጀለትን መድሃኒት ሲወስደው፣ ፊቱን እንደማጨማደድ አድርጎ ዕርካታ ካገኘ በኋላ፣ ባገኘው ነገር ሙሉ ደስታን እንዳገኘ

መነኮሣቱ ነበሩ:: ሰውነታቸው እንደ ነፃ ትግል ታጋይ በሚገባ ፈርጥሞ የተገነባና ቀጥ ያሉ ስለታም ጉራዴዎቻቸውን በካባዎቻቸው ላይ ባሉት ሰፋፊ ቀበቶዎቻቸው ላይ የታጠቁ ሁለት መነኩሳት መንገደኛውን ካስቆሙት በኋላ፣ ስሙን ለገዳሙ አበምኔት ላኩ:: መግባት እንደሚችል የሚፈቅደው መልስ ከመጣ በኋላ እንዲገባ ተደረገ::

በአጥሮቹ ውስጥ ያለው የቅድስት ካተሪን ገዳም እንደእውነቱ ከሆነ አንድ ከተማ ነበር:: በተክርስቲያኑ የሚገኘው መሃል ላይ ሲሆን ሌሎች ህንፃዎችና አዳራሾች፣ ተመሣሣይ መልክ ያላቸው መኖሪያዎችና ትናንሽ የፀሎት ቤቶች መጠነኛ ክፍተት በመሃላቸው እየተተወ ዙሪያውን ተገንብተዋል:: የግድግዳዎች፣ የመንገዶችና ተራ የመተላለፊያ ጉዳናዎች በምስራቅ ሜዲተራኒያን ከተሞች የሚታዩትን ዓይነት ናቸው:: እንደ መስቀል ጦር ተዋጊ፣ ስስና ወርቃማ የራስ ፀጉር ቀለም ያላቸው ወጣት መነኩሴ፣ ጆን ባፕቲስትን እየመሩት ወደ አበምኔቱ መኖሪያ ወሰዱት:: መኩሴው፣ የጆን ባፕቲስትን ሻንጣ ሲይዙለት፣ በቅሎውን ግን በመግቢያው በር ላይ ከሚገኙት መነኮሣት ዘንድ እንዲተወው መከሩት::

የቅድስት ካተሪን ገዳም የተመሠረተው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በጀስዊታውያን ነበር:: ከዚያ እስከ ዛሬ ድረስ መቆየት የቻለው በነዚሁ አጥሮቹ ነው:: ከዚህም በላይ ምናልባትም ሲወርድ ሲዋረድ በመጡት የሙሴ ዘሮች ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ግምት ባላቸው በነዚህ የተቀደሱ ተራሮች መከላከያነት ይሆናል:: በዚህ ቅድስተ ቅዱሣን ሥፍራ የሚኖሩት የኦርቶዶክስ መነኮሣት፣ የሚመሩት በቀጥታ በኢየሩሣሌም ፓትርያርክ ሥልጣን ሥር ነው:: ይሁን እንጂ ለአንድ የተለየ የሃይማኖት መስመር መሣሪያ ከመሆን በማለት፣ በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሣት የራሣቸው የሆነና ራሣቸውንም የሚያስተዳድር ሥልጣን ያለው ጠባቂ በዚህ አስፈሪና ምስጢራዊ በሆነ ቦታ ላይ መሠረቱ:: ወደዚህ ገዳም ሸሽተው የሚመጡና ከለላም የሚሹ ሰዎች፣ ከየትም ይምጡ ከየት ወይም ምንም ዓይነት ወንጀልም ፈፅመው ይምጡ፣ ደህንነታቸው የተረጋገጠ ነበር:: ጥቂቶቹ በዚህ ቦታ ላይ ለአጭር ገዜ ሲሰነብቱበት፣ ሌሎች ብዙዎች ደግሞ በቋሚነት ስለሚቀሩ፣ የኗሪው ቁጥር እንዲያድግ አድርገዋል:: ከብዙ ጊዜ ሃይማኖታዊ የደረጃ ዕድገት በኋላ ከነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ የገዳሙን ማህበረሰብ ለመምራት ጭምር ተስፋ ይኖራቸው ነበር::

በገዳሙ አበምኔት መኖሪያ ውስጥ የነበረው ሁኔታ፣ ጆን ባፕቲስት ከዚህ በፊት በመጀመሪያ ጉብኝቱ ወቅት ከሚያውቀው እጅግ አዲስና የተለየ ነበር:: መነኮሣቱ የሚነጋገሩት



እየተንሾካሾኩ ነበር:: የብርጉድና የክርቤ ሽታ፣ የድንጋይ ንጣፍ ባለባቸው መተላለፊያዎች በአየሩ ውስጥ ተበትኗል::

«የገዳማችን አስተዳዳሪ በጣም ታምመዋል» ሲሉ አበምኔቱ ለጆን ባፕቲስት ነገሩት:: ከሶስት ሣምንት በፊት ቅዳሴ ሥርዓት ላይ እያሉ ወድቀው ህሊናቸውን ስለሣቱ አንስተን ወሰድናቸው:: ይህ ሁኔታ ከገጠማቸው ወዲህ ቃላት አነጣጥመው ለመናገር ያቅታቸዋል:: በምሽት የህመሙ ስቃይ ይበረታባቸዋል:: ሲያቃስቱና አንዳንዴም ሲጮሁ እንሰማቸዋለን:: ባልደረባህ የሚጠጣ መድሃኒት ስለሰጣቸው እፎይታን የሚሰጣቸው ቢሆንም እኛ ግን እስካሁን እንደተጨነቅን ነን»

ጆን ባፕቲስት የገዳሙን አለቃ ለመመርመር እንዲችል ሃሣብ አቀረበ:: ይሁን እንጂ ከዚህ አስቀድሞ ውስጡን ሲበላው የነበረ ጥያቄ ነበረው::

«ጓደኞቼ፣ ሜትር ዠረሚና ሁለቱ ሴቶች የት እንዳሉ ይንገሩኝ»

«ስለነርሱ አትጨነቅ::» አሉት አበምኔቱ:: «እዚህ ከመጡ ሁለት ሣምንት አልፏቸዋል:: እስካሁንም አንተኑ ነው የሚጠብቁህ:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ ግን ትናንትና የኛው ወንድሞች በተራራው ጫፍ ላይ ባንዲት አንዲት የፀሎት ቤት አጠገብ ሆነው የማለዳዋ ፀሐይ ስትወጣ ለማየት ሄዱ:: እዚህ ምንም የሚሠራ ነገር ባለመኖሩ ሣይሰላቹ እንዳልቀሩ ነው:: ወጣ እንዲሉ ሃሣቡን የሰጧቸው እኔ ስለነበርኩ አዝናለሁ:: ይሁን እንጂ በማንኛውም ሁኔታ ነገ ጧት ተመልሰው እዚሁ ይደርሣሉ::»

ጆን ባፕቲስት ለጊዜው ተስፋ እንደመቁረጥ ካለው በኋላ፣ መልካም የዕረፍት ለሊት ሊያገኝ፣ ልብሶቹንም ለመቀየር እንደሚችል ለራሱ በመንገር፣ በአካልና በአዕምሮ ብርታት አግኝቶ፣ በማግስቱ ጧት ሊያገኛቸው እንዲችል ለመሄድ ወሰነ::

የገዳሙ አበምኔት፣ ጆን ባፕቲስትን ወደ አስተዳዳሪው መኝታ ክፍል አስገቡት:: የመኝታ ክፍሉ ሰፊ ሲሆን፣ ረገቻቹሞቹ መስኮቶቹ ለምለም ሣርና የደወል ቅርፅ ያላቸው አበቦች ፈንድተው ወደሚታዩበት ስገነት ይከፈታሉ:: በአንደኛው ግድግዳ ላይ የባቢሎንን ግንብ የሚወክል የሰጋጃ ጥልፍ ተሰቅሏል:: የገዳሙ አስተዳዳሪ የንድፍ ሥራ ባለሞያ ሆነው ደማስቆስ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ኖረው ነበር:: ነገር ግን ከባለቤታቸውና ከሁለት ወንዶች ልጆቻቸው ድንገተኛ ሞት በኋላ እግራቸው እንደመራቸው ወደፊት ተጉዘው የሲና ተራራን

ጉዳና ገቡበት። ሲና ከገቡ ወዲህ፣ ቅድስት ካተሪንን ለቅቀው ወጥተው አያውቁም። ከአስር ዓመት ባነሰ ጊዜም ውስጥ ከፍተኛው መሪዋ ለመሆን በቅተዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ሲና ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰነበተበት ሰሞን እኒህ ሰው ገዳሙን ለማስፋፋት የሚያስችላቸውን ንድፍ ለማዘጋጀት የፕላን መሥሪያ ኮምፓሳቸውን፣ ማዕዘን ማውጫዎችንና ማስመሪያዎቻቸውን በመገልገል ላይ ነበሩ። በአንድ ጠርዝ አጠገብ የተቆለሉ የወረቀት ጥቅሎች ይታያሉ። እነዚህ ያለጥርጥር ያልተገበደዱ ሥራዎቻቸው ይሆናሉ።

ምስኪኑ ሰው፣ ሊለዩ በማይችሉበት ደረጃ ከስተዋል። ፊታቸው እንቅልፍ በማጣትና በጭንቀት ተሸብሽቧል፣ ቆዳቸው እንደሰም ገርጥቷል። አፋቸውም የስቃዩ መጠን ስላየለባቸው ተጣምሟል።

«ሁሉም ነገር ከመፈፀሙ በፊት በድጋሚ አንተን የማየት ዕድል ስላገኘሁ በጣም ደስ ብሎኛል» አሉት በመከራ።

አንዳች ቃል ለመተንፈስ አቅም የሌላቸውን ሰው የደረቀ እጅ፣ ጆን ባፕቲስት ጠበቅ አድርጎ ያዘ። ሽማግሌው ወዲያውኑ አሸለቡ። ዶክተሩ ከክፍሉ ውስጥ ሹልክ ብሎ ወጥቶ አበምኔቱን አገኛቸው። ስቃዩን እያስታገሱላቸው ሊያቆዩዋቸው ብርቱ ተስፋ የነበራቸው ቢሆንም፣ መሞታቸው የማይቀር መሆኑን አረዳቸው።

«እጅግ የተለየ የሚሆነው ነገር» አሉ አበምኔቱ። «እርሣቸው ይህንንም ወይም ያኛውን ፈፅሞ አይፈሩም። ይበልጥ የምንጎዳው ግን እኛ ነን»

«እንደማስበው በሁለት ቀናት ውስጥ . . . »

አበምኔቱ የመስቀል ቅርፅ አመላክተው አማተቡ። እንባቸውንም ጠራርገው፣ ለጆን ባፕቲስት ወደ ተያዘለት ክፍል ይዘውት ሄዱ።

❧

የፀሐይዋን አወጣጥ ከሚመለከቱበት የማረፊያ ቦታ ወርደው፣ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ሲሆን በመምጣት ላይ ሣሉ፣ ፍራንቾይዝና ገብረማ፣ ጆን ባፕቲስት ከገዳሙ ወጥቶ ሽቅብ ሲመጣ አገኙት። ሞቅ ባለ ሁኔታ አቅፈውት ሰላምታ ከሰጡት በኋላ ስለጉዞውና ስለአመጣጡ ጠየቁት። እርሱ ግን ስለአሊስ ተጨንቆ ነበር።



«ለጥቂት ወደ ኋላ ቀረት ብላ ነው። ለአጭር ጊዜ ያህል ብቻዋን መሆን ስለፈለገች ነው። ከዚህ ብዙም በማይርቀው ከቤተመቅደሱ ባሻገር፣ በትልቁ ማህበረሰብ መሬት ላይ ታገኛታለህ» አለችው ፍራንቾይዝ።

እነርሱን ትቶ በመሄዱ ይቅርታ ጠይቆ፣ ጆን ባፕቲስት የእግር መንገዱን ተከትሎ ሽቅብ ቀጠለ። ጊዜው ሞቃት ስለነበረ ጃኬቱን አውልቆ ትከሻው ላይ አደረገው። እነስተኛዋ ቅድስተ ቅዱሳን በመንገድ መጠማዘዣ አጠገብ በድንገት ታየች። ቤተክርስቲያኗ ተራ የድንጋይ ጎጆ ናት። ጣሪያዋም በቅርፅ የለሽ የድንጋይ ቁርጥራጮች የተሠራ ነው። መከማቱ፣ ሌላው ቀርቶ የመስቀል ቅርፅ እንኳ በላይዋ ላይ አላቆሙም። ይህን ያደረጉት የተለያየ እምነት ኖሯቸው ሃሣባቸውን ሰብስብ አድርገው ራሣቸውን መግዛት ለሚፈልጉ ጎብኚዎች ካላቸው አክብሮት የተነሣ ነው። ሕንፃውን፣ ከአንድ ባህረገብ መሬቱ ላይ ካለ ቋጥኝ ጋር የሚያገናኝ አነስተኛ ደልዳላ መሬት ሲኖር፣ ቀጥ ብሎ የሚታየው ቋጥኝ አንድ የተንጠለጠለ አካል ይመስላል። በዚህ ቦታ መሬቱ በሦስቱ ማዕዘኖቹ የሰመጠ ስለሆነ፣ የፀሐይዋን አወጣጥ ለማየት የሚጋርድ እንቅፋት የለም። በነዚህ የድንጋይ ቅርፃች መካከል ጆን ባፕቲስት፣ አሊስን ለይቶ አወቃት። ወይም መኖርዋን ተገነዘበ። እርስዋም ብትሆን እንደተመለከተችው ተመሣሣይ ሃሣብ አድርባት ባለችበት ቆመች። ወደርስዋ ሮጠ። አሥር እምጃዎች ያህል ሲቀረው ሆን ብሎ ርምጃውን አንቀረፈፈው። ምን ያህል ተለውጣለች! ፊትዋ፣ ሰውነትዋና አቋቋምዋ በአጠቃላይ የጉመራ ነው። ውበትዋም ይበልጥ ያሸበረቀና የሚያበራ ሆኗል። የለበሰችው የፈረስ ግልቢያ ልብስ ነው። ጥብቅ በሚያደርጋት ጠባብ ልብስ የታሠረች አይደለችም። ፀጉርዋን ለቃዋለች። በርስዋ ላይ ከሚታየው የግርማ ሞገስ ድባብ ጋር ሲታይና ማንም ሊቆጣጠራት የማይችል መሆኑ ሲታወቅ፣ ይህ ሁሉ ነገር ኢምንት ነው። እርስዋም በበኩልዋ፣ እርሱ ባልነበረባቸው ጊዜያት፣ አብሯት ያኖረችውን የደከመ ቅርፅ፣ ይበልጥ የደቀቀ ሆኖ ሲታያት እንዳልነበረ ሁሉ፣ አሁን ብርቱና ሃያል ቁመናው ጎልቶ ወጣ። ብሩህ ዓይኖቹና ተዋህደው የሚታዩት የብርታትና የቁመና ዛላው የርሱን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እንደነበረ አድርጉ አሣያት።

ሁሉም ነገር እንግዲህ ይኸው ነው። ሁሉም እንቅፋት ተሸንፏል። ጠጠራማ ከሆኑ አሥር እርምጃዎች ያህል ከሚሆን ስፋት በስተቀር ሁለቱን የሚለያቸው አንዳችም ነገር የለም። የደምና የዘር ልዩነት፣ የአባቷ ተቃውሞ፣ የንጉሡ ግዴለሽነትና የብዙ ሰዎች ምቀኝነት፣ በእግራቸው ሥር ሆኖ ከሚንከባለለውና ቀልጦ ከቀዘቀዘው የእሣተ ገሞራ ፍርክስካሽ የበለጠ ጉዟቸውን ሊያደናቅፈው የሚችል አይደለም።

